## 3.4.2. ሊከሰት የሚችልን ግጭት ጠቋሚዎች

በሀዲያ ሴራ ሊከሰት የሚችል የግጭት ሁኔታ መኖሩን ለመለየትና ለመጠቆም የሚያስችሉ የተለያዩ ዘዴዎች አሉ። ከእነዚህ መካከል በግለሰቦች ወይም በቡድኖች መካከል ሊኖር የሚገባው ማህበራዊ ግንኙነት መቀነስ እንደ አንድ ጠቋሚ ይወሰዳል።

በግለሰቦች ወይም በቡድኖች መካከል ሁል ጊዜ ግንኙነትና መረዳዳት ተጠናክሮ በሚታይባቸው እንደ ሰርግ፣ የቀብር ቦታ፣ እድር፣ የገበያ ስፍራ እና የመሳሰሉት አጋጣሚዎች ላይ የግንኙነት መቀዛቀዝና አለመረዳዳት ከታየ ችግር እንዳለ መረዳት ይቻላል። ሌላው ሊከሰት የሚችል ግጭት መኖሩን ከሚጠቁሙ ሁኔታዎች የሚጠቀሰው፣ ሴቶች በጋብቻ ከሚኖሩባቸው የጐረቤት ማህበረሰብ ዘንድ ወደ ተወለዱበት አካባቢ ዘመዶቻቸው የሚያመጧቸው መረጃዎች ናቸው። የሀዲያ ሴቶች እርስ በርስ ያላቸው ግንኙነትና አካባቢያቸውን በጥንቃቄ የመከታተል ከፍተኛ ችሎታቸውን በመጠቀም በባሎቻቸው ዘመዶች አካባቢ በስጋ ዘመዶቻቸው ላይ ያነጣጠረ ምንም ዓይነት የግጭት ዝግጅት ካለ ሁኔታውን ለሥጋ ዘመዶቻቸው ይጠቁማሉ።

ከላይ ከተጠቀሱት ሁኔታዎች በተጨማሪ የግጭት ሁኔታን ለመተንበይ የሚያስችሉ በርካታ ባህላዊ ምልክቶችን በጥንቃቄ መመርመርና መተንበይ በሀዲያ ህዝብ ዘንድ የተለመደ ነው። በዚህም መሠረት የልጆች የአጨዋወት ሁኔታና በጨዋታ ወቅት ልጆቹ የሚጠቀመሟቸዉ ቃላት፣ ከግጭት አመላካች ዘዴዎች ዉስጥ ይጠቀሳሉ። ከዚህም ባሻገር በህዝቡ ባህል የሚታመንባቸዉ ሌሎች ከእምነት ጋር የተያያዙ አሌቶች አሉ። ከእነዚህም ዉስጥ የንፋስን አቅጣጫና እንቅስቃሴ፣





የጨረቃን ቅርጽና አቅጣጫ፣ የጸሀይ አወጣጥና አገባብ፣ የታረደ እንስሳን አንጀት ማጥናት፣ የጅብ ጩሃትንና የወፎች ጫጫታን በሀሪይና አቅጣጫ እና የመሳሰሉትን ክስተቶችና ሁኔታዎችን በመተንተን ሊከሰት የሚችል ግጭት መኖሩን ይጠቁማሉ።

ምንም እንኳን በሰው ልጆች ታሪክ እንደሚታወቀው ግጭትን ፈጽሞ ማስወገድ ባይቻልም ከላይ የተጠቀሱት ጠቋሚ መረጃዎችን በመጠቀም የሀዲያ ህዝብ የግጭትን መጠንና የሚያስከትለውንም ጉዳት ለመቀነስ ጥረት ያደርጋል። ይህንን ውጤት ለማምጣትም የሀዲያ ህዝብ ሴራው ያስቀመጠለትን ዘዴዎች በመጠቀም የታዩትንም ሆነ ሊከሰቱ የሚችሉ ግጭቶች መኖራቸዉን የሚያመለክቱ ሁኔታዎችን ለማጣራትና አስፈላጊውን የቅድመ ጥንቃቄ እርምጃ ለመውሰድ መረጃ የመሰበብሰብና የመተንተን ስራ ይሰራል። መረጃ በሚሰበሰብበት ወቅት ትልቅ ትኩረት የሚሰጠው ማንኛውንም ያልተለመዱ እንቅስቃሴዎችና ግንኙነቶችን መከታተል ይሆናል።

እንደዚህ አይነት እንቅስቃሴዎችን ለመከታተል በማህበረሰቡ ውስጥ ለለከትትሉ ጥርጣሬን በማያጭር ሁኔታ መረጃ የሚሰበስቡ ግለሰቦች ይመደባሉ። ምክንያቱም ማንኛውም አይነት ጥርጣሬ ካለ የግጭቱን እውነተኛ ምክንያት ለመረዳት የሚያስችሉ መረጃዎች ስለሚደበቁ ነው። በእንደዚህ አይነት ግለሰቦች አቅም መረጃን ለመሰብሰብ የሚያስቸግር ከሆነና የግጭት ሁኔታው ሰፊ መልክአ ምድራዊ አካባቢን የሚያካልል ከሆነ ሰላይ ፈረሰኞች የአካባቢውን የተለያዩ ዳርቻዎች እንዲቃኙና መረጃ እንዲያሰባስቡ ይደረጋል።

የተገኘውንም መረጃ በመጠቀም በተቻለ መጠን ግጭት እንዳይከሰት የሚያስችሉ ውይይቶችን ሊገጩ በሚችሉ ወገኖች መካከል እንዲጀመር ይደረጋል፡፡

### 3.4.3. ህድሮ

በሀዲያ ሴራ ግጭትን ለመከላከል ጥቅም ላይ ከሚውሉ ዋነኛና በጣም ውጤታማ ከሆኑ ዘዴዎች የሚጠቀሰው መሃላ (ህድሮ /Hidiro/) ነው፡፡ እንደዚህ አይነቱ መሃላ የሚፈጸመው በሁሰት ትልልቅ ቡድኖች መካከል ይሆናል፡፡ የሀዲያ ህዝብ በውስጥም ሆነ ከአጐራባች ማህበረሰቦች ጋር በርከት ያሉ (ህድሮዎችን /Hidilluwwa/) በመግባቱ ሊከሰቱ የሚችሉ የግጭቶችን መጠን በእጅጉ ሊቀንስ ችሏል፡፡ ለምሳሌ፣ በሶሮ /Sooro/ እና በሌሞ /Leemo/ የሀዲያ ጊቾዎች መካከል ህድሮ ከተፈጸመ ወዲህ ይህ ነው የሚባል ጠንካራ ግጭት ተከስቶ አያውቅም፡፡ በመሆኑም ከረጅም ዘመናት ጀምሮ ያለ ግጭት በሰላም እየኖሩ ይገኛሉ፡፡

በአጠቃላይ ህድሮ በግጭት ወቅት የነፍስ መጥፋት ወይም የንብረት ውድመት ቢከስት በቁም በቀል ስሜት ግጭቶች እየተስፋፉ እንዳይሄዱና ተጨማሪ የህይወት መጥፋትና የንብረት ውድመት እንዳይከሰት፣ በተጋጩት ቡድኖች መካከል እውነተኛ መከባበርና መተባበር እንዲሰፍንና ተመሳሳይ ግጭት እንደገና እንዳይከሰት በማድረግ በጣም ውጤታማ የሆነ የሀዲያ ሴራ አካል ነው፡፡

በሀዲያ ጐሳዎች መካከል የሚገባው ህድሮ መሃላውን በፈጸሙ ጐሳዎች መካከል ጋብቻ የሚከለክል ዝምድናን በመፍጠር የሚጠናቀቅ ነው፡፡ የሀዲያ ህዝብ ከሌሎች የአካባቢ ማህበረሰቦች ጋር የሚገባው ህድሮ ጋብቻን የሚከለክል





ባይሆንም በመሃላው ወቅት ተቆጥሮ የተገባውን ቃል የማክበርን ግዴታ የሀዲያ ሴራ ያስቀምጣል፡፡

አብዛኞቹ የሀዲያ አዛውንት እንደሚያስረዱትና እንደሚስማሙበት በኦሮሞ የሞጋሳ ስርአት ውስጥ አብዛኛው የሀዲያ ህዝብ በዛሬው ሰፊ የኦሮሚያ አካባቢዎች ተውጠው እንዲቀሩ ለማድረግ በኦሮሞ መስፋፋት ዘመን ጥቅም ላይ ከዋሉት የሀዲያ ሴራ ስርአቶች ዋነኛው ህድሮ እንደነበረ ይነገራል፡፡ የሀዲያ ሴራ ለህድሮ የሚሰጠውን ቦታና የሀዲያ ህዝብ ህድሮ በገባበት ጉዳይ ላይ ያለውን ታማኝነት የኦሮሞ ተስፋፊ ሃይሎች ከኦሮሞ ህዝብ ተመሳሳይ ባህላዊ እሴት ጋር በማጣመር በአግባቡ መጠቀም እንደቻሉ ይነገራል፡፡ በሀዲያ ሴራ መሰረት ከተፈጸሙና በሀዲያ ብሄር ውስጥ ከሚታወቁት ህድሮዎች መካከል ጥቂቶቹ የሚከተሉት ናቸው፡፡

| *የሀድሮው መጠሪያ* | *ህድሮ የፈጸሙ ቡድኖች* | *የተፈጸመበት ቦታ* |
|---|---|---|
| አርያና ሄገናና | /Ariyannaa Heganannaa/ | ሌሞ /leemo/ |
| ኡንጃሞ ብቂቆ | /Uunjamoo Biqqiiqqoo/ | ሌሞ /leemo/ |
| ሆጐአና ዳቸና | /Hogo'annaa Daachchanna/ | |
| ጨንጌአና ሞሎልቾ | /Caange'annaa Molloolliichchoo/ | ሻሾጎ /shaashoogo/ |
| አሾአና ሀይባ | /Ooshsho'annaa Hayyibbaa/ | ሌሞ /leemo/ |
| ዳሞኦ ሳንኮኦ | /Daamo'oo Sankoomaa/ | ሶሮ /Sooro/ |
| አሼኤ አውራራ | /Aashe'ee Awuraaraa/ | |
| ዶቦኦ ኩሾኦ | /Doobbo'oo Kushsho'oo/ | |

| የሀድሮው መጠሪያ | ሀድሮ የፈጸሙ ቡድኖች | የተፈጸመበት ቦታ |
| --- | --- | --- |
| ኮብርመና/ Kobirmanna/ | /Bohaalle Aefo'oo/ | ባደዋቾ/ Baadawwachcho/ |
| ኦዬሜ | /Ansoommee Wogo'oo/ | ባደዋቾ/ Baadawwachcho/ |
| ሀዲያ፣ አማራና ከንባታ | | |

### 3.4.4. ዋንኛዎቹ የግጭት መንስኤዎች

የሀዲያ ህዝብ በርከት ባሉ ምክንያቶች የርስ በርስም ሆነ ከሌሎች ማህበረሰቦች ጋር ግጭት ውስጥ እንዲገባ ሊያደርጋው የሚችል ምክንያቶች አሉት፤ እነዚህን ምክንያቶች ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊ፣ ባህላዊ፣ ፖለቲካዊና ስነ ልቦናዊ ብሎ መመደብ ይቻላል።

ኢኮኖሚያዊ ባህርይ ያላቸው የግጭት መንስኤዎች በአብዛኛው የሚያያዙት እያደገ የመጣው የህዝብ ቁጥር ካሰው የእርሻና የግጦሽ መሬት እንዲሁም የውሃ ፍላጐት ካሰመጣጣም ጋር ነው። ከግጭት መንስኤዎች የኢኮኖሚ በህርይ አላቸው ተብሰው ከሚወሰዱት ውስጥ ለእርሻና ለግጦሽ መሬት የሚደረግ ፉክክር፣ ውሃንና የዱር እንጨትን ለመቆጣጠርና ለመጠቀም የሚገበ ሽኩቻና የድንበር መግፋት፣ የእንስሳትና የሌላም ንብረት ዘረፋና ሌብነት በዋነኝነት ሊጠቀሱ ይችላሉ።

የኢኮኖሚ መነሻ ያላቸውን ግጭቶች በጣም አደገኛ የሚያደርገው፣ ተጋጮቹ እንደ መሬትና ውሃ ያሉትን





መሰረታዊ ሀብቶች በዘላቂነት ከሌላው ለመንጠቅ ወይም በእጃቸው ለማቆየት የሚያደርጉት ትግል መሆኑ ነው። የኢኮኖሚ መነሻ ካላቸው ግጭቶች ውስጥ ባለፉት ቅርብ አመታት ውስጥ የነበሩትን ብቻ እንኳን እንደምሳሌ ብንወስድ በሀዲያና በዳውሮ በግጦሽ መሬትና በከምባታና በሀዲያ መካከል በእርሻና በግጦሽ መሬት ምክንያት የታዩትን አለመግባባቶች መግለጽ ይቻላል።

ማህበራዊ ግንኙነትን መነሻ በማድረግ ከሚከሰቱት ግጭቶች መካከል በጋብቻ ምክንያት የሚፈጠሩ አለመግባባቶች፣ የሰውን ሚስት መድፈር፣ ነፍስ ማጥፋት፣ ነውርና ያልተገባ ተግባርን መፈፀም፣ ሌላውን መናቅና ዝቅ አድርጐ መመልከት በዋነኝነት ሊጠቀሱ ይችላሉ። በጋብቻ ምክንያት የሚከሰቱ ግጭቶች በርካታ ባህርያትን የያዙ ናቸው። ለምሳሌ፣ ለሌላ ሰው ለትዳር የተዘጋጀች ወይም ቃል የገባችን ልጃገረድ አታሎ ወይም ሀይልን ተጠቅሞ ማግባት፣ ከባልዋ ተለይታ የምትኖር ነገር ግን በባህላዊ ወይም በህጋዊ መንገድ ፍቺ ያልፈጸመችን ሴት /Gooraame/ ማግባትና ባልዋ የሞተባትን ሴት የባልዋ ቤተሰቦች ወራሽ ባል እንዲሆን ከፈቀደው ሰው ውጪ ማግባት፣ የባልን ወይም የእጮኛን ወገን በአጠቃላይ እንደመናቅ ስለሚቆጠር ከፍተኛ ግጭት እንዲቀሰቀስ ምክንያት ሊሆን ይችላል።

በሀዲያ ህዝብ ውስጥ የሚኖሩና ህዝቡ በአንዳንድ ጉዳዮች እኩል ስፍራ የማይሰጣቸው ጐሳዎች ክልክል በሆኑ ጉዳዮች ሲሳተፉ ግጭቶች የመቀስቀሳቸው እድል ሰፊ ነው። ለምሳሌ፣ የሀዲያ ብሄር ተወላጆች በአካባቢው ከሚኖሩትና በሸክላ ስራ ከሚተዳደሩ የፉጋ /Fuga/ ጐሳ ጋር የጋብቻ ዝምድና

እንዲፈጥሩ አይፈቀድላቸውም፡፡ ይህንን ክልከላ በመጣስ ፉጋ ከሀዲያ ጋር ጋብቻ ፈጽሞ /ፈጽማ/ ቢገኝ /ብትገኝ ጉዳዩ ግጭትን የመቀስቀስ አቅም አለው፡፡ ባህላዊ መነሻ ያላቸው የግጭት ምክንያቶች በዋናነት የሚያያዙት በሀዲያ ባህል መሰረት ክብር ለማግኘትና ዝናን ለማትረፍ የህዝቡ ባህል ከግጭት ተሳትፎ ጋር በማያያዝ የሚያሳድረው ተጽእኖ ነው፡፡ በዚህ መሰረት በሀዲያ ባህል አንድ ሰው ትልቅ ክብርና ዝና ሊኖረው ከሚችልባቸው መንገዶች አንዱ በጦርነት ወቅት የሚፈጽመው ታላቅ ጀብዱ ነው፡፡

ጀብዱ መፈጸሙን ከሚያመለክቱት መንገዶች መካከል ዋነኞቹ ጠላትን መግደልና[53] መማረክ ናቸው፡፡ ጦርነት በማይኖርባቸው ወቅቶች የሀዲያ ወንድ ዝናንና ክብርን ለማግኘት በአደን በመሳተፍ አደገኛ የሆኑ እንደ አንበሳና ነብር

[53] በሀዲያ ባህል አንድ ሰዉ ጠላትን ሲገድል በእጁ ጣቶች ቢጫ ቀለም ያለዉን የብረት ቀለበት እንዲያጠልቅ የሚፈቀድለት ሲሆን፣ ይህም ጀግንነት በድራንቻ /Diraancha/ ወይንም ሙዚቃዊ ግጥም ይሞገሳል፡፡ ለምሳሌ፣ በብራዉካምፔር (1999 : 53) ላይ የሚከተለዉን ድራንቻ /Diraancha/ እናገኛለን፡፡

| *ሀዲይሳ* | *ያማርኛ ፍች* |
|---|---|
| ጉለእ ዴድ ዌየኪ | |
| Gula'i deed weyyakkii | |
| ግንድ ኦሸች ኦዴኤ | የግንዶ ልጅ ኦዴ |
| Gind oosichchi odde'ee | |
| ጉቤዳሞ ቃያቲ | ባሰ ትልቅ ጉልበታሙን ገሉ |
| Gubeedaamo qayyaatii | |
| ጉማዕ ሶስ አገና | ቀሰበቶቹ እንደ ሙሉ ጨረቃ ያበራሉ |
| Guma'i soos agana | |





የመሳሰሉ አዉሬዎችን መግደል[54] ይጠበቅበታል፡፡ ከላይ የተጠቀሱትንና ሌሎችንም የወንድነትና የጀግንነት መገለጫ የሆኑ ተግባሮች ያላከናወነ ወንድ በወንድሞቹ ሚስቶች (ሄሬዋ /Hereewwa/) እና በጓደኞቹ ሚስቶች ደካማነቱን የሚገልጹ ስድቦችና አሽሙሮች ይከተሉዋል፡፡

ከዚህ በተጨማሪ የፈረስ እቃው /ማስዋቢያ/፣ የልጆች ስምና ባል ሲሞት ሚስት ለሀዘን[55] የሚትለብሰዉ ልብስ የግለሰቡን ባህላዊ ቦታ የሚያንጸባርቅ እንዲሆን ይደረጋል፡፡ ይህንን የባህላዊ ጥያቄ ጫና ለመቋቋም ማንኛውም የሀዲያ ወንድ ለጦርነትና ለአደን ይሽቀዳደም እንደነበረ ይነገራል፡፡ ምንም እንኳን የዚህ ዓይነቱ አመለካከት በዚህ ዘመን የቀረ ቢሆንም ለረጅም ዘመናት ህዝቡ ጦርነት ናፋቂና በግጭቶች ተሳታፊ ሆኖ እንዲቆይ የራሱ ሆነ አስተዋጽኦ አበርክቷል፡፡

[54] በሀዲያ አደገኛ አዉሬ ለገደለ ወንድ ከሚባሉት ድራንቻዎች ዉስጥ የሚከተለዉን ከብራዉከምፔር (1999: 60) ላይ እናገኛለን፡፡

| *ሀዲይሳ* | *ያማርኛ ፍች* |
|---|---|
| ጎምቦዕል ለም ዕዶም | የጎምቦራ ወንዝ ሁለቱንም ማዶ |
| Gombo'l lam idom | |
| ገሮ ጊች ቤቶ | የሚኖር ጎሳ ልጅ |
| Garo giichchi beetoo | |
| ጎንች ሆብች ሳዎ | የወንድ አንበሳ ጓደኛ |
| Goonch hobbichchi saawwo | |
| መጭ ቤሌጫሞ ( ለገዳይነታቸዉ እንደምልክት ጆሮ ላይ የሚንጠለጠል የብረት ጉትቻ) | ባለ ጉትቻ |
| Macci belecaamoo | |
| ሜንት አድዕል ሄሮ | ምራቶቹ ነገስታት ምስቶች |
| Meent adi'l hero | |

[55] ለምሳሌ በሀዲያ ባህል ሚስት በሃዘን ወቅት በፀጉሯ ላባ ስክታ እና የኣንበሳ ወይንም የነብር ቆዳ ለብሳ ማልቀስ የሚፈቀድላት ባሏ ጀግና ከሆነ ብቻ ነዉ፡፡

በሀዲያ ህዝብ ውስጥ ለግጭት መንስኤነት ተጠቃሽ ተደርገው የሚወሰዱት ፖለቲካዊ መንስኤ ያላቸው ጉዳዮች በርካታ ናቸው። ከነዚህም ውስጥ በሀዲያ ሴራ /seera/ ባህላዊ አስተዳደር መዋቅር የመሪነት ስልጣንን ሴራው በአስቀመጠው መስፈርት መሰረት፣ የመዋቅሩ አባላት በስምምነት ከለጡት ግለሰብና ቤተሰብ እጅ በሀይል ለመንጠቅ የሚደረግ ሙከራ ከፍተኛ አለመግባባትና ግጭትን ያስከትላል።

ይህንን አይነት ሁኔታ የሚከላከለው ስልጣን ያለው ግለሰብ ብቻ ሳይሆን አጠቃላይ የመዋቅሩ አባላትና የባለስልጣኑ የቅርብ ዝምድና ያላቸው ወገኖች ይሆናሉ። በመሆኑም የዚህ አይነት ግጭት በርካታ ሰዎችን የማሳተፍ አቅም ያለው በመሆኑ ጉዳቱም እጅግ የከፋ ሊሆን ይችላል።

ፖለቲካዊ መገለጫ ያለው የግጭት መንስኤ ተብሎ የሚወሰደውና የሀዲያ ህዝብ ታሪካዊ መለያ የመሆን ደረጃ የደረሰው የግጭት ምክንያት፣ የሀዲያ ህዝብ ለዘመናት እራሱን በራሱ ለማስተዳደር ሲያደርጋቸው የኖረዉ ግጭቶችና ጦርነቶች ናቸው። የሀዲያ ህዝብ በየዘመኑ ከተነሱትና የሀዲያን ማንነትና ራሱን በራሱ ማስተዳዳር መብት ከማይቀበሉ ወገኖች ጋር ብዙ ዋጋ ያስከፈሉ ጦርነቶችን አካሂዷል።

### 3.4.5. የግጭት አፈታት ዘዴዎች

የሀዲያ ሴራ የጉዳይ አቀራረብ፣ ጉዳዩ የሚቀርብበት የሴራ መዋቅርና ጉዳዩ የሚቀርብበት ቦታ እንደተከሰተው ግጭት ይለያያል። በአጠቃላይ በጣም ቀላል የሆኑና በአካባቢ ደረጃ ተደጋግመው የሚከሰቱ ግጭቶች የሚያስከትሉትም ጉዳት የተሳታፊዎቹም ብዛትና ስብጥር በአብዛኛው ከአንድ ቤተሰብ





ስለሚሆን በታችኞቹ መዋቅሮች ማለትም በምኔ ፣ ነፈራ እና ሞሎ ደረጀ ይታያሉ።

ከባድ ግጭቶች የሚያስከትሉት ወይም ሊያስከትሉ የሚችሉት ጉዳት ከባድ በመሆኑና የተሳታፊዎች ብዛትና ስብጥርም ስለሚያስገድድ በአብዛኛው የሚታዩት በላይኛው የሀዲያ ሴራ መዋቅሮች ማለትም በሱሎ ፣ በጊቾ ወይንም በጊራ ደረጃ ይሆናል። አንድ ግጭት ያስከተለውን ውጤት በማየት ቀላል ነው ተብሎ የሚወሰደው በግጭቱ ምክንያት የህይወት መጥፋት፣ ከፍተኛ የንብረት ውድመትና ዘላቂ የአካል ጠባሳ ወይም አካለ ጎዶሎነት ያልተፈጠረ ከሆነ ብቻ ነው።

ቀላል ግጭት ለሚመለከተው የሴራ መዋቅር የሚቀርበው በተበዳዩ ወይም በተበዳዩ የቅርብ ቤተዘመድ አማካይነት ይሆናል። ጉዳዩ የሚቀርብበት ቦታ በአብዛኛው ወደ መዋቅሩ መሪ (ዳና /Daana/) ቤት ወይም ደጃፍ በመሄድ ሊሆን አቀራረቡም፣ የጉዳዩን አጠቃላይ ገጽታ በማስረዳት ይሆናል። በመሆኑም የምኔ ፣ የሞሎ ወይም የነፈራ ዳና ጉዳዩን በመስማት አስፈላጊውን መፍትሄ መፈለግ ይጀምራል።

ከባድ ግጭቶች በሚከሰትበት ጊዜ ጉዳዩን ለሚመለከተው የላይኛው መዋቅር የሚያቀርበዉ የተበዳዩ ምኔ ፣ ነፈራ፣ ሞሎ ወይም ሱሎ ተወካይ ይሆናል። ጉዳዩም የሚቀርብበት ቦታ ጉዳዩን ሰሚ የሆነው የሴራ መዋቅር መሪና ሽንጎዉ በሚሰበሰብበት ሀፋ /Hafa/ ይሆናል። ሀፋ /Hafa/ የሞሎ፣ የሱሎ፣ የጊቾ ወይም የጊራ ሸንጐ በቋሚነት የሚሰበሰብበት በቂ ጥላ ያለው ትልቅ ዛፍ ስር ይቋቋማል። ይህ እንደ ሀፋ / Hafa/ ወይም ሸንጐ ቦታ የሚያገለግል ዛፍ በማህበረሰቡ

አጠቃላይ እጅግ የሚከበር ይሆናል፡፡ በታውና ዛፉ በመልካም እንክብካቤና በጥሩ ጥበቃ ከትዉልድ ወደ ትዉልድ እንዲተላለፍ ይደረጋል፡፡

ማንኛውም ደረጃ ያለው ጉዳይ የቀረበለት የሀዲያ ሴራ መዋቅር ካዳመጠ በኋላ ሰቀላል ግጭቶች በዳይ ራሱ /ራሷ/ እንዲቀርብ ወይም እንድትቀርብ በከባድ ግጭቶች ወቅት የበዳዩ ወይም የበዳዮች ምኔ ወይም ሞሎ ተወካዮችን እንዲያቀርቡ ጉዳዩን ያቀረበው ተበዳይ ወይም ተበዳዮች መልዕክት የሚያደርስ ሰው ወይም ቡድን ይዘው እንዲቀርቡና ቀጠሮ እንዲወስዱ በመዋቅሩ መሪና በሽንጉዉ ትዕዛዝ ይሰጣል፡፡

በዳይ በተላለፈለት የትእዛዝ መልእክት በተሰጠው ቀጠሮ ወደ ሴራ ሽንጉ ሲቀርብ ሁለቱም የተጋጩ ክፍሎች በሽንጉው መሪና በሽማግሌዎች (በሎመና /Lommanna/) ፊት የሚያቀርቡት ሀሳብ እውነት ብቻ እንደሚሆን በአምላካቸው (ዋኣ /Waa'a/) ስምና በአያቶች መንፈስ (አያና /Ayaana/) ስም በመሃል ያረጋግጣሉ፡፡

ምንም እንኳን ሁለቱም ቡድኖች የሚያቀርቡት ሀሳብ ወዲያዉኑ ወደ መፍትሄ ለማምራት የሚያስችል ቢሆን እንኳ ሌሎች ከጉዳዩ /ከግጭቱ/ የሚያያዙ ነገሮች አይታጡም ተብሎ ስለሚጠረጠር ጉዳዩን የያዘው መዋቅር መሪና ሽንጉው ተጨማሪ የማጣሪያ፣ መረጃ መሰብሰቢያና፣ መረጃ መተንተኛ ጊዜ ይወስዳሉ፡፡ ይህ ሂደት ውስብስብና ረጅም ሲሆን የሚችለው ግጭቱ ከባድ ሲሆንና ያስከተለውም ጉዳት ከባድ ከሆነ ነው፡፡





በተለይም ከባድ ግጭት ከተለከተና ያስከተለውም ጉዳት የህይወት መጥፋት፣ የቤት መቃጠል፣ የንብረት መውደም እና የአካል መጉደል ከሆነ በግጭቱ በተሳተፉ ቡድኖች መካከል ከተከሰተው ግጭት በፊት በነበሩት አጠቃላይ ዘመናት የነበራቸው ታሪካዊ ግኑኝነት /relationship/ በጥንቃቄ ይጠናል፡፡

በሀዲያ ሴራ ይህንን አጋጣሚ በመጠቀም ያላፉትንና የተደበቁትን የግንኙነት ችግሮች በመፍታት አዲሱንና በወቅቱ የቀረበውን የግጭት ጉዳይ በተገቢው መንገድ ፊቶ የወደፊት ግንኙነትን እጅግ ስላማዊና እውነተኛ እርቅ ላይ የተመሰረተ ለማድረግ እንዲቻል የማህበረሰቡን የግንኙነት ታሪክ ተንታኝ ወደ ሆኑና እጅግ ወደሚከበሩ ሰዎች (*ሀራጋኖ* /Hiraagaano/) ዘንድ ይኬዳል፡፡

ሀራጋኖ በማህበረሰቡ ውስጥ የተደበቁና ያላፉ የግጭት ምስጢሮችን በማውጣትና ሁኔታውን በመተንተን የወቅቱን ግጭት ድብቅ መነሻ /root -cause/ የሚያሳዩ ትልቅ የአዕምሮና የአስተሳሰብ ብቃት ያላቸው ግለሰቦች ናቸው፡፡ የሀራጋኖ ትልቁ አስተዋጽኦ በሀዲያ ህዝብ መካከል የሚኖረው ግንኙነት በአጠቃላይና በተጋጭ ቡድኖች መካከል የሚኖረው የወደፊት ግንኙነት በተለይ በእውነተኛ ፍቅርና ሰላም ላይ የተመሰረተ እንዲሆን ማስቻል ነው፡፡ ለዚህ አገልግሎታቸውም ከማህበረሰቡ ዘንድ ከሚሰጣቸዉ አክብሮት ውጭ ምንም አይነት ነገር አያስከፍሉም፡፡ ይህ የሀዲያን *ሀራጋኖ* ከጠንቋዮች (ኪራኖ /Kiirraano/) የሚለያቸው መሰረታዊ ባህርይ ነው፡፡

ጉዳዩ የቀረበለት መዋቅር በማጣራት ሂደት የደረሰበትን ጭብጥ ተከራካሪ ወገኖች የማይቀበሉት ወይም የሚክዱ ከሆነ ጭብጡን ያልተቀበለው አካል፣ ምኔ ወይም አባሮሳ የጉዳዩን ባሰቤት ወይም ባለቤቶች እንዲመክሩና ተጨማሪ ማስረጃዎችን እንዲያሰባስቡ ይታዘዛሉ:: ለዚህም የሚሆን ተጨማሪ ጊዜ ይሰጣል::

ይህ ሁሉ ተደርጐ የተደረሰበትን ጭብጥ አንደኛው ወገን የማይቀበል ከሆነ ነገሩን ያላመነው ወገን የያዘውን አቋም እውነትነት በመሃላ እንዲያረጋግጥ ይደረጋል:: የሚገባው መሃለ (ህዴቻ /hidechcha/) እንደየጉዳዩ ክብደትና ጉዳዮን እንደያዘው መዋቅር ይለያያል:: በታችኞቹ መዋቅሮች ደረጃ የመጨረሻው ውሳኔ ሲያገኙ የሚችሉ ቀላል ጉዳዮች ከላይ የተጠቀሰው ሁኔታ ሲያጋጥማቸው ዱዕምማ የሚፈጸመው የመዋቅሩን መሪና የሸንጐውን አባላት ጉልበት በመምታት ፣ የቤተዘመድ ጉባኤ አባላት አፍጥጠው እየተመለከቱ መሃላቸውን ሰንጥቆ በማለፍ፣ በማህበረሰቡ አደገኛ ናቸው ተብለው የሚታሰቡትን እንደ እሳትና ስለት ተሻግሮ በማለፍ ወይም በሽማግሌዎች የሚነገሩትን የመሃላ አረፍተ ነገሮችን፣ /ለምሳሌ ከታች የተመለከቱትን/ ደግሞ በማለት ይሆናል::

| | |
|---|---|
| ክዕኑዊ እል ቀሴ | የእናንተ ዓይን ይውጋኝ |
| Ki'nnuww ill qase | |
| ክዕኑዊ አያን ኤሴ ብዕሴ | የአባቶቻችን መንፈስ ያጥፋኝ |
| Ki'nnuw ayaan eese bi'iise | |
| እሊ መጪ ቤዕ ቀቾ ኡዌ | ዓይንና ጆሮ የሌለው አካል ጉዳተኛ ልጅ ይስጠኝ |
| Illii maccii bee'i qachcho uwwe | |





ቀላል ግጭት በእርቅና በስምምነት በሚፈጸምበት ወቅት በሀዲያ ሴራ /Seera/ ትልቁ የእርቅ ምልክት ተደርጐ የሚወሰደው በተፈጠረው ሁኔታ ተጸጽቶ ይቅርታ መጠየቅና ይቅር ባይነት ነው:: ይቅርታውና እርቁ በግጭቱ ወቅት የደረሰውን ጉዳት እንደጉዳቱ ዓይነት ለማካካስ ፈጽሞ ዝግጁነት ማሳየትንና መተግበርን ያጠቃልላል:: ለምሳሌ፣ ባል ሚስቱን በግጭት ወቅት ቢደበድባት ጉዳዩን የሚመለከተው በዋናነት የምኔ መዋቅር ሲሆን ግጭቱ በእርቅ ሲጠናቀቅ ባል በድብደባው ወቅት ያደረሰውን ጉዳት ሊጠግን የሚችል ጠቦት በማረድና ፍቅርን በማሳየት እውነተኛ እርቅና ሰላም መውረዱን ያሳያል:: ከዚህ በተጨማሪ በጉልበት ስራ መርዳት፣ የጠፋውን ንብረት በትብብር መተካትና የመሳሰሉት የእርቅ መገለጫ ተግባሮች ናቸው::

እንደ ማንኛውም ማህበረሰብ በሀዲያ ህዝብ ዘንድ የሰው ልጅ ነፍስ እጅግ ክቡር ነው ተብሎ ስለሚታሰብ የሀዲያ ሴራ የሰዎችን በህይወት የመኖር መብት እንዲከበር ከፍተኛ ትኩረት ይሰጣል:: ይህንን የሀዲያ ሴራ ባህርይ በቀላሉ መረዳት የሚቻለው በግጭት አጋጣሚ የሰው ልጅ ነፍስ ሲጠፋ ጉዳዩን በጥንቃቄ በመያዝ ለማጣራት፣ ለመመርመርና፣ ውሳኔ ለማስተላለፍ ያስቀመጣቸውን አካሄዶች በመመልከት ነው:: በሀዲያ ሴራ የህይወት መጥፋት ከፍተኛ ወንጀል ተብሎ ስለሚታሰብ ጉዳዩን የሚመለከቱት የላይኞቹ የሴራ መዋቅሮት ናቸው:: ከባድ በሆኑ ግጭቶችና ውጤታቸው ላይ የሀዲያ ሴራ ያለውን ህግና አፈጻጸም መረዳት እንዲቻል የነፍስ መጥፋትን ያስከተለ ግጭት በዋነኛ ምሳሌነት ሊጠቀስ ይችላል::

### 3.4.6. ሞትን ያስከተለ ግጭት በሴራ መዋቅሮች የሚታይበት መንገድ

በሀዲያ ሴራ መሰረት በግጭት የሚከሰት ሞት በተለያዩ አይነቶች ይከፋላል፡፡ እነርሱም፡-

ሀ. *ሁሸንቻ* /Huushanachcha/ ወይም *አዋዋ* /Awwaawwa/፡- ይህ ፈጽሞ የሰውን ነፍስ ለማጥፋት አላማ በሌላው ሁኔታና አጋጣሚ ሊከሰት የሚችልን የሞት አደጋ ይመለከታል፡፡

ለ. *ሀሎኦ* /Halo'o/፡- የዚህ ዓይነቱ ግድያ ቂም በቀል ይዞ አጋጣሚን በመጠቀም የሚፈጸም የሞት ሁኔታን ይመለከታል፡፡

ሐ. *ሀንታሮ* /Hantaaro/ ፡- የዚህ አይነት ሞት የሚከሰተው ሌላ ሰውን ወይም እንስሳን ለመግደል ሆነ ተብሎ የተደረገ ሙከራ የተሳሳተ ሰውን ሲገድል የሚፈጠር ሁኔታን ይመለከታል፡፡

መ. *ደምሀቅ-ሸና* /Dami'qqi-shanna/ ፡- ይህ አይነቱ የነፍስ መጥፋት፣ በአፊ እላፊ ወይም በሌላ ግጭት ምክንያት አመቺ ቦታና ጊዜ መርጦ በመጠበቅ የሰው ህይወት በማጥፋት የሚከሰት የሞት አይነት ነው፡፡

በሀዲያ ባህል አንድ ሀዲያ ሌላውን ሀዲያ መግደል አጠቃላይ የሀዲያን ህዝብና በተለይም የሟቹን ምኔ ፣ ሞሎ ፣ ሱሎ ወይም ጊቾ እንደመግደል ይቆጠራል፡፡ ለምሳሌ፣ የተመሳሳይ ሞሎ አባል የሆኑ ግለሰቦች በገቡት ግጭት የነፍስ መጥፋት ቢከሰት ገዳዩ የሟቹን አጠቃላይ ምኔ እንደገደለ ተደርጎ ከመወሰዱም በላይ የገዳይ ምኔ በአጠቃላይ እራሳቸውን እንደ ገዳይ በመቁጠር ይጸጸታሉ፤ ማንኛውንም ጥንቃቄ ያደርጋሉም፡፡





በመሆኑም በግጭት ወቅት የሞት አደጋ በሚከሰትበት ጊዜ የሞቱ ዓይነት የትኛውም ቢሆን ገዳይ ለቅርብ ቤተ ዘመዶቹ ክስተቱን በማስረዳት የገዳዩ ቤተዘመዶች የመኖሪያ አካባቢያቸውን ጥለዉ አቅራቢያቸው በሚገኘውና ከሟች ጋር የቅርብ ዝምድና በሌለው በሌላ ጐሣ ዘንድ ይሸሸጋሉ፡፡ ይህ እርምጃ በአንድ በኩል የሟች ዘመዶች በድንጋጤና በደም ፍላት ከሚወስዱት የበቀል እርምጃ ራስን ለመሰወር ሲሆን፣ በሌላ በኩል ገዳይና ዘመዶቹ ለሟች ወገኖች ያላቸውን አክብሮትና በጉዳዩ ላይ የተሰማቸውን ጸጸት ያንጸባርቃል፡፡

የዚህ አይነት የሀዲያ ሴራ የሚያስቀምጠው የመጀመሪያ እርምጃ ተጨማሪ ሞትን ከመከላከሉም በላይ በሟች ቤተሰቦች ዘንድ የመከበርን ስሜት በመፍጠርና የገዳይ ወገኖችን የጸጸት ስሜት በማንፀባረቅ ለቀጣይ ድርድርና ስምምነት ዓይነተኛ በር ከፋች ሚና ይጫወታል፡፡ በዚህ ሁኔታ ውስጥ የሟች ወገኖች በገዳይ ወገኖች ንብረት ላይ በደም ፍላት የሚያደርሱት ውድመት እንደ ንዴት ማብረጃ ስለሚቆጠር የከፋ ጉዳት እንዳያደርሱ የአካባቢው ሽማግሌዎች በልመና ቢያስቆሙም የደረሰው የንብረት ውድመት በተወሰነ ደረጃ ተገቢ ነው የሚል እውቅና ይሰጠዋል፡፡

ከሽሽትና ከተወሰነ የንብረት ውድመት በኋላ የገዳይ ወገኖች ቀጥለው የሚወስዱት እርምጃ በሟች ወገኖች ዘንድ ሊፈሩና ሊከበሩ የሚችሉ የሀዲያ ሴራ /Seera/ የከፍተኞቹ መዋቅሮች መሪ የሆኑና ሌሎችም ተዋቂ ሽማግሌዎች ወደ ሟች ወገኖች በመላክ የእርቅ ልመና እንዲጀምሩና ቤታቸውና መንደራቸው መመለስ እንዲፈቀድላቸው ድርድር እንዲጀመር ማድረግ ነው፡፡ ምንም እንኳን ይህ የእርቅና የድርድር ጅምር

እንቅስቃሴ በሟች ቤተሰቦች ዘንድ ወዲያውኑ ተቀባይነት የሚያገኝ ባይሆንም የሀዲያ ባህላዊ ዳኞች የአብሮ መኖርንና የሰላም'ን ጠቀሜታ በማስረዳት እንዲሁም የግጭትና የእርቅን ተፈጥሮአዊነት በመንገርና በመምከር ከተወሰነ ጥረት በኂላ ሁልጊዜ ወደ እርቅ ውይይትና ድርድር መገባቱ የተለመደ ነው፡፡

ከላይ የተጠቀሰው ሁኔታ የሚከሰተው በግጭት ወቅት ገዳይ በማያሻማ ሁኔታ የታወቀ ሲሆን ብቻ ነው፡፡ በመሆኑም ጉዳዩን ስሚመለከተው ተገቢው የሴራ መዋቅር በማቅረብና በማስረዳት ጉዳዩ እንዲታይ የሚያመለክተው ተበዳይ ሳይሆን በዳይ (ገዳይና ቤተዘመዶቹ) ይሆናሉ፡፡ አንድ ሀዲያ የሆነ ግለሰብ ከሀዲያ ህዝብ ጋር አብሮ የሚኖር ነገር ግን በዘር ሀረግ ሀዲያ ያልሆነን ሰው ከገደለ ከሀዲያ ሴራ መዋቅሮች ውስጥ *ነፈራ* ከፍተኛ ሚና ይጫወታል፡፡ *ነፈራ* ከዚህም በተጨማሪ በሀዲያ ውስጥ የሚኖሩ በዘር ሀረግ ግን ሀዲያ ባልሆኑ ሁለት ቡድኖች መካከል በሚከሰተው የሞት አደጋ ጉዳይ በከፍተኛ ሁኔታ ይሳተፋል፡፡

በሀዲያ ሴራ መሰረት በሞት ጉዳይ አፈታት ላይ ለመነጋገር አስቸጋሪ የሚሆነው ገዳዩን ማወቅ ባይቻል ነው፡፡ የዚህ ዓይነት ሁኔታ ሲከሰት በተለያዩ ደረጃዎች ያሉ የሀዲያ ሽማግሌዎች ጉዳዩን የመመርመርና ገዳዩን የማጣራት ስራ ይሰራሉ፡፡ ለዚህ ተግባራቸው የመጀመሪያ የሚሆነው ገዳዩን በምን ዓይነት ሁኔታ ማጣራትና መመርመር እንደሚቻል ስፊ ውይይት ማካሄድ ነው፡፡

ማጣራቱና የወንጀለኛው ፍለጋ የሚጀምረው የግድያ ወንጀሉ የተፈጸመበት አካባቢ ነዋሪዎችን በአጠቃላይ ሰብስቦ





በማወያየት ነው፡፡ የዚህ ዓይነቱ የነዋሪዎች ስብሰባ በተለምዶ የሚካሄደው በጧት ከብት ከመሰማራቱ በፊት ነው፡፡ ስብሰባዉን /ውይይቱን/ ከጠሩት ሽማግሌዎች መካከል (ገዳዩን ከሚያጣሩት) የትልቁ መዋቅር መሪ የሆነው ግለሰብ ወይም እሱ የሚወክለው ሌላ ሽማግሌ ህዝብ የተጠራበት ጉዳይ ከመጀመሩ በፊት ጸሎትና ምርቃት በማድረግ ጉዳዩ እንዲጀመር ያደርጋል፡፡

ጉዳዩ ከሚብራራበትና ህዝቡ ወንጀለኛውን እንዲያጋልጥ ወይም ወንጀለኛው እራሱን /እራሷን/ እንዲያጋልጥ ወይም እንድታጋልጥ በሚደረገው ውይይት ማሃል ሽማግሌዎች ነገሩ እንዲገለጥና እውነት እንዲወጣ ጸሎት (*ፋቴኤ* /Faate'e/) ያደርጋሉ፡፡ በዚህ ዓይነቱ ወንጀለኛን የማፈላለግ ሂደት እያንዳንዱ የአካባቢው ነዋሪ ንቁ ተሳትፎ እንዲያሳይና ስለወንጀሉና ስለአፈጻጸሙ በቂ ግንዛቤ እንዲጨብጥ ይደረጋል፡፡

ለዚህም ይረዳ ዘንድ ሽማግሌዎች ወንጀሉ የተፈጸመበትን አካባቢ በመጐብኘት የተገኘውን ሁሉ መረጃ ይሰበስባሉ፡፡ ከራሱ ከሟች አስከሬንም ላይ እንዲሁም ከሟች ቤተሰቦችና የቅርብ ጓደኞች ስለሟች ውሎ፣ ግንኙነትና ተሳትፎ ተገቢውን ሁሉ መረጃ ይሰበስባሉ፡፡ በመጀመሪያ ስብሰባ ፍንጭ የማይገኝ ከሆነ ተደጋጋሚ ስብሰባዎችን በመጥራት መረጃ ሊኖራቸው ይችላል ተብለው በሚጠረጠሩ ግለሰቦች አካባቢ ህዝብ ላይ ከፍተኛ የስነ ልቦና ጫና በማሳደር እውነቱን ለማውጣጣት የተቻለዉ ሁሉ ጥረት ይደረጋል፡፡

በዚህ ረገድ የአካባቢው *ዳኑዋ* እና *ሎመና* ህዝቡ እውነት ከደበቀ ዘራቸው እንደሚጠፋና የቅድመ አያቶች መንፈስ

በንጹህ ግለሰብ ደም ምክንያት እንደሚቆጣ በማስገንዘብ ህዝቡ ከፍተኛ የትውልድ ሃላፊነት እንዲሰማው ጥረት ያደርጋሉ፡፡ የዚህን ዓይነት ምክርና የሽማግሌዎች ተግሳጽ ሰምቶ ወንጀለኛው የማይጋለጥ ከሆነ ከዳኞችና ሽማግሌዎች እጅግ የሚፈራውና የሚከበረው በታላቅ ቁጣ በመነሳት አጠቃላይ የአካቢውን ነዋሪዎች የሚያጠቃልል የእርግማን ንግግር በማድረግ ህዝቡም እርግማኑን መልሶ እንዲለው ይጠይቃል፡፡ ከሚባሉት እርግማኖች ጥቂቶቹ የሚከተሉት ናቸው፡፡

ኩ ሳም እ ቀቾኔ እ ሹሞኦኔ ኣፎና

Ku saam I qachchonnee I shumo'onnee afonaa

ይህ አጋጣሚ በልጆቼና በዘሮቼ ይድረስ

ሞኣ ማጣሞሃሬ እ እል ብኤ

Moo'aa Maaxaamoohaare I illi bi'e

አይቼ ደብቄ ከሆነ አይኔ ይጥፋ

ማጬሳ ደጳኣሞሃሬ እ ማጭ ገዌ

Macceesa Daphphaammoohaare I macci gawwe

ሰምቼ ሸሽጌ ከሆነ የእኔ ጆሮ ይደንቁር

ጉዳዩ ይህን ደረጃ ሲደርስ የአካባቢው ነዋሪዎች የስነ ልቦና ጫናውንና ስጋቱን ፈጽሞ መቋቋም ስለሚያቅታቸው የሚያውቁትን ማንኛውንም ነገር ይናዘዛሉ፡፡ በህዝቡ መሃልም ገዳዩ ካለ በግልጽ በህዝቡ ፊት ወይም በሚስጥር ለሽማግሌዎች ብቻ በመንገር ራሱን ያጋልጣል፡፡





እርግማኑ ተፈርቶ በመጨረሻም ቢሆን ገዳዩ ራሱ ወይም ራሷ ወይም ማንኛውም ፍንጭ የሚጋለጠው በሀዲያ ሴራ እና በህዝቡ እምነት እርግማን የሚያስከትለው ጣጣ ለትውልድ የሚተላለፍ ነው ተብሎ ስለሚታመን ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በሀዲያ ሴራ እውነት በማጋለጥ ምክንያት ምንም ዓይነት ተከታይ ጫና እንዳይኖር ህብረተሰቡ ራሱ የሚከላከል ሲሆን ያየውን የሰማውን አደገኛ ወንጀል የሚያጋልጥ ግለሰብ እንደ ጀግናም ይቆጠራል፡፡

ከላይ የተጠቀሱት አጠቃላይ ጥረቶች ተደርገው እንኳን ተጠርጣሪዉን ለመለየት ካልተቻለ የሀዲያ ሴራ የጠለቃ / Xallaqqa/ ጊዜ ይሰጣል፡፡ ጠለቃ በአንዴ እስከ ስድስት ወር ሊዘልቅ የሚችል ጊዜ ሲሆን በምርመራና በስብሰባ ወቅት ሽማግሌዎች የሰጡት እርግማን ተጨባጭ ሥራ በመሥራት ምልክት ያሳያል ተብሎ በሀዲያ ሴራ የሚጠበቅበት ወቅት ነው፡፡ በዚህ ወቅት ግድያ ፈጽመው በደበቁ ግለሰቦች ወይም ግድያው ሲፈጸም አይተው ወይም እንዴትና ማን እንደፈጸመው ሰምተው በሸሸጉ ሰዎች ህይወት፣ ንብረትና ጤና ላይ ድንገተኛ፣ አደገኛና ያልተጠበቀ ችግር ይደርሳል ተብሎ ይታመናል[56]፡፡

ከዚህ በተጨማሪ በዚሁ በጠለቃ ወቅትም ጉዳዩን ለሽማግሌዎች በመንገር ማጋለጥ እንዲቻል ማንኛውም ከጉዳዩ ጋር ሊያያዙ የሚችሉ ምልክቶችና ማስረጃዎች በጥንቃቄ ክትትል ይደረግባቸዋል፡፡

[56] ይህ የሴራ ስርኣት በንጹሃን ሰዎች ላይ በአጋጣሚ በሚደርሰዉ አደጋ ግለሰቦቹ በወንጀለኝነት እንዳይጠረጠሩ አደጋዉ የደረሰባቸዉ ሰዎች ምልክቱን በማየት ራሳቸዉን ካላጋለጡ በወንጀለኝነት አይፈረጅም፡፡

በሀዲያ ሴራ በግጭት ምክንያት ሞት ሲከሰት ገዳይ ወዲያውኑ ከታወቀና በፍጹም ገዳዩን ማወቅ ካልተቻለ ጉዳዩ እንዴት እንደሚያዝ ከላይ ለማየት ሞክረናል።

ገዳይን በግልጽ ከማወቅና ፈጽሞ ከአለመለየት በተጨማሪ ሌላ ሊከሰት የሚችለው ሁኔታ የሟች ቤተሰቦች የሚጠረጥሩት የግድያ ፈጻሚ መኖር ነው። በሀዲያ ሴራ መሰረት የሟች ቤተሰቦች የግድያ ወንጀል መፈጸሙን የሚጠረጥሩት ግለሰብ ወይም ቡድን ካለ ጉዳዩን ለሚመለከተው የሴራ መዋቅር በማቅረብ እንዲታይላቸው የመጠየቅ መብት አላቸው።

በዚህ ወቅት ተጠርጣሪዎች እንዲጠሩ ተደርገው በግድያ መጠርጠራቸው ይነገራቸዋል። የሟች ቤተሰቦችም ለጥርጣሬያቸው ማረጋገጫ የሚሆኑ የሰውና ሌሎችም አይነት ማስረጃዎች (ነቃሻ /Naqaasha/) ለመዋቅሩ ሽማግሌዎች በማቅረብ ጉዳያቸውን ያስረዳሉ። ሽማግሌዎቹም የቀረበላቸውን ማንኛውንም ዓይነት ማስረጃ በታላቅ ጥንቃቄ በመመርመርና በመተንተን ስህተት ያለበት ፍርድ እንዳያስተላልፉ ከፍተኛ ጥንቃቄ ያደርጋሉ። የሚደረገውን ከፍተኛ ጥንቃቄ ለማገዝ ተበዳይና የተበዳይ ምስክሮች (ነቃሻዎች/Naqaasha/) እንዲሁም ተጠርጣሪ ማንኛውም የሚሰጡት ቃልና ሀሳብ እውነት ብቻ እንደሆነ በመሃላ ያረጋግጣሉ።

የተገባውን መሃላ እና የቀረበውን ማስረጃና ምስክር በጥንቃቄ በመመርመር ሂደት ላይ ሁለቱም ቡድኖች በጉዳዩ ላይ ደግመው ደጋግመው እንዲያስቡና በተቻለ መጠን ከሽማግሌዎች የመጨረሻ ውሳኔ በፊት እውነቱን እንዲያወጡ ይመከራሉ።





በሂደቱ መጨረሻ የሴራ መዋቅሩ ሽማግሌዎች ገዳይ ወንጀሉን መፈጸሙን ከረጋገጡና ይህንንም ውሳኔያቸውን ካስታወቁ በኋላ ተጠርጣሪው ውሳኔውን ካልተቀበለ ገዳይ ወንጀሉን አለመፈጸሙንና ከደሙ ንጹህ መሆኑን ለማረጋገጥ ጥቁር መውጋት (*የሄማቻቀሰማ* /Heemachcha qasimma/) የሚባል የሀዲያ ሴራ የመሃላ ስነ ስርአት ይከናወናል። ለሄመቻ ቀስማ ስነ-ስርአትም ጥቁር ውሻ ወይም ጥቁር በግ ይቀርባል። ስነ ስርአቱን ለመፈጸም ሟችና የተጠርጣሪ የቅርብ ቤተሰቦች ከእያንዳንዳቸው ሰባት ሰዎችን ይዘው ሽማግሌዎች ወደ ቀጠሩት ቦታ እንዲመጡ ይደረጋል።

ከዚያም በተጠርጣሪ ቤተሰቦች የቀረበውን ጥቁር በግ ወይም ውሻ በጦር ወግተው በመግደልና የመጨረሻውን መሃላ በመፈጸም ንጽህናቸውን ያረጋግጣሉ። ይህ ስነ ስርአት እንደሚያመለክተው የነፍስ ማጥፋትን የመሳሰሉት ወንጀሎች በሀዲያ ሴራ መሰረት የአጠቃላይ ህዝብ እና በተለይም የቅርብ ቤተሰብ የጋራ ሃላፊነት መሆናቸውን ነው። በተለይም ገዳይ የፈጸመውን ወንጀል ለጥንቃቄ እንኳን ሲል ከቅርብ ቤተሰቦቹ ለአንዱ ወይም ለማንኛውም ሰው ሲናገር ይችላል ተብሎ ስለሚገመት ይህንን የሄመቻ ቀስማ መሃላ አጠቃላይ ቤተሰቡ ፈጽሞ ቤተሰቡ እንዳይጠፋ በማሰብ በጉዳይ ላይ እውቀት ያለው ግለሰብ ጉዳዩን የማጋለጥ አጋጣሚንም ይፈጥራል።

ከላይ የተጠቀሱትን አጠቃላይ ሂደቶች አልፎ፣ ከማሃላው ጋር ተያይዘው ይከሰታሉ ተብለው የሚጠበቁትን አደገኛ ጉዳቶች በጥንቃቄ እንዲረዳ ከተደረገ በኋላ ተጠርጣሪውና ሰባቱ የቅርብ ቤተሰብ ተወካዮች የሄመቻ ቀስማን ስነ ስርአት ከፈጸሙ ከግድያው ወንጀል ጥርጣሬ ነጻ መሆናቸውን

ያረጋግጣሉ። በስነ ስርአቱ መጨረሻ በሄመቻ ቀስማ ወቅት ተወግቶ የተገደለው ጥቁር በግ ወይም ውሻ እና እንስሳው የተገደለበት ጦር ተቃጥሰው እንዲወገዱ ይደረጋል።

ከዚህ ስነ ስርአት በኋላም ገዳዩ ስላልተሰየና የእርቅ ስነ ስርአት ስላልተፈጸመ የጠሰቃ ጊዜ በሽማግሌዎች ለስድስት ወር ይታወጃል። በዚህም ጊዜ ማንኛውም በማህበረሰቡ ውስጥ አደገኛ፣ አስደንጋጭና ድንገተኛ የሆኑ ከባድ የንብረትና የአካል ጉዳቶች ከትትል ይደረግባቸዋል። ከዚህ ውጭ በማንኛውም መንገድ እውነተኛ የወንጀሉ ፈጻሚ እንዲጋለጥ ጥረቱ ይቀጥሰል።

### 3.4.7. የጢግ-ጉላ ስነ ስርአት

የጢግ ጉላ /Xiiguulla/ ስነ ስርአት የሚፈጸመው በግጭት ወቅት የህይወት መጥፋት (ሞት) ተከስቶ ገዳይ ከታወቀ ከኋላ ሁለቱ ወገኖች ለእርቅ ዝግጁ ሲሆኑ ነው። ስለዚህም ጢግ ጉላ የጥል፣ የበቀልና የጸጸት ስሜትን በማንጻት ወደ ሰላማዊና ጤናማ ግንኙነት የመመለስ ስነ ስርአት ነው። በተለይም ገዳይ የወገኑን ደም በማፍሰሉ ከፍተኛ ሃጢአት እንደሰራ ስለሚቆጠር ይህ የተወገዘ ተግባር በሀዲያ ሴራ ሊነጻ የሚችለው በጢግ ጉላ ነው ተብሎ ይታመናል። በመሆኑም የጢግ ጉላ ስነ ስርአት ለሟች ቤተሰቦችና ለገዳይ እና ቤተሰቦቹ የስነ ልቦና ፈውስን ይሰጣል።

ይህ የመጨረሻው የእርቅ ስነ ስርአት እንዲፈጸም በሁለቱ ተጋጭ ወገኖች መካከል የነበረው አጠቃላይ ግንኙነት ተጠንቶ ያሰፉና የተደበቀ ማንኛውም ወንጀል ካለ መፈታት ይገባቅበታል። የሀዲያ ሴራ ሞትን የመሰለ ከባድ አደጋ በግጭት ወቅት ሲደርስ ለደረሰው ከባድ አደጋ ያጋለጠ





የተደበቀና ያልተፈታ ሌላ ወንጀል በሟችም ሆነ በገዳይ ወገኖች በኩል ይኖራል ተብሎ ስለሚገመት የዚህ ዓይነት ሁኔታ መኖሩን ሁለቱም ወገኖች እንዲያጣሩ ያስገድዳል።

የዚህ ዓይነቱ የሀዲያ ሴራ ልምምድ በግልጽ የተከሰተ ከፍተኛ አደጋን በርካታ የተደበቁ ችግሮች እንዲጋለጡ እንደ ምክንያት የመጠቀምን መርህ በግለጽ ያሳያል። እንግዲህ በወቅቱ የተከሰተውን የሞት አደጋ እንደሰበብ በመጠቀም ያለፈና የተደበቀን የወንጀል ጉዳይ በማጣራትና በተገቢው መንገድ በመፍታት ለአዲሱ ስምምነትና እርቅ ተገቢውን መንገድ ለመክፈት የሚችና የገዳይ ቤተሰቦች ወደ *ሀራጋኖ* /Hiraagaano/[57] እንዲሄዱ ይደረጋሉ።

*የሀራጋኖ* ትእዛዝ ከተፈጸመና በወቅቱ በተከሰተው የሞት አደጋ የነበረውን አጠቃላይ ነበራዊ ሁኔታ እና እውነቱ ከታወቀ በኋላ ሁለቱም በግጭቱ የተሳተፉ ወገኖች በፍጹም ልብ ለእርቅ ዝግጁ ሲሆኑ ወደ ጢግ-ጉላ ስነ ስርአት ማምራት ይቻላል።

በሀዲያ ሴራ መሰረት የጢግ ጉላ ስነ ስርአት የሚፈጸመው በአካባቢው ባለ ወንዝ ዳር ነው። ምናልባትም ወንዝ የሚገኝበት ቦታ ከአካባቢው ነዋሪዎች መኖሪያ ሰፈር ርቀት ካለው በሠፈሩ አቅራቢያ በሚገኝ የተገሰሰና አስፈሪ ሥፍራ (ጫካ ወይንም ቁጥቋጦ ዉስጥ) ሥነ ሥርዓቱ ሊፈጸም

[57] በሀዲያ ሴራ መሰረት ወደ *ሀራጋኖ* /Hiraagaano/ የገዳይና የሟች ወገኖች እንዲሁም የሴራ ሽማግሌዎች በተመሳሳይ ሰዓት በተለያየ መንገድ ይሄዳሉ። ከመሄዳቸዉ በፊት የምሽንሽ ገፅማ /Mishiinsh ga'mma/ ወይንም በዱላ ጫፍ ላይ የሚታሰረዉን ብረት በመንከስ *ሀራጋንቾ* /Hiraagaancho/ ከሚሰጠዉ መፍትሄ ላለመዉጣት መሃላ ይፈፅማሉ (እሰፋ ቡንጤ እና ታገሰ ኤረንጎ ከጻፉት ማስታዎሻ)።

ይችላል፡፡ የወንዝ ዳርቻ ወይንም ሌላ የተገለለና አስፈሪ ሥፍራ ለሥነ ሥርዓቱ መፈጸሚያ የሚመረጠው በግጭት ምክንያት በሁለቱ ወገኖች ላይ የገባውን የጸጸት፣ የበቀልና የጥላቻ መንፈስ ለማባረር ነው፡፡

ለጢግ ጉላ ስነ ስርአት ማስፈጸሚያ የሚያስፈልገው አጠቃላይ ወጪ የሚሸፈነው በገዳይ ወገኖች ይሆናል፡፡ በዚህ መሰረት የገዳይ ወገኖች ለሟቹ ለቅሶና ቀብር ማስፈጸሚያ የወጣውን ወጪ ከመተካት ጀምሮ ለእለቱ የጢግ ጉላ ስነ ስርአት የሚያስፈልጉ ጥቁር (ሄመቻ /Heemachcha/) እና ቡላ (አጃራ /Ajaara/) በጐችን፣ቡልኮ (ዌያካ /Weyyakka/) ፣ ማር (መረቦ /Marabo/) እና ሌሎችም በእርቁ ፍጻሜ ለማዘጋጀው ድግስ የሚያስፈልግ አጠቃላይ ወጪ ማዘጋጀትና ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል፡፡

ስነ ስርአቱንም ለመፈጸም ጉዳዩን የያዘው የሴራ /Seera/ መዋቅር ዳኞች *(ዳኑዋ/Dannuwwa/)* ፣ የአካባቢው ተዋቂ ሽማግሌዎች፣ ገዳይና የሟች የቅርብ ምትክ፣ የገዳይና የሟች የቅርብ ቤተሰቦች በንጋት ወደ ጢግ ጉላ ስነ ስርአት መፈጸሚያ ቦታ ይሄዳሉ፡፡ በዚህ ጊዜ ገዳይ ከሟች የቅርብ ቤተሰቦች ጋር ፊት ለፊት በሚገናኝበት ሰዓት ድንገት በስሜታዊነት ወደ እርቅ የሚደረገውን ጉዞ የሚያደናቅፍ አንዳች ነገር እንዳይፈጠር የሟች ቤተሰቦች በታዋቂ ሽማግሌዎች ምክር ይሰጣቸዋል፡፡ ገዳይ ወደ ጢግ ጉላ ሲመጣ እጅግ መጸጸቱን ለመግለጽ ጸጉሩን ተላጭቶና ጭንቅላቱንና ፊቱን በጥቁር ልብስ ተሸፍኖ መሆን ይጠበቅበታል፡፡





የጢግ ጉላ ስነ ስርአት ሲጀመር የሟች ቤተሰቦች ገዳይ ያመጣውን ዌየካ /Weyyakka/ እንዲለብሱ ከተደረገ በኋላ ገዳይ ያቀረበውን ጥቁር በግ አርዶ ሆድ እቃውን በመተርተር፣ ትንሹን አንጀት አውጥቶ እንዲያስቀር ተደርጐ የተቀረው የበግ አካል ወደ ወንዙ ወይም ወደ ጫካው ይጣላል፡፡ ከዚያም የታረደው የጥቁር በግ ትንሹ አንጀት አንደኛዉ ጫፍ በገዳይ ሌላኛው ጫፍ ደግሞ የሟች ወራሽ ወይም ምትክ ተብሎ በሚታሰበው ሰው እግር ላይ ይታሰራል፡፡

ይህ በሁለቱ ጫፍ በሁለቱም ሰዎች እግር ላይ የታሰረው ትንሹ አንጀት መሃሉ ላይ በፉጋ /Fuga/ እንዲቆረጥ ይደረጋል፡፡ በዚህ ተግባር በሁለቱ ወገኖች መካከል የተዛመተዉ የበቀልና የጥል መንፈስ እንደተቆረጠ ይቆጠራል፡፡ የአንጀት መቁረጥ ስነ ስርአት ከተደረገ በኋላ ገዳይ በአጠገቡ ባለው ወንዝ ገላውን እንዲታጠብ በማድረግ ወንጀሉን ከፈጸመ ቀን ጀምሮ በሀዲያ ህዝብ ዘንድ እንደ ሀጢያተኛ ተደርጐ ይቆጠር የነበረበት ዘመን ወይም ወቅት አብቅቶ ወደ ምህረትና ንጽህና ዘመን ይሸጋገራል፡፡

እነዚህ ከላይ የተጠቀሱት ስነ ስርአቶች እየተፈጸሙ እያሉ ወደ ጢግ ጉላ ስነ ስርአት የታደሙት ሴቶች ወደ ስፍራው ተይዞ የተሄደውን ጥቁር ማር በውሃ በመበጥበጥ ውህዱን ወይም በረከቱን (*አንጬታን* /Anceetaa/) በገዳይና በሟች ወራሽ ወይም ምትክ ይረጫሉ፡፡ በወንዝ ዳር የሚፈጸመው የጢግ ጉላ ስነ-ስርአት የሚጠናቀቀው የጉዳዩ አስፈጻሚ የሆነው የሴራ መዋቅር መሪዎችና የአካባቢው ሽማግሌዎች የታረደውን በግ ደም በውሃ በመበረዝ እየረጩ ለሰላም፣ ለእርቅና ለስሪየት በሚያደርሱት ጸሎትና እሱን ተከትሎ በገዳይና በሟች ቤተሰቦች መካከል በሚደረግ የሰላምታ

ልውውጥ ይሆናል። የሰላምታ ልውውጡና መሳሳሙ የጥልና የበቀል ዘመን አብቅቶ ሰላማዊ ግንኙነት ለመጀመር ዝግጁነት እንዳለ ያረጋግጣሉ።

ከመንደር ወጣ ባለ ወንዝ ዳር ወይም ሌላ ቦታ ሲደረግ የነበረው ስነ ስርአት ከተጠናቀቀ በኋላ፣ ቀጣይ የጢግ ጉላ ስነ ስርአትን ለመፈጸም በስፍራው የነበሩት ሁሉም ተሳታፊዎች ጉዟቸውን ወደ ሟች ቤተሰቦች መኖሪያ ቤት ያደርጋሉ። ወደ ሟች መኖሪያ ቤት ደጃፍ ሲደርሱ በቤቱ በራፍ ላይ ገዳይ ሰወንጀሉ መፈጸሚያ የተጠቀመበት መሳሪያ ለምሳሌ፣ ጦር እንዲጋደም ተደርጐ መሣሪያውን ገዳይ ዘሎ በማለፍ ወደ ቤት እንዲገባ ይደረጋል። ይህንንም በማድረግ ደግም ተመሳሳይ ወንጀል እንደማይፈጽም ያረጋግጣል።

ወደ ሟች ቤተሰብ መኖሪያ ቤት ከተደረሰ በኋላ ሁሉም ሰው ከራሳቸው ጸጉር ጀምረው ተከናንበው ጨለማ ወደ ሆነው ቤት ውስጥ ይገባሉ። እርቁ የሚፈጸምበት ቤት ጨለማ እንዲሆን በርና መስኮት ይዘጋል። ማንኛውም ብርሃን የሚሰጥ ነገር እንዲጠፋ ይደረጋል። ወደ ቤቱ የሚገቡ ሰዎችንም ማንም የሚያስተናግዳቸውና መቀመጫ የሚሰጣቸው አይኖርም። ይህ ታላቅ ጨለማ ከሞት አደጋ መከሰት ጀምሮ በሁሉቱም ወገኖች መካከል የቆየውን ከበድ መለያየትና የጥላቻ ስሜትን ያንጸባርቃል። ጨለማው የወንጀሉን አስከፊነት ጭምር ያንጸባርቃል።

በዚህ እጅግ ከባድ ጨለማና የጸጥታ ሁኔታ እርቁን የሚመሩት ዳኖዎች ለሁሉም ተሳታፊ በሚሰማ ድምጽ የሚከተለውን ቅደም ተከተል ያለውን ጥያቄና መልስ





በመለዋወጥ[58] የእርቁን ስነ ስርአት ያስፈጽማሉ።

ዋእ ጫክ ፎቆዮኔ
Wai caakki fooqooyyonne?
የእግዝአብሄር ብርሃን አያበራም ወይ?

ፎቆኮ
Fooqookko
ይበራል

በዚህ ጊዜ፣ ቤት ውስጥ መብራት ወድያውኑ ይበራል። የገዳይ ወገኖችም እንደተከናነቡ መቀመጫ ፈልገው ይቀመጣሉ። ከዚህ ቀጥሎ፡-

ጉንጉእል ድሎዮኔ
Gunguu'll dilloyyonniihee?
ክንብንቡ አይወርድም ወይ?

ድሎኮ
Dillookko
ይወርዳል

በዚህ ጊዜ የገዳይ ወገኖች የተሸፋፈኑትን ክንብንብ አውርደው ተገልጠው ይቀመጣሉ። በገዳይና በሟች ቤተሰቦች መካከልም ባዶ ቦታ ይተዋል። ከዚህ በመቀጠል የሚከተሰዉ ጥያቄ ይጠየቃል።

[58] ይህንን ቅደም ተከተል ያለውን ጥያቄና መልስ የሚለዋወጡት ጉዳዩን ሲመለከቱ የነበሩ ሽማግሌዎች ራሳቸዉ ናቸዉ።

ዋእ ዎግ ቤዶዮኔ

Wa'i wog beedooyyonne?

የእግዝአብሔር ስርአት አይፈጸምም ወይ?

ቤዶና

Beeddonna

ይፈጸም

በዚህ ጊዜ ገዳይ ቡላ በግ እንዲያቀርብ ይታዘዛል፡፡ በጉንም በማረድ በሁሉም ተሳታፊዎች ላይ ደም ይረጫል፡፡ የበጉም ትንሹን አንጀት በማውጣት አንዱን ጫፍ በገዳይ ሌላኛዉን ጫፍ ደግሞ በሟች ወራሽ ወይም ምትክ እግር ላይ በማሰር በዚህ ዙር ሽማግሌዎች መሀል ላይ አንጀቱን በመቁረጥ የእርቅ መንፈስ እንደሰፈነ ያረጋግጣሉ፡፡

ቀጥሎም ገዳይ ከተቀመጠበት በመነሳት በቤቱ መሃል በሁለቱ ወገኖች መካከል በተተዋው ባዶ ቦታ ላይ ያመጣውን ስጦታ ይዞ ይቆማል፡፡ በሽማግሌዎች ትእዛዝም ያመጣውን ስጦታ የሟችን አባት ጉልበት እና የሟችን እናት ጡት በመሳም ይሰጣቸዋል፡፡ ከዚህም በመቀጠል ሽማግሌዎቹ ሁሉም ሰው ተነስቶ ተቃቅፎ ከልብ እንዲሳሳም በማድረግ እርቁን ይፈጽማሉ፡፡ በእርቁና በመሳሳሙ መሃልም ሴቶች ያዘጋጁት አንጩታ /Anceeta/ በሁሉም ተሳታፊዎች ላይ በሽማግሌዎች አማካይነት ይረጫል፡፡ በመጨረሻም ለእርቁ ስነ-ስርአት ታዳሚዎች ለአንድ ቀን ሙሉ የሚዘልቅ የድግስ ስነ ስርአት ይኖራል፡፡

ገዳይ ከጢግ ጉላ ስነስርአት በኋላ የሟች ቤተሰብ አንድ አባልና የሟች ተተኪ ተብሎ ስለሚታሰብ ቀድሞ ሟች





ለቤተሰብ ይሰጥ የነበረውን አገልግሎት አሁን በፍቅርና በቤተሰብነት ስሜት ይሰጣል፡፡ አብሮ መኖር፣ አብሮ መብላት፣ አብሮ መስራት የመሳሰሉ የእውነተኛ እርቅና ሰላም መስፈንን የሚያረጋግጡ ግንኙነቶች በእጅጉ ይጠናከራሉ፡፡

በአጠቃላይ የጢግ ጉላ ስነ ስርአት ሶስት ዋና ዋና ደረጃዎችን ያቀፋ ስርአት ነው፡፡ እነርሱም፦

ሀ. ከሰፈር ወጣ ባለ ወንዝ ወይም የተገለለና አስፈሪ ጫካ ወይንም ቁጥቋጦ ዉስጥ የሚፈጸም ስነ-ስርአት፣

ለ. በሟች ቤት ውስጥ የሚፈጸም ስነ-ስርአትና

ሐ. እርቅና የሰላም መውረድን አስመልክቶ የሚዘጋጅና ለአንድ ሙሉ ቀን የሚዘልቅ የግብዣና የአብሮነት ጊዜ ናቸው፡፡

### *3.4.8. ሳዕማ* (የዝሙት ወንጀል)

በሀዲያ ሴራ እንደ ከባድ ወንጀልና ሀጢያት ተደርገው ከሚቆጠሩ ነገሮች አንዱ ዝሙት (*ሳዕማ* /Saa'imma/) መፈጸም ነው፡፡ በሀዲያ ብሄረሰብ የግብረ ስጋ ግንኙነት የሚፈጸው በሀዲያ ሴራ ወይም በሌሎችም ተገቢ ተቋማት እውቅና የተሰጠው ጋብቻ በፈጸሙ ወንድና ሴት መካከል ብቻ ነው፡፡ ከዚህ ስርአት ውጭ የሚፈጸም ማንኛውም የግብረ ስጋ ግንኙነት እጅግ የተወገዘ ነው፡፡

በመሆኑም በምንም አይነት አጋጣሚ ከጋብቻ ውጪ ድንገት የግብረ ስጋ ግንኙነት ተፈጽሞ ቢገኝ በሀዲያ ሴራ ጉዳዩ የሚታይበትና የተሰራው ሀጢያት የሚነጻበት ስርአት አለው፡፡ ነገር ግን ክስተቱ እጅግ አስደንጋጭና አሳፋሪ በመሆኑና

ሴራው ግልጽና የአካባቢውን ማህበረሰብ አሳታፊ በሆነ መንገድ ጉዳዩን ስለሚመለከተው የዝሙት ወንጀል ክስተት ድግግሞሽ እጅግ በጣም ዝቅተኛ ነው፡፡ ከጋብቻ በፊት የተፈጸመ የግብረ ስጋ ግኙኝነት ካለም የጋብቻ እለት መጋለጡና ከፍተኛ ችግር ማስከተሉ ስለማይቀር ወጣት ሴቶች ለክብረ ንጽህናቸው[59] ከፍተኛ ጥንቃቄ ያደርጋሉ፡፡

ምንም እንኳን ከጋብቻ ውጭ እና ከጋብቻ በፊት ግብረ ስጋ ግኙኝነት መፈጸም እጅግ የተወገዘ ተግባር ቢሆንም ችግሩን ለመከላከል ትልቁን ድረሻ የሚወስደው፣ በዚህ የሀዲያ ሴራ /Seera/ ስርአት ላይ ወጣቶች በቂና ተገቢ እውቀት እንዲኖራቸው የተፈጠሩ ስህተቶችንና የተወሰዱ እርምጃዎች እንደምሳሌ በመጠቀም በተለያዩ አጋጣሚዎች ወጣቱን ግንዛቤ ያስጨብጣል፡፡

በመሆኑም ግንዛቤ የማስጨበጥን ሀላፊነት በመውሰድ ወጣት ወንዶችና ሴቶች ማንኛውንም ከወጣቶች የሚጠበቀውን ተሳትፎ አብረው እንዲያከናውኑ ይፈቀድላቸዋል፡፡ በዚህ ረገድ የወጣቶች ጌጃ /Geja/ ትልቅ ምሳሌ ሊሆን ይችላል፡፡ የወጣቶች ጌጃ በአንድ የእድሜ ክልል ውስጥ ያሉ የአንድ አካባቢ ወጣቶች የጾታ ልዩነት ሳይኖር በህብረትና በደስታ ወላጆቻቸውን በማገዝ ሃላፊነት መውሰድን፣ አብሮ መስራትን፣ የሀዲያን ሴራ እና የመሳሰሉ ጉዳዮች የሚለማመዱበት የደቦ ስርአት ነው፡፡

[59] በህዲ.ዖ ባህል ክብረ ንጽህና ያለዉን ትልቅ ግምት ከሚያመለክቱት የሚጠቀሰዉ፣ *በፊንዳነኖ*/ Fandaanano/ እምነት በመንግስተ-ሰማያት ባል ከሚስቱ ጋር አብሮ ሊሆን የሚችለዉ ከነድንግልናዋ ያገባት ከሆነ ብቻ ነዉ የሚለዉ እስተሳሰብ ነዉ፡፡





በጌጃ ማህበር ውስጥ ወጣት ወንዶችና ሴቶች ጾታን መሰረት ያደረገ ልዩነትን በማያንጸባርቅ ሁኔታ በማንኛውም ስራ በደስታና በጥሩ ስሜት ይሳተፋሉ፡፡ ለምሳሌ፣ በማህበረሰቡ እንሰት መፋቅና ቆጮ ማዘጋጀት በዋናነት የሴት ስራ ነው ተብሎ የሚታሰብ ቢሆንም ወጣት ወንዶች ከወጣት ሴቶች ጋር በመሆን በእንሰት መፋቅ[60] ስራ እየተሳተፉ እናቶቻቸውን ያግዛሉ፡፡

በሀዲያ ማህበረሰብ ውስጥ የእርሻ ስራ በዋናነት የወንዶች ተግባር ነው ተብሎ የሚታሰብ ቢሆንም ወጣት ሴቶች ከእኩያ ወንዶች ጋር በመሰረቱት ጌጃ አማካይነት በሁሉም የእርሻ ስራዎች ላይ ይሳተፋሉ፡፡

በቤተሰብና በማህበረሰብ ደረጃ የሚጠበቅባቸውን ዕለታዊ ሃላፊነት ከተወጡ በኋላ ምርታማና የተለያዩ የግል ችሎታዎችንና ጥበቦችን ለማሳደግ በሚያስችል መልኩ ከአመሻሽ ጀምሮ አብረው እንዲዝናኑ ይፈቀድላቸዋል፡፡ ለምሳሌ፣ ወጣት ወንዶችና ሴቶች አብረው በሚዝናኑበት ጊዜ የዊጣ ኢቅማ /Wiixa iiqqimma/ ወይንም ምግራ ፌርማ/Migira feerimma/ ስራ ወይም ለቤት እቃ መስሪያ የሚውል ስንደዶ ለቀማን ከመዝናናቱ ጋር አንድ ላይ ያስኬዳሉ፡፡ የዝላይ ስፖርትና ሌሎችም ጨዋታዎችን፣ ባህላዊ ዘፈንንና ቃላዊ ግጥሞችን ወይም ሸርማን እና የሙዚቃ መሳሪያ አጨዋወትን የሚማሩት በዚህ በመዝናኛ ጊዜያቸው ነው፡፡

[60] የዚህ አይነቱ የጾታ ልዩነትን ታሳቢ ያላደረገ አብሮ የመስራት ባህል በዚህ ዘመን እየጠፋ ይገኛል፡፡

ወጣት ወንዶችና ሴቶች በሀዲያ ሴራ የተለያዩ አይነት ኀደኝነትቶችን ይመለርታሉ፡፡ ለምሳሌ፣ *ሳዎማ* /Saawwooma/ ለግርዛትና ለሰርግ ጊዜ የሚሆን ሚዜነትን ፣ *በለሌ ለንድቾ ወራድቾ* /Balale landichchoo woraaddichcho/ ወይም የከንፈር ወዳጅ ይጠቀሳሉ፡፡ በዚህ ሁሉ አብሮ የመስራት እና አብሮ የመዝናናት የግኑኝነት ሂደት ውስጥ ከጋብቻ በፊት የሚደረግ ግብረ ስጋ ግንኙነት የተከለከለ መሆኑን ለማሳየት በሀዲያ አፈታሪክ ተዋቂ ከሆኑትና ፍቃድንና ክልከላን ከሚያሳዩት አባባሎች[61] ውስጥ የሚከተለውን ለአብነት ማጥቀስ ይቻላል፡፡

ሱሪ ሀናኔ ሱለኔ ጊቾኔ

Surii hanaane sullane giichchane

ከእምብርት በላይ የሱሎና የጊቾ ነው

ሱሪ ወሮኔ ሰዕም አንቾኔ

Surii woroone sa'mmi annichchane

ከእምብርት በታች የእድለኛው ነው፡፡

ከላይ ከተመለከተው አባባል መረዳት እንደሚቻለው ከጋብቻ በፊት የወጣት ሴትን በጨዋታና በመዝናኛ ወቅት መንካት የሚፈቀደው የአካል ክፍል ከእምብርት በላይ ያለው ብቻ ሲሆን መንካት የሚፈቀድለትም በዝምድና ሀረግ ከሱሎ/Sullo/ ጀምሮ ወደ ሰይ የሚገኝ ወጣት ወንድ ብቻ ነው፡፡ ከእምብርት በታች ያለውን የአካል ክፍል ከጋብቻ በፊት በማንኛውም አጋጣሚ ማንም ወንድ እንዲነካ ያልተፈቀደለት ሲሆን በሴት ልጅ የህይወት ዘመን ይህ የአካል ክፍል እድለኛ ሆኖ የሚያገባት ወንድ ብቻ እንዲነካው ይፈቀዳል፡፡

[61] ይህንን የሀዲይሳ አባባል የነገሩን አቶ ገብረከዳን አንክሶ ናቸዉ፡፡





አንዲት ሴት ከባሏ ውጪ የግብረ ስጋ ግንኙነት ፈጽማ ብትገኝ የሀዲያ ሴራ በሁለቱም ወንድና ሴት ተሳታፊዎች ላይ ከፍተኛ ቅጣት ይጥልባቸዋል፡፡ ከጋብቻ ውጪ ግብረስጋ ግንኙነት የፈጸመው ወንድ የሀዲያን ሴራ በመጣሱና የሴትየዋን ባል በመበደሉ ለሴትየዋ ባልና ለሴራ አንድ ወይፈን፣ አንድ ብርድልብስና አንድ እንስራ ማር በማቅረብ ይቀጣል፡፡ በዚህ ተማሳሳይ ወንጀል የተሳተፈች ሚስት ሀጢአት ስለፈጸመች ቆሸሻለች ተብሎ ስለሚታሰብ በሀዲያ ሴራ *የሀርፈን አንሻ* /Hirfana Anshaa/[62] ስነስርአት ይከናወናል፡፡

ከጋብቻ ውጭ ግብረስጋ ግንኙነት ፈጽማ የተገኘች ሚስት በባሏ ዘንድ እንደ ነፍሰገዳይ ስለምትታይ በጭረሽ በፊቱ መውጣትና መታየት ስለሌለት ቤቷን ጥላ ወደ ቤተሰቦቿ ትሰደዳለች፡፡ ከዚያም ጉዳዩን የሚመለከት ተገቢው የሴራ መዋቅር ሽማግሌዎችን በመያዝ ባልን ካረጋጉ በኂላ ምናልባት ከሀርፈን አንሻ ስነስርአት በፊት ወደ ቤቷ ብትመለስ እንኳን ከባሏ ጋር አብራ መተኛት ስለማይፈቀድላት ብቻዋን ቁርበት አንጥፋ መሬት ላይ ትተኛለች፡፡

ሀርፈን አንሻ (በቀጥታ ትርጉሙ ቁርበት አጠባ) ሴቷ የባሏን መኝታ አቆሸሻለች ወይም አርክሳለች ተብሎ የሚፈጸም የማንጻት ስነስርአት ነው፡፡ ለስነስርአቱም ማስፈጸሚያ ሴቷ ከወላጅ ቤተሰቦቿ ዘንድ አንድ መልኩ የሚያምር ነጭ ኮርማ እና አንድ እንስራ ማር እንድታመጣ ይደረጋል፡፡ ስነ-ስርአቱም በሚፈጸምበት በሚፈጸምበት እለት ሴቷ በራሷ ቤት ድግስ

[62] ቁርበት አጠባ (ሀርፈን ኣንሻ) በሀዲያ ባህል ቁርበት ለመኝታ እንደ አንሶላ የሚያገለግል ከመሆኑ የተነሳ የተሰጠ ስያሜ ነዉ፡፡

እንድታዘጋጅ ይደረጋል:: ከዚያም ያመጣችው ኮርማ ታርዶ በባልና በሚስት ላይ ደሙ ይረጫል:: ሳዕማ /Saa'imma/ ወይም ዝሙት በፈጸመችውም ሚስት ጭንና ግንባሯ ላይ በተለየ ሁኔታ ደም ይቀባል::

ይህ የሚደረገው ጥፋተኝነቷዋ እንዲታይ በመሆኑ ደሙን እንደተቀባች ሳትታጠብ ታድራለች:: በመጨረሻም በኮርማ ደም ነጽታለች ተብሎ ስለሚታሰብ የሴራ ሽማግሌዎች መክረውና መርቀው የዚህ አይነት ነገር በማህበረሰቡ ውስጥ ድጋሚ እንዳይከሰት አስጠንቅቀው ባልና ሚስት ወደ ቀድሞ ኑሮአቸው እንዲመለሱ ያደርጋሉ::

### 3.4.9. የውሳኔ አፈጻጸም /Enforcement/ ዘዴዎች

በማንኛውም ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ ወይንም በባህላዊ ጉዳይ የሀዲያ ሴራ እና ጉዳዩን እየተመለከተ ያለው የሴራ መዋቅር መሰረታዊ መርህ እውነትን ማውጣትና ፍትህን ማስፈን ነው:: ከዚህም በተጨማሪ ማንኛውም ጉዳይ በሴራ መዋቅር በሚታይበት ጊዜ ባለጉዳይ ወይም የባለጉዳዩ ወገን የሆነ ዳና / Daanna/ በውሳኔ አሰጣጥ ስርአቱ በቀጥታ ስለሚሳተፍ ሂደቱ እጅግ አሳታፊ ነው::

በመሆኑም ማንኛውም የሴራ መዋቅር ውሳኔ በባለጉዳዮች ሙሉ ተሳትፎ ስምምነት የሚደረስ የሚሆንበት አጋጣሚ እጅግ ብዙ ነው:: ከዚህም የተነሳ የሀዲያ ሴራ ውሳኔ ለማስፈጸም ብዙ ችግር አይገጥመዉም:: በሀዲያ ባህል ከአንድ የጉዳዩ ባለቤቶች ውጭ አጠቃላይ የሀዲያ ህዝብ ለሴራና ለውሳኔዎቹ የሚሰጠው ክብርና ታማኝነት ስአፈጻጸም ከፍተኛ እገዛ የሚያደርግ ማህበራዊ ህይል ነው::





ነገር ግን በማንኛውም አጋጣሚ አንድ ሀዲያ የሆነ ግለሰብ ለሴራ ውሳኔ አልገዛም የሚል ከሆነ ዋነኛ የማስፈጸሚያ መሳሪያ ማህበራዊና ባህላዊ፣ የተለያየ መልክና ደረጃ ያላቸውን ጫናዎችንና ማእቀቦችን መጣል ነው:: እነዚህ ጫናዎችና ማእቀቦች የውሳኔ አካልም የሚሆኑበት አጋጣሚዎች ይኖራሉ:: የሴራን ውሳኔ ማስፈጸሚያ ከሆኑት ዘዴዎች ውስጥ በጣም የታወቁት የሚከተሉት ናቸው::

ሀ. *ዱንቻ* /Duuncha/:- ይህን ውሳኔ አልቀበልም ያለውን እንቢተኛ በባህላዊ ስርአት መርገም ነው:: ቀላል በሆኑ ጉዳዮች ግለሰቦች በእንብተኝነት የሚቀጥሉ ከሆነ የሀዲያን ሴራ የበላይነት ለማረጋገጥ ሽማግሌዎች *በዱንቻ* (Duuncha) እንቢተኛውን ወደ ስርአት እንዲመለስ ያስገድዳሉ:: ምክንያቱም በሀዲያ ባህል ዱንቻ በተረጋሚው ላይ ከፍተኛ የሆነ የአምላክ ቁጣን በመቀስቀስ ከፍተኛ ችግር የመፍጠር ችሎታ አለው ተብሎ ስለሚታሰብ ነው::

ለ. *ዳንቡሳ* /Danbuussa/:- በሀዲያ ሴራ ማንኛውም ሀዲያ ለፈጸመው ጥፋት ወይም ለቀረበበት ክስ ቀርቦ መልስ የመስጠት ግዴታ አለበት:: ይህንን ሁኔታ በመቃወም ለማንኛውም የሴራ መዋቅር መሪዎች /Daannuwwa/ ተደጋጋሚ ጥሪ ምላሽ ለመስጠት እብሪተኛ የሆነ ግለሰብ ቢኖር ዳንቡሳ የውሳኔ ማስፈጸሚያ ሆኖ ሲያገለግል ይችላል::

ዳንቡሳ የሴራ ሽማግሌዎች በርካታ የተከበሩ እንግዶችን በመያዝ ወደ እንቢተኛው ግለሰብ ቤት በድንገት የሚያደርጉት ጉብኝነትና እንቢተኛው ግለሰብ ለእንግዶቹ

የሚያደርገው ደረጃውን የጠበቀ ግብዣ ነው። እነዚህ በታላቅ ቁጣና *የዱንቻ* /Duuncha/ ወይም የእርግማን እቅድ የመጡ የሴራ ዳኞች እና የተከበሩ እንግዶች ተቀምጠውባቸዉ የመጡትን ፈረሶችና በቅሎዎች ልጓማቸውን ሳይፈቱ በማሰር በእንቢተኛው ግለሰብ ደጃፍ ከዋናው ቤት በር ፊታቸውን በተቃራኒው በማዞር ወንበር ሳይጠብቁ መሬት ላይ በመቀመጥ ለከባድ እርግማን ይዘጋጃሉ።

በዚህ ዝግጅት ወቅት ሽማግሌዎቹ ማንንም አያነጋግሩም ወይንም እርስ በርሳቸውም አይነጋገሩም። ማንኛውም ምግብ ወይም መጠጥ በቤቱ ባለቤት ቢቀርብላቸውም አይቀምሱም። በዚህ ሁኔታ ውስጥ የእርግማን እቅድ ሊቀየር የሚችለው የእንቢተኛው ግለሰብ *ምዕን ዳና* ቀርቦ እንቢተኛው ላደረሰው በደልና መጉላላት ይቅርታ በመጠየቅ ማንኛውንም የሽማግሌዎች ውሳኔ ለመቀበል ዝግጁ መሆኑን ሲያረጋግጥ ብቻ ነው። ከዚያም ተከስቶ የነበረው ችግር በሰላማዊ መንገድ የሚፈታበት ሁኔታ እንዲመቻች ሽማግሌዎቹ ይጠየቃሉ።

የእንቢተኛው ምኔ ግለሰቡ ለፈጠረው ችግርና መጉላላት ለሴራ ዳኞች እና ለተከበሩ እንግዶች ቅጣት እንዲሆን አንድ በሬ፣ አንድ እንስራ ማርና ቅቤ ያቀርባል። በሬው (ሞራ /Moora/) ይታረዳል። ስጋውም እዚያው በቀረበው ቅቤ ተሰርቶ ይበላል። ማሩንም በውሃ በመበጥበጥ *ድቃሳ* /Diqaasa/[63] ተዘጋጅቶ ይጠጣል። የቀረውም ቅቤ በሽማግሌዎች እናት (ሰሞ/Sammo/) ላይ ይቀባል። በዚህም የሽማግሌዎች ቁጣ እንዲበርድ ይደረጋል። ለፈረሶችናቅሎዎችም እህልና ሳር ይቀርብላቸዋል።

[63] ዲቃሳ በሀዲይሳ ጠጅም ሆነ ሌሎች ከማር የሚዘጋጁ መጠጦች መጠሪያ ነዉ።





አንድ ግለሰብ ለዳንቡሳ እንኳን እንቢተኛ ከሆነ እነዚያ ከላይ በተጠቀሰው ሁኔታ በግለሰቡ ግቢ ውስጥ የተቀመጡት ሽማግሌዎች በጣም የመረረ እርግማን በመፈጸም የግለሰቡን የግቢ በር በእሾክ በመዝጋት ወደ ቤታቸው ይመለሳሉ። ከዚያ ወደሚቀጥለው ከፍተኛ የሆነ የማስፈጸሚያ ዘዴ ሽማግሌዎች ይሸጋገራሉ።

ሐ. *ያይማ* /Yaayyimma/:- ይህ ከማንኛዉም ማህበራዊና ባህላዊ ተሳትፎና ግንኙነት የማግለልና ማእቀብ የመጣል ቅጣት ነው። በተለያዩ የውሳኔ ማስፈጸሚያ ስልቶች የሚደረጉ ሙከራዎች በአጠቃላይ ለሴራ እምቢተኛ የሆነውን ግለሰብ መመለስ ሲያቅታቸው በሀዲያ ሴራ የያይማ ቅጣት ይጣላል።

ቅጣቱ እጅግ ከባድ በመሆኑ እምቢተኛውንና ቤተሰብ ለበርካታ ችግሮች የሚደርግ በመሆኑ በህዝብ ውስጥ እየኖሩ የስነልቦና ለቀቀን በሚያስከትል ሁኔታ እንደመታሰር ይቆጠራል። ይህ ውሳኔ የተላለፈበት ግለሰብ ለእለት ከእለት ኑሮ አስፈላጊ የሆኑና ከሌሎች የአካባቢው ማህበረሰቦች ጋር በሚደረግ ግንኙነት ብቻ ውጤታማ ሊሆኑ በሚችሉ ጉዳዮች ላይ ግንኙነቱ ሙሉ በሙሉ እንዲቋረጥ ይደረጋል። ለምሳሌ፣ እሳት መጫርን መከልከል፣ ምግብና ውሃ አብሮ መጠቀምን ማስቆም፣ ከብቶችና ልጆች ከሌሎች የአካባቢው ነዋሪዎች ከብቶችና ልጆች እንዳይቀላቀሉና እንዳይጫወቱ ማገድ፣ ገበያ እንዳይገዙም እንዳይሸጡም መከልከል፣ በለቅሶና በሰርግ ስነስርአት እንዳይሳተፉ መከልከልና ለቅሶ ቢገጥማቸው አስከሬኑን ወስዶ ከመቅበር ውጪ ማንኛውንም ግንኙነት አለማድረግ እና የመሳሰሉ በጣም ከባድ ጉዳዮችን

ያጠቃልላል:: *ያይማ* የሚያስከትለውን ጉዳት በመመልከት በሀዲያ ህዝብ ዘንድ እንደሞት ቅጣት የሚቆጠርበት አጋጣሚ ይጠቀሳል::

*የያይማን* ቅጣት የሚያስፈጽሙት የታችኞቹ የሴራ መዋቅር እርከኖች ናቸው:: *ያይማ* ከፍተኛውን ጫናና ጉዳት የሚያደርሰው በሴቶች ላይ ነው:: ምክንያቱም የእለት ከእለት የቤተሰብ ህይወት ሴቶች እርስ በርሳቸው በሚያደርጓቸው ግንኙነቶች የተመሰረቱ በመሆናቸው ነው:: ባል በፈጠረው ስህተትና ግትርነት ለተወሰነው *ያይማ* አፈጻጸም ተጨማሪ ጫና በባል ላይ ለማሳደር ሚስት ቤቷንና ልጆቿን ጥላ ወደ ቤተሰቦቿ ልትሄድ ትችላለች::

*የያይማን* ማእቀብ ለማስነሳት ዋነኛው ቅድመ ሁኔታ እምቢተኛው ግለሰብ ለሴራ ውሳኔ እውቅና መስጠትና በሽማግሌዎች ላይ ለፈጠረው መጉላላት ቅጣት (*ጉዙሞኦ* /Guzummo'o/) ማቅረብ ነው:: ለዋናው ጉዳይ የተበየነው ውሳኔ እንደተጠበቀ ሆኖ በሀዲያ ሴራና በአስፈጻሚዎቹ ላይ ላሳየው ንቀት ትልቅ በሬ (*ሞራ* / Moora/) እና ማር በማቅረብ *ያይማ* እንዲነሳ መጠየቅ ይቻላል::

## 3.5. ሴቶችና የሀዲያ ሴራ

የሀዲያ ሴራ ለሴቶች የተለየ ክብር ያለው ሆኖ ለሴቶች ብቻ የሚሰሩ ከተለያዩ ማህበራዊና ባህላዊ ጉዳዮች ጋር የተያያዙ አሰራሮች አሉት:: ለሴቶች ብቻ የሚሰሩ አሰራሮች በጥቅሉ ሴት ልጅ በማህበረሰቡ ውስጥ ያላትን ስልጣንና ይህንን ስልጣን መቼና የት መጠቀም እንደምትችል በግልጽ ይደነግጋል::





ምንም እንኳን የሀዲያ ሴራ በተለያዩ መዋቅሮቹ /ምኔ፣ ነፊራ፣ ሞሎ፣ ሱሎ፣ ጊቾ እና ጊራ/ የስልጣን ቦታዎች ላይ ሴቶችን የማያሳትፍ ቢሆንም የሴቶች ውሳኔና ፍላጎት የማይጣስባቸው የራሳቸው የሆኑ አሠራሮች አሉት:: ከእነዚህ የሀዲያ ሴራ አሰራሮች ውስጥ ለንድ-ስኮ /Land sikko/፣ ለንድ-መቻ /Land machcha/ እና ሄፍቾ /Heeffichcho/ በዋናነት ይጠቀሳሉ::

ሀ. *ለንድስኮ* /Landisikko/:- ይህ ሴቶች ከጋብቻ ከኂላ የሚይዙትን ቀጭንና ለስለሳ /refined/ በትርን ያመለክታል:: በሀዲያ ህዝብ ዘንድ ይህ ለሴት ልጅ የሚሰጥ በትረ-ሥልጣንን ይወክላል:: ሴት ልጅ በማንኛውም የተፋፋመ ግጭት ወቅት ለንድ-ስኮ በተጋጭ ቡድኖች መካከል በማጋደም ከተማጸነች ማንም ግለሰብ በትሩን በመሻገር ለግጭት አይዳረግም:: በዚህ ሁኔታ ግጭትን በማብረድ ለድርድርና ውይይት ምቹ ሁኔታን በመፍጠር ሴቶች በለንድ-ስኮ ስልጣናቸው ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያበረክታሉ::

ለ. *ለንድ መቻ* /Land machcha/:- ይህ የሀዲያ ሴራ ለሴት ልጅ የሚሰጠው ሥልጣን ሆኖ ሴቶች በተወለዱበት ጎሣ ውስጥ ብቻ የሚጠቀሙት ነው:: በሀዲያ ባህል ለንዳ / Landa/ የሚለው ቃል በአንድ መልኩ ልጃገረዶችን ሲወክል በሌላ በኩል ግን ሴቶችንና በሴቶች በኩል የሚመጣውን የደም ዝምድና ትውልድን በአጠቃላይ ያመለክታል::

ለንድ መቻ ከዚህ አንጻር ሴት ልጅ ካገባችም በኂላ በስጋ ዘመዶቿዋ ላይ ያላትን መብትና ስልጣንን ያመለክታል::

ለምሳሌ፣ ሴት በስጋ ዘመዶቿ መካከል ማንኛውም ችግርና ግጭት ቢከሰት በሰንድ መቻ ስም (ለንድ መች መገኖ /Land machcha magano /) በማለት የወገቧን መቀነት በመፍታት ከለመነች ልመናው ወዲያውኑ ተቀባይነት በማግኘት ወደ መፍትሄ የማምራት እድል በጣም ከፍተኛ ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ሰንድመቻ ሴት ልጅ ከስጋ ዘመዶቿዋ በአቅማቸው ሊሰጧት የሚችሉትንና በወቅቱ ያስፈለጋትን ንብረት /እህል፣ እንስሳት፣ እንስት/ ወዘተ. የማግኘት መብትን ያጎናጽፋታል፡፡

በአጠቃላይ ሰንድመቻ የሀዲያ ሴራ ሴት ልጅ የቤተሰቦቿን ንብረት የመውረስ መብት ስለሚነፍጋት እንደማካካሻ የሚሰጣት ስልጣን ነው ተብሎ ስለሚታመን እጅግ ይከበራል፡፡

ሐ. *ሄፍቾ* /Heefiichcho/:- ሄፍቾ የሴቶችን መንፈሳዊ ስልጣን የሚወክል ሆኖ ጥቅም ላይ የሚውለው ሴት ልጅ አግብታ በምትኖርበት የባሏ ዘመዶች ዘንድ ነው፡፡ *ሄፍቾ* የአንድ አካባቢ ሴቶች በመሰባሰብ በግጭት ወቅት ሰባሎቻቸው ድልን የሚለምኑበት፣ በአካባቢያቸው ነውርና ያልተለመደ ነገር በሚከሰትበት ጊዜ ክስተቱን በማስመልከት የልመናና የማስወገድ ስነ ስርአት የሚፈጽሙበትና አደገኛ ድርቅ፣ ጐርፍ ወይም ሌላም የተፈጥሮ አደጋ ሲከሰት አምላክን የሚለምኑበት መንፈሳዊ ስልጣናቸው ነው፡፡ *የሄፍቾ* ስልጣንን በመጠቀም ሴቶች ከሚፈጽሟቸው ስነ ስርአቶች ዋነኛዉ የዱፋ መቋጠር (*ጉፍ ጉድማ* /Guffaguddimma/) ስነ ስርአት ሲሆን ይህ የሚከናወነዉ በጦርነት ወቅት የጠላት





እግሮች እንዲሰናከሉና እንዲወድቁ በመመኘት ነዉ፡፡

በአጠቃላይ የሀዲያን ህዝብ ባህላዊ የአስተዳደር መዋቅሮችና የግጭት አፈታት ስርአታቸውን[64] በመገምገም ጥላሁን አማኑኤል (2009: 68-69) እንዳመለከተዉና ነባራዊ እውነታም እንደሚያንጸባርቀው የሀዲያ ህዝብ ባህላዊ የአስተዳደር መዋቅሮችና የግጭት አፈታት ስርአት በጐሳ የተዋቀረ ሆኖ ከታች ወደ ላይ እየሰፋ በመሄድ አጠቃላይ የሀዲያን ህዝብ የሚያቅፍ ይሆናል፡፡ ነገር ግን በአንድ ኩታገጠም አካባቢ መኖርና በተለይም የግጭት አወጋገድን ብቻ ነጥለን ካየን መንፈሳዊ ስልጣንንም ታሳቢ ያደረጉ አሰራሮች በተወሰነ ደረጃ እንደሚንጸባረቁ መረዳት ይቻላል፡፡ በተለይ ተመሳሳይ መልክአ ምድራዊ አካባቢን ታሳቢ በማድረግ የተዋቀረው የነፈራ /Nafara/ መዋቅር ለዚህ ጥሩ ማሳያ ሊሆን ይችላል፡፡

[64] ይህንን በሚመለከት ስለ ሃድያ ሴራ ባህላዊ የአስተዳደር ተቋማትና ሚናቸዉ በሚለዉ ርዕስ ስር ያለዉን ይመለከቷል፡፡

# ክፍል 4፤ ሃይማኖት

## 4.1. *ፈንዳነና*፤ የሀዲያ ጥንታዊ ሃይማኖት

*የፈንዳነና*/Fandaanano/ ሃይማኖት በአሁኑ ጊዜ እየሞተ ያለ የሀዲያ ብሄረሰብ ሀገር-በቀል /indigenous/ ሃይማኖት ነው። የሃይማኖቱ ስያሜ *ፈንዳነና* ሲሆን ተከታዮቹ በብዙ ቁጥር *ፈንዳና* /Fanadaano/ በነጠላ ቁጥር ደግሞ *ፈንዳንቾ* / Fandaancho/ በመባል ይጠራሉ። ሀይሌ (1971) ይህንን በመጥፋት ላይ ያለውን ሃይማኖት እንደ ሀገር-በቀል ሃይማኖት ሰንዶ ወይም መዝግቦ ለማስቀረት ቀጥተኛ መረጃዎችን በመውሰድ ከሌሎች ጸሀፍት ይልቅ እጅጉን በተሻለ ሁኔታ ጽፎታል። ስለ ሃይማኖቱ መጥፋት እንደ ዋና ምክንያት የሚገለጸው በዋናነት የክርስቲና (የኦርቶዶክስ እና ፕሮቴስታንት) እና በተወሰነ ደረጃ የእስልምና ሃይማኖት ያሳደሩት ተጽዕኖ እንደሆነ ነው። እንደ ሃይሌ አገላለጽ በሀዲያ ካሉት ጐሳዎች *ፈንዳነና* ከከፍተኛ ስርጭት ወደ ዝቅተኛ ሲታይ በባደዋቾ፣ በሊብዶ፣ በሻሾጐ እና በሶሮ በቅደምተከተላቸው ተሰራጭቶ የነበረ ሃይማኖት ነው። በሌላ በኩል፣ ቀቤና እና ሌሞ ላይ የእስልምና ሃይማኖት በአንጻራዊነት ተስፋፍቶ ይገኝ እንደነበረ ተጠቁሟል። በአሁኑ ዘመን ሲታይ የእስልምና ሃይማኖት በአንጻራዊነት ከሌሎቹ የዞኑ ወረዳዎች ይልቅ በአንሌሞ፣ በሌሞ፣ በሻሾጐና ምስራቅ ባደዋቾ ተሰራጭቶ እንዳለ ማየት ይቻላል። ቀጥሎ በመጥፋት ላይ ባለ *የፈንዳነና* ሃይማኖት ውስጥ መነሳት ያለባቸው መሰረታዊ ስርአቶች እንደሚከተሰዉ ቀርበዋል።

የፈንዳነናን አጀማመር (Origin) በሚመለከት የተለያዩ አመለካከቶች ይሰነዘራሉ። አንዳንድ ምንጮች እቶ (Itto) እና አልበጆ (Allbajjo) የሚባሉ ሰዎች እንደወፍ እየበረሩ፣





ባህርን ተሻግረው የመጡ ሰዎች ናቸው ሃይማኖቱን ያስተዋወቁት በማለት ይገልፃሉ። በሌላ በኩል፣ ሌሎች ምንጮች ደግሞ *ቦያም* (የመካከለኛው ዘመን የሀዲያ ገራድ) ናቸው ለመጀመሪያ ጊዜ ወይም እንደገና ያስተዋወቁት በማለት ይገልፃሉ። የፕላዝኮዊስኪ (1957:85) ምልከታ በሀይሌ (1971፡5) እንደተጠቀሰው፣ ባደዋቾ ያሉ *ቦያም-መና* ወይም ደግሞ *ዶድች-መና* የተባሉት ጐሳዎች የፈንዳነናን ሃይማኖት አጥብቀው የሚከተሉ እንደነበር ተገልጸዋል፤ ይህም ሃይማኖት ለጐሳዎቹ የተለየ ፋይዳ እንዳላቸዉ ተጠቁሟል። እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ ከሀዲያ ዞን ውስጥ ጥቂት የፈንዳነና ተከታዮች ያሉበት አካባቢ ባደዋቾ እንደሆነም ታውቋል። ከፍ ሲል ቀረቡት መረጃዎች በመነሳት ስለሃይማኖቱ ጥንተ-አመጣጥ ወይም ጅማሬ ከመላምቶቹ በስተቀር ቁርጥ ያለ መነሻ መናገር አይቻልም።

## 4.2. *የፈንዳነና እምነት መሰረት*

የፈንዳነና ሃይማኖት ተከታዮች የእምነታቸው መሰረት *ዋዓ* / Waa'a/ /ሁሉን ቻይ፣ የሁሉ የበላይ የሆነ አምላክ፣ *ኢመዕን-ዋዓ* /Iima'n Waa'a/ (ከሰማያት በላይ ያለ አምላክ) ወይም *ሄመች ዋዓ*[65] /Heemachchi Waa'a/ ነው። የሃይማኖቱ ተከታዮች *ዋዓ* የሚሰውን ከመሬት በላይ የያዘውን ሰማያዊ ሰማይ እና ከሰው ልጆች እይታ ሩቅ የሆነው ስፍራ ወይም

[65] የሰማይ ቀለም በሀዲያዎች ሲጠራ ሄመቻ(ጥቁር) ተብሎ ነዉ፤ ምክንያቱም የሰማያዊ ቀለም እቻ ፍች ሀዲይሳ ስለሌለዉ ወደ ሰማያዊ የሚጠጋጋዉን ጥቁር ይተከዋል። ለዚህም ነዉ ሰማያዊ አምላክ ማለት ሲገባቸዉ *ሄመች ዋአ* ብለዉ የሚጠሩት። ሀዲያዎች ሲራገሙ፣ *ኩ ሄመች ዋዕ ፊረዶና* (ይህ ጥቁር አምላክ ይፍረድብህ)፤ *ሄመች ዋዕ ኬሴ ቀሴ* (ጥቁር አምላክ አንተን ይዉጋህ) ... እያሉ በሚናገሯቸዉ አባባሎች "ጥቁር አምላክ" የሚሰዉ *ኢመዕን-ዋዓ* /Iima'n Waa'a/ ከሚሰዉ ጋር እቻ ፍች አለዉ።

አድማስ እንደሆነ ያስባሉ። ጸሀይ (ኤሊንቾ /Eelliincho/) እና ጨረቃ ወይም አገና / Agana/ የዋዓ አይኖች እንደሆኑም ይታመናል። ዋዓ ሁሉን የሚያይ አምላክ ሆኖ በማንም የስጋ አይን አይታይም፤ ምክንያቱም የሰው አይነት ተጨባጭ ወይም የሚዳሰስ ቅርጽ የለውምና።

በፈንዳነኖ ዋዓ የሰማይ፣ የምድር እና የፍጥረታት ሁሉ ፈጣሪ እንደሆነ ስለሚታመን ቆጫንቾ /Qooccaancho/ ወይንም ፈጠሪ ተብሎ ይታወቃል። ዋዓ መልካም የሆኑ ነገሮችን ሁሉ የሰራ ወይም የፈጠረ ሲሆን ሰዎችን ከክፉት መናፍስት ወይንም ሼጣና /Sheexaana/ እና ሀቡሳ /Habusa/ ይጠብቃቸዋል። ከሰዎች ጋር በሚኖረው ግንኙነትም ተግባቦቱ የሚሰምረዉ በአንጃማ /Anjaammaa/ ወይም በዋዓ በተመረጠ ግለሰብ ነው። እንደ ሃይማኖቱ ተከታዮች እምነት እሱ ሊያናግራቸው የሚፈልጋቸው ደግሞ የሚመረጡት ልዩ በሆነ ውስጣዊ የተግባቦት ድምጽ ነው። በዋዓ እና በተመረጠ ግለሰብ መካከል የሚኖረው ግንኙነትም ግላዊ /personal/ ነው ተብሎ የሚታመነው ለዚህ ነው።

በጥንታዊ ህዲያዎች ምንም እንኳን አምላክ እንደሆነ የሚያምኑት ዋዓ አንድ ቢሆንም የእኔ አምላክ (ኢ- ዋዓ /I Waa'a/) ፣ የአባቴ አምላክ (ኢያን ዋዓ /Iyyann Waa'a/) ፣ የእኛ አምላክ (ን-ዋዓ /Ni Waa'a/) በማለት ይጠሩታል። አንድ ፈንዳንቾ ክፉ ነገርም ሆነ መልካም ነገር ሲገጥመው ነገሩ የሚያያዘው ከአምላክ ጋር ነው። መልካም ነገር ሲገጥመው የእኔ አምላክ ይሄን አደረገልኝ በማለት የሚናገር ሲሆን በሌላ በኩል አንድ ፈንዳንቾ ንብረቱ ቢበላሽበት ለምሳሌ፣ ከብት ቢሞትበት የእሱ አምላክ ከምንም የማያድን ወይም አመዳም (ግዕል-ቡቻም /gii'l buchchaam/) እንደሆነ ይነገረዋል።





ይህም አባባላቸው አምላክህ ከብትህን እንኳን ሊያድን የማይችል ነው የሚል ወቀሳ ማቅረባቸውን ያመለክታል።

ፈንዳነኖ የተለያዩ የሚመለኩ መናፍስት ያሉት ሲሆን የግንኙነት ተዋረድም እንዳላቸው በተከታዮቹ ይታመናል። በዚህ መሰረት ዋዓ (የሁሉ የበላይ አምላክ) እንዳለ ሁሉ ጃራ[66] /Jaara/ የሚባል ትንሹ አምላክ አለ። በሀዲያ ባህል የፈንዳነኖ ተከታይ የሆነን ወንድ ከክፉት ሁሉ የሚጠብቅ ጃራ የተባለ መንፈስ አለ ተብሎ ይታመናል። ይህ መንፈስ ወይም ጃራ የተቆጣ ቀን ያንን ሰው ከመጠበቅ ራሱን ገሸሽ እንደሚያደርግም ይነገራል። ቁጣውን ለመግለጽና የሰውዬውን ጥፋት ለማጋለጥ ያንን ሰው በበሽታ ይመታል። በዚህ ጊዜ ግለሰቡ ከጃራው ጋር ለመታረቅ ምን ማድረግ እንዳለበት ጃራው መግለጽ አለበት። ለምሳሌ፣ ያ ሰው በሚስቱ፣ በልጆቹና በጓደኞቹ ላይ በደል ፈጽሞ ቢሆን ጤናማ ግንኙነት እንዲኖረዉ ይገልጸዋል። በዚህ ሁኔታ ግለሰቡ የተባለውን አስተካክሎ ከመንፈሱ ጋር ሲታረቅ መረበሹና መታወኩ ይቆማል።

ቀደም ሲል እንደተጠቀሰው ወንዶችን ከክፉ እንደሚጠብቃቸው የሚታሰበው መንፈስ ጃራ ነው ተብሏል። በተመሳሳይ ሁኔታ ሴቶችም የሚመሩበትና የሚጠበቁበት መንፈስ አለ፤ ይሄም መንፈስ ኢዶታ /Idoota/ በመባል ይታወቃል። ሴቶች አንድ ላይ ሆነዉ፣ ደግሰዉ በመብላትና በመጠጣት የሚያከብሩት በአል ኢዶታ-ብጥማ በመባል

[66] ጃራ በሃይማኖቱ ለሽኬ-ጃራ እና ለዋቅች-ጃራ ተብሎ የሚታወቅ ሲሆን ልዩነታቸዉን በተመለከተ፣ ለሽኬ-ጃራ መንፈሱ ረገብ ያለ እንደሆነ የሚነገር ሲሆን ለዋቅች-ጃራ የሚባለዉ ደግሞ የዛር መንፈስ የሚወርድበትን ግለሰብ (ቦሮዳንቾ) እሳት ዉስጥ ሊከት የሚችል ጠንካራ ጃራ (የዛር መንፈስ) እንደሆነ ይነገራል።

በእል *እዶታ-በጥማ በመባል ይታወቃል*:: እነዚህ ሁሰቱ የመናፍስት አይነቶች ተጠሪነታቸው ሁሉን ሰሚችል እምላክ *(ቆጫንች ዋዓ* /Qooccaanch Waa'a/) ነው ተብሎ ይታሰባል። በሌላ አባባል *ጃራ* እና *እዶታ* ሁሰቱም የተፈጠሩት *በዋዓ* (ፈጣሪ) እንደሆነ በሃይማኖቱ ተከታዮች ይታመናል። *በጃራ* የሚጠበቁት ወንዶች እና *በእዶታ መንፈስ* የሚመሩ ወይም የመሚጠበቁ ሴቶች ደግሞ አቅጣጫ የሚያገኙት (የሚመሩት) በግላቸው በሚሰሙት ውስጣዊ ድምጽ ነዉ።

*ያገቡ ጉልማሶች መንፈሱን ሰማስደሰት ሲሉ የሚያዘጋጁት* ልዩ የምግብ ድግስ አሰ። የወንዶች *ጃዕል-ቡሎ* /Jaa'l bullo/ ሲባል የሴቶቹ *እዶጥ-ቡሎ* /Idooxx bullo/ በመባል ይታወቃል።

*የእዶታ* ድግስ አንዲት ሴት የእናትነት ወጓን ከጀመረች በሁዋላ በየሰባት አመት የምታከብረው በአል ነው። ሰዚህም በሰባተኛ አመቷ ከጓደኞችዋ ጋር በመሆን ግብዣ በማድረግ ስነስርአቱን ትፈጽማሰች። *የእዶታ መንፈስ* ባል ሚስቱን በተደጋጋሚ ከመታት (ከጎዳት) ድንገት ሲቆጣ ይችላል። ነገር ግን ሁሰቱም ተስማምተው ሰላማዊ ኑሯቸውን ሲጀምሩ ወዲያውኑ *እዶታው* ጸጥ ይላል።

*በፈንዳነኖ* ከ*ጃራ* እና *እዶታ* በተጨማሪ ሌሎች በአንጻራዊነት እንደሚሻሉ የሚታሰቡ መናፍስት አሉ፤ *ወሪቃ* /Woriiqa/ እና *ጌርግሳ* /Geergisa/ ። *ወሪቃ* ከበሮ እያስመታ የሚጠነቁል መንፈስ ሲሆን መንፈሱ ያደረበት ደግሞ *ወሪቅ-መንቾ* /Woriq mancho/፣ኪራንቾ/kiiraanchcho/ ወይም *ጃዕል-መንቾ*/ jaa'l-mancho/ ተብሎ ይጠራል። *ጌርግሳ* መንፈሱ ሲሆን *ጌርግስ-መንቾ* /Geergis-mancho/ ደግሞ የጥንቆላ መንፈሱ





*ያረፈበት* ግለሰብ ነው። እነዚህ *መናፍስት* ባንድ ሰዉ ውስጥ ቢገቡና *መግባታቸው* ቢገለጥ ግለሰቦቹና ቤተሰቦቹ ባይፈልጉም *መቃወም* አይችሉም። በዚህ *መንፈስ* የተያዘን ሰው ከመንፈሱ ነጻ ሲያስወጣ የሚችለው እውነተኛ ወይም ጠንካራ *ፈንዳንቾ* እንደሆነ ይነገራል።

*ጅና* /Jina/ (ጂኒ) ሌላው የመንፈስ አይነት ሲሆን አነስተኛ ማእረግ ወይም ቦታ ያለዉ፣ ብሎም አቅም የለሽ የሚባል አይነት *መንፈስ* ነው። ይህ *መንፈስ* ርኩስ እንደሆነ በጥንታዊ ሀዲዮች የሚታመን ሲሆን በጥሩ አቋም ያደገን ወይም ያለን ግለሰብ ሲጎዳ እንደማይችል ያምናሉ። ሀዲያዎች እንደ *ሀቡሳ* እና *ሼጣና* ያሉ ርኩሳን *መናፍስት* በሰው አምሳል ሲገለጡ እንደሚችሉ ያስባሉ። እነዚህ አንድን ሰው በተሰይ የማህበረሰቡን ህግ የጣሰን ወይም የሞራል ውድቀት ውስጥ የወደቀን ሰው በቀላሉ ያጠቃዋል ተብሎ ይታመናል። ይህን ጉዳት ደግሞ ሲያደርስ የሚችሰው አንድም፣ በጊዜያዊ ጉዳት መትቶት በመጥፋት ወይም በሰውዬው ላይ መንፈሱ በማደር ሲጎዳ፣ ሲያሰቃየው ይችላል። ነገር ግን ሰይጣንን ሰማባረር ችሎታ እንዳሰው የሚታመንበት *ፈንዳንቾ* ወይም *አንጃማ* መስዋእት በማድረግ፣ ምግብ አሰርቶ በጨለማ ስፍራ በመወርወር ሲያበርረው ይችላል።

*በፈንዳነኖ* ሃይማኖት ሰእባብ በተሰይም እንዳየቀሰሙ አይነት የተሰያየ አመሰካከትና ስፍራ ይሰጣል። እባቡ *የጃራ መንፈስ* እንደሚያርፍበት ስሰሚታመን ይከበራል። ሆኖም ሁሉም የእባብ አይነት (መልክ) እምልኮ (አክብሮት) አይሰጠዉም። በጥንታዊ የሀዲያ ሃይማኖት ቡናማ/brown/ እና ቀይ/red/ ቀሰም ያላቸው እባቦች ሰመልካም መናፍስት መጓጓዣ እንደሆኑ ሲታመን ጥቋቁር እባቦች ግን ሰእኩይ መናፍስት

መጓጓዣ እንደሚያገለግሉ ይታመናል፡፡ በዚህ ምክንያት ቀይ እና ቡናማ ቀለም ያላቸው በጥንታዊ የሃይማኖቱ ተከታይ ሀዲዮች አይገደሉም፤ ይልቁን ይፈራሉ፤ ይከበራሉ፡፡ ሴላ ሰው እንኳን በስህተት ገድሎ ቢያገኙት ልክ የቅርብ ዘመድ የሞተባቸው ያህል ፊታቸውን በመንጨት ሀዘናቸውን ይገልጻሉ፡፡ ሰው ሲሞት እንደሚቀበር ሁሉ ለሞተው እባብ ሳር እና ቅጠል በመቁረጥ በላዩ ላይ ይነሰንሱበትና በክብር እንደቀበሩት አስከሬን አይነት እንክብካቤ ይደረግለታል፡፡ በአንጻሩ ጥቁር[67] እባብ ከክፉ መንፈስ (ሰይጣን) ጋር የሚያያዝ በመሆኑ በተቻለ መጠን አሳደው ይገድላሉ፡፡

## 4.3. የአምልኮና የመስዋእት አቀራረብ ስርአት

በፈንዳነኖ ሃይማኖት ውስጥ የሚሳተፉት ለመስዋእት የተለያዩ ነገሮችን ያቀርባሉ፡፡ ከነዚህም ዋና ዋናዎቹ፡-

- የእንስሳት ደም[68]
- ቡሎ(የገብስ ዱቄት በማሰሮ ዉስጥ በቅቤ ታሽቶ ተሰርቶ የሚዘጋጅ ምግብ)
- የተነጠረ ቅቤ (*ጠሊላ*/Xaliila/) እና
- የከብቶች ትኩስ ወተት (*ኢበዶ*/ Iibado/) ናቸው፡፡

በእነዚህ የአምልኮው ስነስርአት ሲፈጸም *ሰዳ* (Sadda) ተብሎ የሚታወቀዉን የሳር አይነት ወስደው በደም እና በተነጠረ ቅቤ ውስጥ በመንከር ወደ ሰማይ አምላክ፣ ጸሀይ፣ ጨረቃ እና ክዋክብት በመርጨት ያመልካሉ፡፡ አምልኮው የሚቀርበው

[67] በሀዲያ ባህል ጥቁር (*ሄመቻ*) አብዛኛዉን ጊዜ የመልካም ነገር ተምሳሌት (ወኪል) አይደለም፤ በመሆኑም፣ ለመስዋዕት የሚቀርቡ በጎች መልካቸዉ ቡላ ወይም ቀይ ነዉ፡፡

[68] በደም የሚደረግ መስዋእት ከኦሪት ዘመን የመስዋእት ስርአት ጋር ተመሳሳይነት ያለዉ ነዉ፡፡





*ለዋዓ* ከሆነ መስዋእቱ የሚደረገው በየትኛውም የቀን ክፍል ሊሆን ይችላል፡፡ አምልኮው ለጸሀይ፣ጨረቃና ከዋክብት ከሆነ ደግሞ ምሽት ነው የሚሆነው፡፡ ለጸሀይ፣ ለጨረቃና ለክዋክብት አምልኮ የሚደረግበት ምክንያት እነሱ *ለዋአ* (ሁሉን ከፈጠረ አምላክ) ቀጥሎ አነስ ያሉ አማልክት እንደሆኑ ስለሚታመኑ ነው፡፡

ቀደም ሲል *ጃራ* /Jaara/ የወንዶች ጠባቂ መንፈስ እንደሆነ *እዶታ* ደግሞ የሴቶች ጠባቂ መንፈስ እንደሆነ ተነስቷል፡፡ እነዚህም በፈንዳነኖ ስርአት በሚከተሰው መልኩ የአምልኮ ስነስርአት ይደረግላቸዋል፡፡

- ለመስዋእት የተሰዋው እንስሳ ደም በአምላኪዎቹ ወንዶች፣ ሴቶችና ህጻናት ግንባር ላይ ይቀባል፡፡
- ለሃይማኖታዊ ስነስርአቱ ከተዘጋጀው ደም የቤቱ ምሰሶ ወይንም (ኡቱባ /Utuba/) በደም ይቀበል፡፡
- እቤት ውስጥ የወተትና የቅቤ ምርት ሲትረፈረፍ *ጃዕል-ቡሎ* /Jaa'l-bullo/ ይዘጋጃል፡፡ በሌላ በኩል ሴቶች በየለባት አመታቸው ለሚያደርጉት የእዶታ በአል *እዶጥ-ቡሎ* /Idooxx-bullo/ ይዘጋጃል፡፡

*ወሪቃ* (Woriiqa'a) እና ጌርግሳ (geergissa) የሚባሉት በአንጻራዊነት መልካም የሆኑ መናፍስት እንደሆኑ የሚታመንባቸው ናቸው፡፡ እንደ ሀይሴ (1971) አገላለጽ ወሪቃ የሚባለው እሳቤ ከሀዲያ የመነጨ ሲሆን፣ ጌርግሳ የሚባለዉ ለቅዱሳን የተሰጠ ስያሜ ሆኖ በ15ኛዉ ምእተ አመት በዘርዓ ያዕቆብ ዘመነ መንግስት በነበረው የክርስትና እምነት ተጽእኖ /influence/ ምክንያት ወደ ፈንዳነኖ ሳይገቡ እንዳልቀሩ ይገመታል፡፡ በነዚህ መናፍስት የተሞሉ ግለሰቦችን

የሃይማኖቱ ተከታዮች ስለተለያዩ ጉዳዮች ለምሳሌ፣ ስለኢኮኖሚ፣ ስለጤናና ስለ ማህበራዊ ችግሮች አስመልክተው ያማክሯቸዋል፡፡ እነዚያ መናፍስት ያደሩባቸው ግለሰቦችም ያንን ችግራቸውን እንደሚመልሱላቸው በመግለጽ እጅ-መንሻ እንዲሰጧቸው ይጠይቃሉ፡፡ የተጠየቁትን ስጦታ መስጠት ባይፈልጉ እነዚያ ተጠያቂዎች መንፈሱ በራሳቸው፣ በቤተሰቦቻቸው እና በንብረታቸው ላይ ጉዳት ያደርሳል ተብሎ ስለሚታሰብ ስጦታው የግድ ይሰጠዋል፡፡

ቀደም ሲል ቡናማ በእንግሊዝኛዉ አጠራር /brown/ ቀለም ያለው እባብ በፈንዳነና ሃይማኖት ተከታዮች በእጅጉ እንደሚከበር ወይም እንደሚፈራ ተገልጿል፡፡ እባቡ ወደ አንድ የሃይማኖቱ ተከታይ ቤት ቢገባ ጃራ እንደገባ ስለሚታመን የቤቱ ባለቤት እንደ ኢኮኖሚ አቅሙ በግ፣ ፍየል ወይም በሬ አርዶ ደሙን ከቅቤ ጋር በመቀስቀል ለዚያ እባብ ይሰጣል፡፡ ያ እባብ የቀረበለትን ደም ቢጠጣ፣ ቅቤውንም ቢልስ፣ መንፈሱ በመስዋዕቱ እንደተደሰተና እንደተቀበለው በማሰብ በደስታ ይሞላሉ፡፡ ነገር ግን እባቡ የቀረበለትን ደምና ቅቤ ሳይቀምስ አልፎት ቢሄድ መንፈሱ በቤተሰቡ አባላት ላይ እንደተቆጣ ስለሚታሰብ ቤተሰቡ በጭንቀት ይሞላል፡፡ ለእባቡ ቁጣ ቀጥለው የተጠቀሱት አይነት ጥፋቶች በተለምዶ እንደምክንያትነት ይጠቀሳሉ፡፡

- ♦ አንድ ህፃን ልጅ በቅርብ የደረሰን የበቆሎ እሸት ወላጆቹ የአምልኮ ስነስርአት[69] ሳያደርጉ አስቀድሞ በልቶ ከሆነ፣

[69] በፈንዳነና ሃይማኖት ምርት ሲደርስ፣ መጠጥ ሲቀርብ፣ ላም ስትወልድ ወዘተ. የመጀመሪያዉ ቅምሻ ሳይደረግ ወይም አስቀድሞ የመስዋእት ስነስርአት ሳይፈጸም አይበላም ወይም አይጠጣም፡፡ ይህም ስርአት በኩራትን መስጠት(በሀዲይሳ *ያርሽማ ወይም ሉዶ ሉዊማ)* ተብሎ ይጠራል፡፡ ለምሳሌ፣ የበቆሎ እሸት ከመበላቱ በፊት የበቆሎ ንፍሮ ተቀቅሎ ምሽት ላይ ስዚህ ስላደረስከን ተመስገን *(ሉዶ እትስታንና ገለታ)* ተብሎ ከዛፍ ስር ወይም ከጓሮ በኩል ይጣላል፡፡





- ♦ አንድ ላም መጀመሪያ ጥጃ እንደወለደች ተጠራቅሞ የሚጠጣ እንገር (ሀደሮ /haddaro/) ከመጠጣቱ በፊት መደረግ ያለበት የአምልኮ ስነስርአት ሳይደረግ ከቤተሰብ አባላት አንዱ ቢጠጣ፣
- ♦ ከቤተሰብ አባል አንዱ ለአምልኮ ፋይዳ ያለውን ዛፍ ወይም አድባር ቢቆርጥ እና የመሳሰሉት ለመንፈሱ መቆጣት ምክንያት ሊሆን ይችላል፡፡ እላይ በቀረቡት ሁኔታዎች ዉስጥ ጥፋቱ ከቤተሰብ አባላት የየትኛው ግለሰብ እንደሆነ ለመለየት አስቸጋሪ ከሆነ ከቤተሰቡ በእድሜ ተለቅ የሚለው ሰው ወደ ጠንቋይ (*ኪራንቾ* / Kiiraancho/) ዘንድ በመሄድ *ጃራው* የተቆጣበትን ምክንያት ይጠይቃሉ፤ ወይም ያማከራሉ፡፡ ከዚያም ለዚያ ጥፋት መደረግ የሚገባውን ቅጣት ተቀብለው ይፈጽማሉ(ዝኒ ከመሁ:10)፡፡

*በፈንዳነና* ሃይማኖት *ስለሀቡሳ* ወይም *ሼጣና* የተለየ አመለካከት አለ፡፡ አንድ ሰው የሞራል ውድቀት፣ ወይም ጥፋት የተገኘበት ካልሆነ በስተቀር ይሀ መንፈስ እንደማያገኘው በጥንታዊ ሃይማኖቱ ይታመናል፡፡ ምናልባትም *የሼጣና* ወይም *የሀቡሳ* መንፈስ አንድን ሰው ሲለክፍ የሚችልበትን ሁኔታ በሚመለከት ሀይሌ (1971) የፐላዝኮዊስኪ (1957)'ን ጠቅሶ እንደሚከተለው ይገልጻል፡፡

ሀ. አንድ ሰው የግብረ ስጋ ግንኙነትን ከቤት ውጭ በቁጥቋጦ ወይም የትም ቦታ በቀን ላይ ቢያደርግ፣

ለ. ትኩስና ቅባት ያለበትን ምግብ ከቤት ውጭ እየበላ ቢገኝ፣

ሐ. አንድ ሰው በጫካ፣ በቁጥቋጦ፣ በዛፍ ስር ወይም ወንዞች አካባቢ በተለይም ጠራራ ጸሀይ (ሀሩር) ባለበት ጊዜ ተኝቶ ቢገኝ፣

መ. አንድ ሰው ጥቁር እባብ በመንገድ ወይም በቤቱ አጋጥሞት ለመግደል ሞክሮ መግደል ሳይችል ሲቀር ወዘተ. በዚያ መንፈስ ሊያዝ እንደሚችል ፈንዳኖ ያምናሉ።

እላይ በተጠቀሱት ሁኔታዎች አንድ ሰው *በሺጣና* ወይም *በሀቡሳ* ቢለከፍ፣ ጠንካራ *ፈንዳንቾ* ከሆነ መንፈሱን ሊቃወም ይችላል፤ ወደ ጠንቋይ (*ኪራንቾ*) ጋ አይሄድም። ነገር ግን ጠንካራ እምነት የሌለው ከመንፈሱ ነጻ ለመሆን ወደ ጠንቋይ ይሄዳል። ከዚያም በጠንቋዩ የሚታዘዘውን ማንኛውንም መስዋዕት ወይም ስጦታ ያበረክትለታል።

በሀዲያ ትውፊት ለሰይጣን መስዋእት እንዲሆን የታረደ ማንኛውም ስጋ ወይም የተዘጋጀ ምግብ በማንም እንዲበላ አይፈቀድም። በሌላ በኩል ለአምላክ (*ዋ*)፣ ለጸሀይ (*ሌሊንቾ*)፣ ለጨረቃ (*አገና*) ለከዋክብት (*ቦላንካ*)፣ *ለጃራ* /Djaara/፣ *ለእዶታ* /idoota/፣ *ለወሪቃ* /woriiqa/፣ *ለክቶሳ* /kittosa/ እና *ለጌርግሳ* /geergisa/ የተዘጋጀው ምግብ ሊበላ ይችላል፤ አይከላከልም።

## 4.4. ጋብቻ *በፈንዳነኖ ሃይማኖት*

*ፈንዳንቾ* የሆነ አንድ ሰው ከፈንዳነኖ ሃይማኖት ውጭ ለምሳሌ፤ ከክርስቲያን፣ ከሙስሊም ወይም ከሌላ በፍጹም እያገባም። አንድ *ፈንዳንቾ*፣ ከሀዲያ ብሄር እና *ፈንዳነኖን* ተከታይ ከሆነ ቤተሰብ ማግባት እንደሚጠበቅበት በሃይማኖቱ ይታመናል። የፈንዳነኖ ተከታይ የሆነ ሰዉ ሊኖረው የሚችለውን የሚስት ቁጥር በሚመለከት ገደብ የለውም፤ እንደ ኢኮኖሚ አቅሙና እንደፍላጐቱ የፈለገውን ያህል ቁጥር





ሚስት ሊያገባ ይችላል። በምድር በነበረበት የህይወት ዘመኑ ብዙ ሚስት አግብቶ የፈታ ሰዉ በሰማይ ቤት አብሯት የሚሆነዉ ደግሞ ከመጀመሪያ ሚስቱ ጋር ብቻ እንደሆነ ይታመናል። በምድር ያላገቡ ሰዎች ግን በሰማይ ቤትም ለዘላለም ሳያገቡ ወይም ሳጤ እንደሆኑ ይኖራሉ ተብሎ ይታመናል (ሀይሌ 1971፡ 12)። በተከታዩ ክፍል፣ አንድ *ከፈንዳነኖ* እምነት ያፈነገጠ ሰው ዳግም የሃይማኖቱ ተከታይ የሚሆንበት ስርአት ቀርቧል።

## *4.5. መንሰማ*

በጥንታዊ የሀዲያ ባህል አንድ ሰው የፈንዳነኖ ሃይማኖት በማይፈቅድ ስርአት ውስጥ ቢኖር ወይም የሃይማኖቱ ተከታይ ባይሆን ወደ ፈንዳነኖ ሃይማኖት የሚቀላቀልበት ስርአት አለ። ይህም ስርአት *መንሰማ* /Manisimma/[70] ተብሎ ይታወቃል። በሌላ አነጋገር፣ የማንጻት (ወደ ሰዉነት የመመለስ) ስነ ስርአት ማድረግ እንደማለት ነው። አንድ ሰው ከሚከተሉት መንገዶች በአንዱ የፈንዳነኖ ሃይማኖት ተከታይ ሊሆን ይችላል። እነዚህም:-

- ግርዛትን መፈጸም የሃይማኖቱ መሰረትና ቀዳሚ ተግባር መሆኑ፣
- የፈንዳነኖ ሃይማኖት ተከታይ ሰው ልጆች ጋብቻቸውን እንደፈጸሙ፣

[70] በመንስማ ስርአት ዉስጥ የሚያልፈዉ ከሃይማኖቱ ዉጭ የነበረ ወይም ያፈነገጠ ሰዉ ብቻ አይደለም። አንድ ፈንዳንቾ በጦርነት ተማርኮ የነበ ረ ከሆነ ከምርኮ ነጻ የወጣ ቢሆን እንኩዋን ባሪያ ሆኗል ስለሚባል የመንስማን ስርአት እንዲፈጽም ይደረጋል። ስርአቱን ሲፈጽምም በመጀመሪያ ጥቁር በግ ታርዶ በደም ይታጠባል፤ የጥቁር በግ መታረድ ትርጉሙ ግለሰቡ ባርያ ነበር ተብሎ ስለሚታመን የባርነትን አስጸያፊ ገጽታ አመልካች ነዉ። ቀጥሎም ከባርነቱ ገጽታ ፈጽሞ መንጻቱን (ጨዋ መሆኑን) ለማመልከት ሲባል ቡላ መልክ ያለዉ በግ ታርዶ እንደገና በበጉ ደም ይታጠባል።

- አንድ ፌንዳንቾ የነበረ ሰዉ በጦርነት ምክንያት ከተማረከበት ሲመለስ
- በተለያየ ምክንያት ከፌንዳነኖ ሃይማኖት ውጭ የሌላ ሃይማኖት ተከታይ የነበሩ የሀዲያ ብሄር አባላት የሆኑ ወንዶች ናቸዉ።

እላይ ከተጠቀሱት ስልቶች በአንዱ አንድ ሰው ፌንዳንቾ ሲሆን ስነስርአቱን አስፈጻሚ አካላት አሉ። ስርአቱን አስፈጻሚዎች አንድም፣ እውቅና የተሰጣቸው *አንጃማ* (በነጠላ ቁጥር አንጃንቾ) ሲሆኑ ሲችሉ በሌላ በኩል በብሄረሰቡ የፌንዳነኖን ህግጋትንና ልምምዶችን ጠንቅቆ እንደሚያከብርና እንደሚፈጽም የሚታመን ሽማግሌ ሊሆን ይችላል።

አንድ ፌንዳንቾ የነበረ ሰው ወደ ሌላ ሃይማኖት ቢቀየር ወደ መጀመሪያው ሃይማኖቱ ወይም ፌንዳነኖ ለመመለስ የሚደረግ ስርአት አለ። ይህ ሰው የመንጻት ስነስርአት ሲደረግለት ከጉማሬ ቆዳ የተሰራ አለንጋ *(ሎጵ ሀለንጋ* /loophph halagga/) በጎሮሮዉ ውስጥ ይከተትና እውስጡ የገባውን ማንኛውንም የተመገበውን ነገር እንዲያስመልስ ይደረጋል። ይህም የሚደረገው ግለሰቡን ቀጥቶ ወደ መጀመሪያው ሃይማኖቱ ለመመለስ እና ከነበረበት ነውር ለማንጻት ሲባል ነው። አለንጋው ያንን ሰው የመግራት ወይም ስርአት የማስያዝ ተምሳሌትነት ሲኖረው የጉማሬ አለንጋ መመረጡ ደግሞ ጉማሬ *(ሎባ)* በሀዲያዎች ዘንድ የተቀደሰ እንደሆነ ስለሚታመን ነው። በሆዱ ውስጥ የነበረውን እንዲያስታውክ መደረጉ ደግሞ ቀደም ሲል በፌንዳንቾ ያልታረደን እርኩስ ስጋ በልቷል ተብሎ ስለሚገመት ያንን በትዉከት ለማስወገድ ተብሎ ነዉ።





የማንጻቱ ስርአት ሲጠቃለል *አንጃንቾ የመንጻት* ስርአቱን በሚወስድ ሰው ተገዝቶ የተዘጋጀውን ፍየል ወስዶ ያርዳል። ይህንን ስጋ ሌሎች *ታዳሚዎች* ከመብላታቸው በፊት *አንጃንቾ* ከተዘጋጀው *ቡሎ* (ከገብስ በቅቤ ተሰዉሶ የሚሰራ) ከገበታ በሁለት እጆቹ በመውሰድ በእጆቹ ላይ ዘርግቶ ይይዛል። ከዚያም ወደ ሃይማኖቱ የሚመለሰው ግለሰብ የአንጃንቾን ሁለቱን እጆች ተራ በተራ ከላመ በሁዋላ በሁለቱም ጉንጮቹ ሞልቶ መብላቱን ይቀጥላል። እየበላ እያለም የአባቴ ወሪቃ *(እያን ወሪቃ* /Iyyan wooriiqa'a/*)* በማለት ይጣራል። ያ ሰው ከአንጃንቾ እጅ አራት ጊዜ ደጋግሞ ከበላ በሁዋላ ሌሎች *ታዳሚዎች* ከገበታው ምንም አይነት ተጨማሪ ስርአት ሳይደረግ ይበላሉ። ከዚያም ይህ ወደ ሃይማኖቱ የተመለሰው ግለሰብ *መመለሱን* የሚያሳይ ከእንጨት የሚሰራ ማበጠሪያ *(ሹዳቃ* /Shudaqqa/) በጸጉሩ ላይ ይሰካል። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ያ ሰው ወደ እምነቱ *መመለሱን ለማመልከት መንሰማማ* ወይም ወደሰዉነት ተመልሻለሁ ሲል ለሌሎች ያወራል። የዚህ ስርአት ሂደትም *መንሰምማ* /manissamimma/ በመባል *ይታወቃል*።

ግርዛት ከመንስማ ሂደት አስቀድሞ መከናወን የሚገባ ተግባር ነው። አንድ ሀዲያ ወጣት በተለምዶ ከማግባቱ በፊት የግርዘት ስርአት ይፈጽማል። ሆኖም በአንዳች ምክንያት ሳይገረዝ ቢያገባ *መንሰምማን* ለመፈጸም ልጅ እስኪወለድለት ድረስ ይጠብቃል። ልጅ ሲወለድለት ደግሞ ከልጁ ጋር በመገረዝ በመንስምማ ሂደት አልፎ *ፌንዳንቾ* ይሆናል። ይህንን ስርአት ካልፈጸመ ምንም እንኳን ያገባ ቢሆንም *መጸምም* ሆነ ለምግብነት የሚዘጋጁ እንስሳትን ስጋ መባረክ

ወይም *ሀላልስማ* /Halaalisimma/[71] አይችልም፤ ምክንያቱም የመንሰምማን ስርአት እስካልፈጸመ ድረስ እንደነጻ አይታሰብምና። በሌላ በኩል አንድ አባት ሲሞት፣ ልጁ በእድሜ ሰጋ ቢሆንም አባቱን እንዲወክል ተብሎ ተገርዞ እንዲጸም ይደረጋል። ልጁ ያንን ስርአት ከፈጸመ በሁዋላ የሚታረዱ እንስሳትን ሊባርክ ይችላል። በአንጻሩ *በፈንዳናና* ሃይማኖት ሴት ካሰመጸሟም ባሻገር የሚታረዱ እንስሳትን አትባርክም።

## 4.6. መሰረታዊ ሃይማኖታዊ ስርአቶች እና ልምምዶች

*ፈንዳናና*፣ የራሱ የሆነ ሃይማኖታዊ ስርዓቶች አሉት፣ ከእነዚሁ ስርአቶች እንደ አዕማድ (መሰረታዊ ጉዳይ) የሚታዩት *ሀይባና* እና *ሶመኖ* ናቸው።

### ሀ. *ሀይባና፣ የጾም መያዣ ቅድመ ዝግጅት*

በፈንዳናና ሃይማኖት ከፍተኛ አጽንኦት የሚደረግበት የጾም ወቅት አለ። ይህ የጾም ስርአት ከመጀመሩ አስቀድሞ ግን የጾም መያዣ ቅድመ ዝግጅት ወይም ስነስርአት አለ። ይህም ስነስርአት *ሀይባና* /Haybaana/ ተብሎ ይታወቃል። *የሀይባና* ስርአት የሚፈጸመው በህዳር ወቅት ሲሆን በጥንታዊ ሀዲያ የወሩ ስያሜ *ሀይባና* በመባል ይጠራል።

[71] *ሀላላ* ሁለት አይነት ነዉ፤ አንደኛዉ አይነት የሚታረደዉን እንስሳ ጆሮዉን ቆረጥ በማድረግ *(ቃፍ አዕማ)* ሲሆን ሌላኛዉ፣ የእንስሳዉን አንገት በማረድ የሚከናወን ነዉ። የመጀመሪያዉ አይነት ህላላ የሚከናወነዉ አንድ እንስሳ ድንገት ቢታመም ወይም ቢሰበር ሲሞትም ላይሞትም ስለሚችል እንስሳ ድንገት ቢታመም ወይም ቢሰበር ሲሞትም ላይሞትም ስለሚችል





*ሶመኖን ወይም ጾሙን* በታህሳስ ወር የሚይዙ ፈንዳና በህዳር ወር በየአካባቢያቸው ወዳሰው ትልቅ ወንዝ በመውረድ ለጾም ዝግጅት የመንጻት ስርአት ያደርጋሉ። ወንዝ ውስጥ ከገቡ በሁዋላ የጉመሬ አሰንጋ በመያዝ ልክ የጉማሬን ዋና አይነት አስመስለው ይዋኛሉ። ወንዙ ውስጥ እያሉም መላ ሰውነታቸውን ይታጠባሉ። ይህ የመታጠብ ስነስርአት ውጫዊውን የሰውነት ክፍል ብቻ በመታጠብ አያቆምም፤ በአፋቸውና በሆዳቸው ውሃ በማስገባት ከዚያም በማስመለስ እዉስጣቸዉ ሊኖር ይችላል ተብሎ የሚታመነዉን ቆሻሻና አሮጌውን ምግብ በማስወገድ ማንጻትንም ያካትታል። ይህም ፈንዳንች እመቱን ሙሉ ከሰራዉ ሀጢአት መንጻቱን ለማሳየት የሚፈጽመዉን ስነስርአት አመልካች ነዉ።

በወንዝ ውስጥ የነበረው *የሀይባና* ጊዜ ሲያበቃ ከወንዝ ውስጥ ይወጣሉ። የስነስርአቱን መፈጸም ለማመልከት ከወንዙ እንደወጡ *ገረምብ ፊታ* /Garamb fiita/ የተባለን አበባ፣ መፋቂያ (*ሚንቁሳንቾ*/Minqeesaancho/)፣ የእንጨት ማበጠሪያ (*ሹዳቃ* /Shudaqqa/)[72] እና የተሰያዩ የሀይባና ቅጠሎችንና ሳርን በመያዝ ጥርሳቸውን እየፋቁ፣ ማበጠሪቸውን ጸጉራቸው ላይ ሰክተው፣ *የሀይባ* አበባና መፋቂያ ጆሮአቸው ላይ አድርገው ወደ ቤታቸው ያመራሉ። እቤታቸው እንደደረሱም ለሚስቶቻቸው የሀይባና ቅጠል እና አበባ

[72] ጾሙ ለ30 ቀናት የሚደረግ ሲሆን ፈንዳንቾ መጾም ሲጀምር ማበጠሪያዉን በጸጉሩ መሃል አናት ላይ ወደኋላ በማድረግ ይሰካል። ነገር ግን ጾሙ (ሶመኖ) ከተጀመረ 15ኛዉ ቀን ላይ ማበጠሪያዉን ከመሃል አናት አንስቶ በጸጉሩ በጎን በኩል ይሰካል፤ግማሽ ጾሜአለሁ ለማለት። በዚህ ቀን ስድስት ሰአት ላይ ጾሙን ያሳርፋል፤ ይሄም "ማሳረፍ" በሀዲይሳ *ሉሼፕሰማ* ተብሎ ይጠራል። እለቱም የጾም ጊዜ አጋማሽ በመሆኑ "እኩሌታ ቀን" (በጠንች በላ/baxxanchi balla/) ተብሎ የሚታወቅ ሲሆን እለቱ ተደግሶ የሚበላበት ቀን ነዉ። ሶመናንቾ ይህ ቀን ሲያልፍ ቀሪዉን አስራ አምስት ቀናት መጾሙን ይቀጥላል።

በማበርከት የጾም ወቅት ውስጥ ገብተናል (*ሀይባና ኣንጋሞ* / Haybaana aangaammo/) በማለት ያውጃሉ። በሃማኖታዊ ስነስርአቱ ጾመኛ ከማይጾመው የሚለየው ከፍ ሲል የተጠቀሱትን ነገሮች፣ መፋቂያ፣ ማበጠሪያና የመሳሰሉትን በሰውነቱ ላይ በማድረጉ ነው። በሃይማኖቱ ጾመኛ የሆነው *ፈንዳንቾ* ተብሎ ሲታወቅ የማይጾመው ደግሞ *እብጄ* / Ibje'ee/ ይባላል።

### ለ. *ሶመኖ*

*በሶመኖ*/Sommano/ የጾም ስነስርአት ሊሳተፉ የሚችሉት ለመንስማ ስርአት የበቁ ወንዶች ብቻ ናቸው። ወንዶችም ጾሙን መጀመር የሚችሉት 15 ዓመት ሲሆናቸው ነው። ሴቶችና ህጻናት እንዲጾሙ አይፈቀድም። አንድ *ፈንዳንቾ* እንደህመም ባለችግር ምክንያት ለመጾም ሳይመቸው ሲቀር *በአንጃንቾ* (*ሃይማኖታዊ መሪ*) ችግሩ ታይቶ ሌላ ጊዜ በመጾም እንዲያካክስ እድል ይሰጠዋል። በእንደዚህ አይነት ችግር ምክንያት ፈንዳኖ በዚህ ወቅት የሚመገቡት ምግብ *ጣስቤላ* /xasbeela/ በመባል ይታወቃል።

የሶመኖ አፈጻጸም ስርአት ሁለት መልኮች አሉት፤ የ15 እና የ30 ቀናት *ሶመኖ* ወይም ጾም ተብለው። *ታማሚዎች* ወጣት ልጆችና ሽማግሌዎች ለአስራ አምስት ቀናት እንዲጾሙ የሚደረግ ሲሆን ጤናማና ጉልማሳ የሆኑት ለሰላሳ ቀናት ይጾማሉ። የሃይማኖቱ *መሪ* የሆኑት *አንጃኖ* ግን ከሰላሳ ቀናት ያነሰ እንዲጾሙ አይጠበቅም ወይም አይፈቀድም። ፈንዳኖ ሰላሳ ቀኑን ሶመኖ ሲጀምሩ ጨረቃ በምስራቅ በኩል መታየቷን ይጠባበቃሉ። ለአስራ አምስት ቀናት የሚጾሙት ለሰላሳ ቀናት የሚጾሙት ከጀመሩበት አስራ አምስት ቀናት





ወይም ዘግይተው ነው። የጾሙ የመጀመሪያ ቀንና የመዝጊያ ቀን *በአንጃማ* አማካይነት በገበያና በመሰብሰቢያ ቦታዎች ይታወጃል። ጾሙ ከመጀመሩ አንድ ቀን አስቀድሞ ልዩ የፈንዳኖ ጾም መያዣ የምግብ ዝግጅት ይደረጋል፤ ይህም *ሶማዕን-ቡሎ* /somma'n-bullo/ ይባላል። *ሶማዕን-ቡሎ* ከተሰናዳ በሁዋላ የሚበላበት ስርአት አለው። የቤቱ አባወራ *ሶማዕን-ቡሎ* በገበታ ላይ ተደርጐ ቀርቦለት፣ ሚስቱ በባሏ ሁለት እጆች ላይ ቡሎውን ስታደርግለት "*እያን ወሪቃ! እያን ወሪቃ!*" (የአባቴ ወሪቃ ሁለት ጊዜ) በማለት ይጣራል። ይህንን ካደረገ በሁዋላ የራሱን ሁለት እጆች ቡሎውን እንደያዘ አንዴ ይስምና በቡሎው አፉን ሞልቶ አንዴ ይጉርሳል፤ ከዚያም የተረፈውን ቡሎ የተለየ ገበታ ላይ በራሱ ያስቀምጣል። ይህንን ሂደት አራት ጊዜ ይደጋግማል። ከዚያ በሁዋላ ሚስቱና የመጀመሪያ ልጁ የወሪቃውን ስም ከጠሩ በሁዋላ የእሱን እጅ በመሳም ከእጁ ድርሻቸውን ተቀብለው አፋቸውን ወይም ሁለቱንም ጉንጫቸውን በመሙላት ይበላሉ። ቀጥሎም ሌሎች ቤተሰቦች የራሳቸውን ድርሻ ይበላሉ። ይህም ስርአት የሚደረግበት ሰአት ጾም ከመጀመሩ አስቀድሞ ከሌሊቱ 9 እስከ 10 ሰአት ባለው ጊዜ ነው።

በዚህ ስርአት ጿሚዎቹ የተስፋፉ ቤተሰብ ካላቸዉ አስቀድመዉ ለጾም መያዣ ስርአት የሚሄዱት ወደ ታላቅ ወንድማቸዉ ቤት ነዉ። ታላቅ ወንድማቸዉም ከገብስ የተሰራ ቡሎ "*ንያናኖ አፍሰት ዋኣ*" ብሎ በእጁ ሲያደርግና የቡሎዉን መሃል በጣቶቹ ከፊት ከፊት ሲያደርግ ቅቤ በእጆቹ ባለዉ ቡሎ ላይ ይደረጋል። ከዚያም ታናናሽ ወንድሞች እየመጡ የታላቅ ወንድማቸዉን እጆች ተራ በተራ እየሳሙ ቡሎዉን ይቀበላሉ። ከዚያም በእድሜ ወደ ሚከተለዉ ታናሽ ወንድም

ቤት በመሄድ ተመሳሳይ ስርአት ይቀጥልና ሲጠናቀቅ ሶመኖ ተይዟል ይባላል።

ጿሚው (ሶመናንቾ) ከጾሙ መጀመሪያ እስከ መጨረሻው ቀን ድረስ ከንጋት እስከ ምሽት ምግብ አይቀምስም፤ ውሃ አይጠጣም፤ ከዚያም አልፎ ምራቅ እንኳን አይውጥም። በየምሽቱ ከቀኑ የጾም ጊዜ የሚደረገው የምግብ መብያ ጊዜ *አፍጥራ* /Afxira/ ይባላል። ጿሚው በምሽት ይህንን ሳያደርግ ጅብ ቢጮህ ጾሙ እንደሚበላሽበት ስለሚታመን ጾሙን ሳይገድፍ ወደ መኝታ ይሄድና እስከ ቀጣዩ ቀን *አፍጥራ* ድረስ ይቆያል። በዚህ የጾም ወቅት አስራ አምስት ቀናትም ሰላሳ ቀናትም የሚጾሙት ሁሉ ተመሳሳይ የጾም ህግ ይከተላሉ።

በጾም ወቅት፣ ጾሙ እንዳይበላሽ የፈንዳነኖ ሀይማኖት ተከታዮች ጥንቃቄ የሚያደርጉባቸው ነገሮች አሉ፤ ከነዚህም ዋና ዋናዎቹን ሀይሌ (1971፡19) እና ቃላዊ መላሾች በተከታዩ መንገድ ገልጸዋቸዋል።

- በጾሙ ወቅት የግብረስጋ ግንኙነት ማድረግ የተከለከለ ነው።
- አሳን፣ ዶሮንና የዶሮ እንቁላልን መመገብ አይፈቀድም።
- ስጋቸው የሚበላ እንስሳትን እንኳን ሳይታረዱ ቢሞቱ አይበላም፤ ይህ ሳይታረድ የሞተ እንስሳ በክት (*በሂታ* /Bahita/) በመባል ይታወቃል።
- ከውሻ ጋር ንክኪ እንዳይኖር ጥንቃቄ ይደረጋል።





- የሶመኖ ልምምድ ውስጥ የሌለ ሰው ያረደን ስጋ መመገብ አይፈቀድም። በሌላ አነጋገር፣ የእስልምና እና የክርስትና እምነት ተከታዮች ወይም ከፈንዳነኖ ውጭ የሆነ ማንኛውም ሰው ቢያርድ መብላት በሃይማኖቱ የተከለከለ ነው። ከዚህም አልፎ ከፈንዳነኖ ዉጭ የሆኑ ለምሳሌ፣ የክርስቲናና የእስልምና ሃይማኖት ተከታዮች የተጠቀሟቸዉ እቃ እንዳይኖር ጥንቃቄ ይደረጋል። አንድ የመመገቢያ እቃ እንደተነካካ ከተጠረጠረ በጉመሬ አላንጋ እቃዉ ተመቶ እንደሚነጻ ይታመናል።

## 4.7. ከሞት ወዲያ ህይወት

በፈንዳነኖ ሃይማኖት ተከታዮች ከሞት በሁዋላ ስለሚኖረው ህይወት ራሱን የቻለ የህይወት ፍልስፊና አላቸው። በሃይማኖቱ መሰረት ገነት (ጀነት) ወይም የአማኞች ማረፊያ እንዳለ ይታመናል። በሰማይ ለባት ደረጃዎች እንዳሉ የሚታሰብ ሲሆን ስለ ገሀነም ግን አንዳች የሚታወቅ ነገር የለም። ከሞት በኋላ ያለው ህይወት *አሄራ* /aheeraa/ በመባል ይታወቃል። አንድ ሰው ነፍሱ ከስጋው ስትለይበት ነፍሱ በቤቱ ምሰሶ *(ሉቱባ)* ላይ ስጋው እስኪቀበር ድረስ ተንሳፎ ይቆይና ስጋው ወይም አስክሬኑ ሲቀበር ነፍስ ወደ አምላኳ *(ዋዕ ቤዮ* /Waa'i beyyo/*)* እንደምትሄድ ይታመናል። ሀይሌ (1971፡14) *አሄራ* በሰማይ የተመቻቸ ሁኔታ እንዲገጥመው መሟላት ያለባቸውን አስፈላጊ ሆኔታዎች በጽሁፉ ዘርዝሯል። በዚህ መሰረት አንድ ሰው በሰማይ ጥሩ ኑሮ እንዲኖር ተከታዮቹን ነገሮች ማድረግ ይኖርበታል፤

1. በምድር ላይ እያለ ህገ ተፈጥሮን እና ህገ እግዚአብሄርን ወይም የዋዓን ህግጋት መታዘዝ ይጠበቅበታል።

2. አዋቂ ሰው ሲሞት ሊደረግለት የሚገባው:-
   2.1 የቀብር ስነስርአት እንደተፈጸመ አንድ በግ ወስዶ በስሰት እጀርባው ላይ በመውጋት ለፉጋዎች በመጣል *አንሽጣ* /anshshixxa /ስነስርአት ማድረግ፣
   2.2 ሟች ሴት ከሆነች *የአገታ*/aggaata/ ስነስርአት በሞተች በሶስተኛ ቀን አንድ በአድሜ የገፋች ላም በማረድ መፈጸም፣
   2.3 ሟቹ ወንድ ከሆነ *ቦሃ* /booha/ ወይም *ጋባ*/gaabba/ ስነስርአት በአመት ውስጥ አንድ ወይም ሁለት በሬ በማረድ ማዘጋጀት።

አንድ ሰው ሲሞት *ቦሃ/ጋባ/* (ተዝካር እንዳማለት ነው) የሚደረግበት አቢይ ምክንያት ሟቹ *ቦሃ/ጋባ/* እስከሚደረግበት ቀን ድረስ ነፍሱ በአለም ላይ ተንሳፎ፣ እረፍት ሳያገኝ እንደሚቆይ በሃይማኖቱ ስለሚታመንበት ነው። በስነስርአቱ በሟች መቃብር ላይ የደም መስዋእት ተደርጎ ወተት ይደፋበታል።

*የጋባ* ስነስርአት ሲደረግ ቀደም ሲል ለሟች ያለቀሰ ሁሉ ከእያንዳንዱ ጊቾ ይጠራና ድግሱን ይበላል። የአበላል ስርአቱም የሚከናወነዉ የእያንዳንዱን ጊቾ ተወካዮች በመጥራት ከታረደዉ ስጋ ድርሻቸዉን በመስጠት ይሆናል። የጊቾ ተወካይ በእለቱ መገኘት ባይችል እሱን የሚተካ *(ቤይ መንቾ)* ተጠርቶ ይሰጣል።

በሀዲያ ትውፊት ወይም በጥንታዊ ሀዲያ ስለህይወት ባለ ፍልስፍና *ዋዓ* (ፈጣሪ፣ አምላክ) አንድን ሰው ሲፈጥር አስቀድሞ ሁለት አካል እንደሚፈጥር ይታመናል፤ ወይም





ይታሰባል። ከሁለቱ አካላት አንዱ ሰማይ ላይ የሚቀመጥ ሲሆን ሌላኛው ምድር ላይ ተወልዶ የሚኖር ነው። የምድሩ አካል ሲሞት ነፍስ ከዚያ በመውጣት ሰማይ ላይ በተቀመጠው አካል ውስጥ ይገጥምና ወይም ይገባና የሰማዩን ኑሮ ይጀምራል። በመሆኑም ከነፍስ የተለየው ሟች ስጋ ትንሳኤ ሳያገኝ ለዘላለም በስብሶ ይቀራል የሚል ጠንካራ እምነት *በፈንዳነኖ* እምነት ተከታዮች አንዱ የሃይማኖታቸው መሠረት እንደነበረ ወይም እንደሆነ መረጃዎች አመልክተዋል።

በአጠቃላይ *ስለፈንዳነኖ* መነሻ ሲታሰብ ከሌሎች ሃይማኖቶች ለምሳሌ፣ ከእስልምና እና ከኦርቶዶክስ እንዳልሆነ እንደ አንድ መረጃ የሚወሰደው፣ *የፈንዳነኖ* ስርአት በመሰረቱ ከሀዲያ ብሄር ዉጭ የማያሳትፍ መሆኑ ነው። ይህም የሃማኖቱን ጥንታዊነት ወይም ቀዳማዊነት አመልካች ገጽታ ነው። እስልምና ወደ ኢትዮጵያ በሰባተኛ ክፍለ ዘመን ቢገባም የሀዲያ የሙስሊም ሱልጣኔት የተመሰረተው በአስረኛዉ ክፍለዘመን አከባቢ እንደሆነ የኢትዮጵያ ታሪክ ያወሳል። በሀዲያ ሁኔታ የእስልምናን ሃይማኖት ጅማሬ ስንመለከት ምንም እንኳዋን የሀዲያ ጥንታዊ ህዝብ ፈንዳነኖን ባይለቅም የሀዲያ መሪዎች እስልምናን ተቀብለዉ ቆይተዋል። በዚያን ጊዜ ከክርስቲና ሃይማኖት ይልቅ እስልምናን ቢያንስ የሀዲያ መሪዎች የተቀበሉት የእስልምና ሃይማኖት የፈንዳነኖን ሃይማኖት እንዲተው ስለማያስገድድ ነበር። ለዚህም ምክንያቱ የፈንዳነኖ የተወሰኑ ገጽታዎች ለምሳሌ፣ የጾም ስርአት ከእስልምና ጋር ተቀራራቢነት ስለነበረው ቢያንስ የሀዲያ የወቅቱ መሪዎች እኛ ሙስሊም ነን ብለው ለፈንዳነኖ ሃይማኖት ማቆያ እንደጭንብል ተጠቅመው ለማቆየት ረድቷቸዋል። ይህንን አስመልክቶ ሀይሌ (1971፡25) Bassete'ን

ጠቅሶ፣ የወቅቱ የሀዲያ መሪ ለእስልምና መሪ አህመድ ግራኝ ንግግር ሲያደርግ "አንተ ሙስሊም እንደሆንክ ሁሉ እኔም እንዳንተው ነኝ" ያለውን እንደማጠናከሪያ መጥቀስ ይቻላል፡፡ በእንደዚህ አይነቱ የመሪዎች ግንኙነት መነሻነት ሀዲያዎች እስልምናን እንደተቀበሉ ስለሚታሰብ እና ክልላቸውም በእስልምና አገዛዝ ስር ስለነበረ የራሳቸውን ሃይማኖት ውስጥ ለውስጥ ማስቀጠል ችለዋል፤ ምንም እንኳን የእስልምና ሃይማኖት በፈንዳነኖ የተወሰነ ተጽእኖ የፈጠረ ቢሆንም፡፡ በሁለቱ ሃይማኖቶች መካከል በነበረው ንክኪ ሳቢያም ከእስልምና ወደ ፈንዳነኖ የገቡ አንዳንድ ቃላትን መጥቀስ ይቻላል፡፡ ለአብነት፤ *አፍጥራ፣ አስተፍሪላ፣ ሶመኖ* የመሳሰሉት ቃላት የንክኪዉ አሻራዎች ናቸው (ሀይሌ 1971፡ 26)፡፡

በሌላ በኩል ከእስልምና ሃይማኖት ቀጥሎ የክርስትና ሃይማኖት አንዳንድ ቃላት እንደተቀላቀሉ ማየት ይቻላል፡፡ ለአብነት እንደ *ክቶሳ* /Kittoosa/ (ክርስቶስ ከሚለው) ፣ *ጌርግሳ* /Geergissa/ (ከጊዮርጊስ) ያሉ ቃላት ከትልቁ *ዋዓ* / Waa'a/ (አምላክ) ቀጥሎ ያሉትን አማልክትን ለማሳየት ጥቅም ላይ ውለዋል፡፡ በተጨማሪም የሀዲያ ሴት ስትወልድ በዙሪዋ ሆነዉ ሌሎች ሴቶች *ማራሜ ማሬ* /Maarame maare/ (ማርያም ማሪ) እያሉ የሚያሰሙት ድምጽ ወይም ጸሎት ከክርስቲና ሃይማኖት የተወሰደ መሆኑን መገንዘብ ይቻላል (ዝኒ ከማሁ፣ 25)፡፡

ቀደም ሲል *የፈንዳነኖ* ሃይማኖት ከእስልምና ሃይማኖት ጋር በተወሰኑ ገጽታዎቹ እንደሚመሳሰል የተጠቀመ ቢሆንም ሁለቱም ሃይማኖቶች ለየቅል እንደሆኑ በውስጣቸው ካሉት ባህርያት በመንቀስ ማሳየት ይቻላል፡፡ በሃይማኖታዊ





ስነስርአት ይሳተፉ ከነበሩ አዛዉንት ተጠይቀዉ በሰጡት ምላሽ፣ *ፈንዳነኖ* በሀዲያዎች ዘንድ ከሌሎች ሃይማኖቶች ለምሳሌ፣ ከእስልምናና ክርስቲና ቀዳሚ እንደሆነ ገልጸዋል፡፡ በሌላ አባባል *ፈንዳነኖ* ከአባት ወደ ልጅ ሲሸጋገር የመጣ እንጂ የእምነቱ ተከታዮች የነበሩት ከእስልምና ወይም ከሌላ ሃይማኖት ተከታይነት በመቀየር የመጣ እንዳልሆነም ያወሳሉ፡፡ የሃይማኖቱን ጥንታዊ ገጽታ ከሚገልጹ ነገሮች አንዱ *በፈንዳነናና* በኦሪት ዘመን በነበረዉ የአምልኮ ስነስርአት መካከል የመስዋእት አቀራረብ ስርአት መመሳሰል ነዉ፤ ያዉም የእንስሳትን ደም በማፍሰስ መከናወኑ ነዉ፡፡ በጥቅሉ፣ ስፊ ስርጭት የሌላቸዉ ባህላዊ እምነቶች በባህርያቸዉ ከሌላዉ ሃይማኖት የቀዳሚነታቸዉ (የጥንታዊነታቸዉ) ሁኔታ ጎልቶ እንደሚታይ ማሰብ ይቻ ላል፡፡ ይህ ሲባል ግን እስልምና ወይም ሌላዉ ሃይማኖት በፈንዳነኖ ላይ አንዳች ተጽእኖ አልፈጠረም ማለት አይደለም፤በሃይማኖቶቹ መካከል በንክኪዉ ምክንያትና በጊዜ በሂደት የሃይማኖታዊ ስርአት ተመሳሳይነት ወይም መወራረስ ሊታይ ይችላልና፡፡ ጠቅለል ባለ አነጋገር ሁለቱን ሃይማኖቶች (እስልምናና ፈንዳነኖን) የተለየ የሚያደርጉ ባህርያትን እንደሚከተለው መቃኘት ይቻላል፡፡

- *በፈንዳነኖ* የጾም ስርአት እንዲሳተፉ የሚጠበቁት ወንዶች ሲሆኑ ሴቶችን አይጨምርም፤ በእስልምና ግን ወንዶችም ሆኑ ሴቶች ይጾማሉ፡፡
- *ፈንዳነኖ* የሰላት ስግደት ስርአት የለውም፤ ይልቁን ንጋት ላይ እና ምሽት ላይ ወደ ሰሜን እና ምስራቅ በማጉንበስ ለፈጣሪያቸው ጸሎት ያቀርባሉ፡፡ እስልምና ላይ ግን በቀን አምስት ጊዜ የስግደት ሰአት አላቸዉ፡፡

- *ፈንዳና፡ ፈንዳኖ* ስለመሆናቸው የሚገልጹት ጸጉራቸው ላይ *ማበጠሪያ (ሹዳቃ /Shuddaqqa/)* በመሰካት፣ *መፋቂያ* ጀሮ ላይ በማኖር ሲሆን የእስልምና ሃይማኖት ተከታዮች ግን በራሳቸው ላይ በሚያደርጉት ጥምጣምና ቆብ ተለይተው ይታወቃሉ።
- *ፈንዳኖ* ሃይማኖታዊ ስርአታቸውን የሚመሩበት መጻህፍት የሌላቸው ከመሆኑም በላይ ውስን የአምልኮ ማእከል የላቸውም። በአንጻሩ ሙስሊሞች ሃይማኖታቸውን የሚከተሉበት መጽሀፍ ያላቸው ሲሆን በተጨማሪም ውስን የአምልኮ ስፍራ ወይም መስጊድ አላቸው።

በአሁኑ ጊዜ *ፈንዳነኖ* እየሞተ ያለ ሃይማኖት ሲሆን ሃይማኖቱን የሚከተሉ ጥቂት ቤተሰብ በባዳዋቾ አካባቢ እስከአሁን አሉ። ከእነሱም ውስጥ *ፈንዳነኖን* የሚያራምዱት በአብዛኛው በእድሜ የገፉ አዛውንት ናቸው። ይህም ሃይማኖቱ በመጥፋት ጫፍ ላይ እንዳለ አመላካች ነው። ለዚህም አቢይ ምክንያቱ በአሁኑ ወቅት፣ ቀደም ካሉ አመታት ጀምሮ አብዛኛው የሀዲያ ብሄረሰብ በዋናነት የክርስቲና (በተለይም የፕሮቴስታንት) ሃይማኖት እና በተ ወሰነ ደረጃ የእስልምና ሃይማኖት ተከታይ ወደ መሆን በመቀየራቸው ነው። በሌላ በኩል የሀዋሪያዊት፣ የኦርቶዶክስ፣ የካቶሊክ እና የአድቬንቲስት ሃይማኖት *በፈንዳነኖ* ላይ ያስከተ ለዉ ተጽእኖ በቀላሉ የሚታይ አይደለም። *ለፈንዳነኖ* ሃይማኖት መጥፋት እንደትልቅ ምክንያት የሚጠቀሰዉ የፕሮቴስታንት ሃይማኖት እጅጉን መስፋፋት ሲሆን፣ ቀደም ባሉት ዘመናት በተለይም *ከፈንዳነኖ* ወደ ክርስቲና ሽግግር ይደረግ በነበረ ወቅት የፈንዳነኖን ሃይማኖት አውጋዥ ከሆኑና





በቤተ ክርስቲያናት ይዘመሩ ከነበሩ ዝማሬዎች ውስጥ የተወሰኑ ስንኞችን እንደ ምሳሌ መጥቀስ ይቻላል።

*ምሳሌ፣*

| | |
|---|---|
| <u>እ አንጋ አመዴ ዩሱሳ</u> 2x<br>I anga amade yesuusa | እጀን ያዘኝ ኢየሱስ |
| ክ አንጊ ኡባ ብኦምቤእሳ<br>Ki angii ubaa bi'oombee'issa | ከእጅህ ወድቄ እንዳልጠፋ |
| እ ፎዕል ሀደራ ኣኤ ዩሱሳ<br>I foo'll hadara aa'e yesuusa | ነፍሴን አደራ ኢየሱስ |
| ጃራ እዶታ ቄሳሞ<br>Jaara idoota qeessaammo | ጃራ እና እዶታ አሪቄአለሁ |
| ጋዋ ዊሪሲማ ኡራሞ<br>Gaawwa wiriissimma uraammo | ጋያ ማጨሱን ትቻለሁ |
| አት ሰቦ ህርሞ ሰባሞ<br>At sabbo hirimo sabaammo | አንተ የምትጠላውን<br>እርም ጠልቻለሁ |
| እዋዓ አን ኬሴ አመዕኖሞ<br>I waa'a an keese ama'nnommo | አምላኬ ሆይ እኔ<br>አንተን አምንሀለሁ |
| ኤሴ ኡንጅትቴ ሆሮኤም<br>Eese uunjittitte horeme | ፈጽመህ አትጣለኝ እባክህ |

ከፍ ሲል በቀረበዉ አጭር የሀዲይሳ መዝሙር ዉስጥ፣ በሀዲያ ጥንታዊ ሃይማኖት ላይ የፕሮቴስታንት ሃይማኖት ያሳደረዉን ተጽእኖ መመልከት ይቻላል። በተለይም ቀደም ሲል የፈንዳነኖ ሃይማኖት ዉስጥ የተጠቀሱት *ጃራ* እና *እዶታ* የተባሉ መናፍስት እና ከሃይማኖቱ ጋር ተያያዥነት የነበረዉ *ጋያ* ማጨስ በፕሮቴስታንት ሃይማኖት መወገዛቸዉን መዝሙሩ ያሳያል። ከፈንዳነኖ ወደ ፕሮቴስታንት ሃይማኖት የተለወጡት ሀዲያዎች አምላካቸዉ አይወድም ብለዉ የሚያስጿቸዉን ሱሶች እና ሌሎች እርሞች መተዋቸዉን

አዉጀዉ፣ አምላካቸዉን ፈጽመህ አትጣለኝ፣እንዳልወድቅ ያዘኝ፣ በማለት መማጸናቸዉንና ህይወታቸዉን ለእሱ ለመስጠት ቃል መግባታቸዉን ዝማሬዉ አሳይቷል። ይህም ከሃይማኖት አንጻር የፍልስፍና ለዉጥ ማድረጋቸዉን ያሳያል። ተከታዮቹ ስንኞችም የፈንዳኖ ሃይማኖት ዳግም እንዳይታይ የሃይማኖቱ ተከታዮች መፈለጋቸዉን የሚያመለክቱ ናቸዉ:: በመቀጠል ደግሞ ከአንድ መዝሙር የተወሰደዉን ቅንጫቢ ይመለከቷል::

| | |
|---|---|
| *ኦድ ዋሮኔ ኦድ ዋሮኔ* | *ዳግም አይምጣ ዳግም አይምጣ* |
| *ለዕም ኮሬ ክድ ደበዕሎኔ* | *ለሁለተኛ ጊዜ ወዲህ አይመለስ* |
| *ገለት ቤዕ ዋመኔ አዶ ዱንም* | *በምስጋና ቤስ መቃብር ላይ ወተት መድፋት* |
| *ጎጋል ኡቱበኔ ቡሮ ለብም* | *በደረቅ ምሰሶ ላይ ቅቤ መቀባት* |
| *ቦሮጂኒና በላ ኡዊሚ* | *ለጠንቋይ በላ መስጠት* |
| *ኦድ ዋሮኔ ኦድ ዋሮኔ* | *ዳግም አይምጣ ዳግም አይምጣ* |
| *ለዕም ኮሬ ክድ ደበዕሎኔ* | *ሁለተኛ ጊዜ ወዲህ አይመለስ* |

እላይ በቀረበዉ የዝማሬ ቅንጫቢም የፈንዳኖ ሃይማኖት አካል ከሆኑት ለምሳሌ፣ መቃብር ላይ ወተት የመድፋት፣ ምሰሶ ላይ ቅቤ የመቀባት፣ የዛር መንፈስ ላረፈበት ግለሰብ ስጦታ የመስጠት የመሳሰሉትን ስነስርአቶች በምሬት መወገዛቸዉ ኦድ ዋሮኔ (ዳግም አይምጣ) በሚል አዝማቹ ተመልክቷል:: በአጠቃላይ ክእንዲህ አይነቱ አመለካከትና ሃይማኖቱን ከማዉገዝ ተግባር ተነስቶ በአሁኑ ጊዜ ሃይማኖቱ በመጥፋት ጫፍ ላይ መድረሱን የተለያዩ ቃላዊና ጽሁፋዊ መረጃዎች ያስረዳሉ::





ሀዲያዎች ከፈንዳኖ ወደ ክርስቲና (ፕሮቴስታንት እምነት) የተሸጋገሩበትን ሁኔታ በሚመለከት ጥቂት ሀሳቦችን ማንሳት ተገቢ ነዉ:: የተለያዩ መረጃዎች እንደሚያመለክቱ የፕሮቴስታንት ሃይማኖት ወደ ሀዲያ የገባዉ በ1927 ሲሆን ወቅቱ ክርስቲና የመንግስት ሃይማኖት የነበረበት ጊዜ ነበር:: በዚህ ጊዜ (በሀይለ ስላሴ የአገዛዝ ዘመን) ህዝቡ የመንግስት ሃይማኖት የነበረዉን የኦርቶዶክስ ክርስቲና ሃይማኖት እንዲቀበሉ የህግ ግፊትና ተጽዕኖ ሲደረግ የነበረ ቢሆንም የሀዲያ ህዝብ ሃይማኖቱን ለመቀበል ፈቃደኛ አልነበረም:: ለዚህም ምክንያቱን አስመልክቶ ላጵሶ (1982:98) እንደሚከተለዉ ይገልጻል::

> *... የመንግስቱን ሀይማኖትና ፕሮፖጋንዳ እምቢ በማለት በኋላ ከዉጭ በሚሲዮናዉያን አማካይነት የመጣዉን የፕሮቴስታንትና የካቶሊክ ሃይማኖቶች በፈቃዳቸዉ ወሰዱ:: እነዚህ ብሄረሰቦች የመንግስቱን ሃይማኖት እምቢ ያሉበት ዋና ምክንያት የዚህ ሃይማኖት ክፍል በብሄረሰቦቹ በመሬት ጉዳይ ላይ በመግባቱ ሲሆን ከዉጭ የመጡ ሃይማኖቶቹን የተቀበሉት ዋና ምክንያት ደግሞ ሃይማኖቶቹ ያመጡ ሚሲዮናዉያን በመጠንም ቢሆን እንኳን ለአካባቢዉ ትምህርት፣ መድኃኒትና አንዳንድ ማህበራዊ አገልግሎቶች ይዘዉ ስለመምጣታቸዉ ነዉ::*

ከፍ ሲል በተጠቀሰዉ ሁኔታ በተለይ በሱዳን ኢንተርዮን ሚሺን አማይነት የፕሮቴስታንት ሃይማኖት ወደ ሀዲያ የገባ ሲሆን ጣሊያን በ1935 ላይ ወደ ኢትዮጵያ ሲገባ ሚሲዮኖች ከአገር የመዉጣት ፈተና አገጋጥሟቸዉ ነበር:: እንደ ላጵሶ (1982:98) አገላለጽ ለሃይማኖቱ ትምህርት መቀጠል በወቅቱ ከሚሲዮናዉያኑ ባማርኛ ፊደል ንባብና ጽህፈት የተማሩ ወጣቶች ስለነበሩ የወንጌል ስብከትና የመንደር ትምህርት ሊጀምሩ መቻላቸዉ ነዉ::

ከነዚህም ወጣቶች ሽጉጤ ዳዳ፣ ሰብሮ ወሶሮ፣ ረጠቦ አመሴ እና አባጎሌ ኑነሞ[73] ይጠቀሳሉ::

[73] አባጎሌ ኑነሞ በ1894 ተወልደዉ እስከ 2001 የኖሩ ሲሆን፣ ከጣኦት አምልኮ ተከታይነት ወደ ፕሮቴስታንት ሃይማኖት ከተለወጡ የመጀመሪያዎቹ አማኞች አንዱ ነበሩ:: አባጎሌ በህይወት ዘመናቸዉ የቃለህይወት ቤተክርስቲያንን ከመምራት አልፈዉ በመንግስታዊ የአመራር ጉዳዮች ተሳትፈዋል:: በ1940ዎቹ እና 50ዎቹ በነበረዉ የወንጌላዉያን ክርስቲያኖች ስደትና እስራት እስከ አሰላ ድረስ ለአምስት አመታት በበቅሎአቸዉና በእግራቸዉ እየሄዱ ፣ጠያቀዋል፤ስለእነሱም ተከራክረዋል:: ከዚህም በተጨማሪ አባጎሌ በሀዲያ የዘመናዊ ትምህርት ጅማሬ ላይ ትልቅ ሚና ተጫዉተዋል:: ከእነዚህ ትምህርት ቤቶች ዉስጥ በሆሳዕና ከተማ አቅራቢያ የነበረዉ ኤስ አይ ኤም ቦቢቾ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት ተጠቃሽ ነዉ:: ትምህርት ቤቱ ቆይቶ የህዝብና የመንግስት ወደ መሆን የተሸጋገረ ሲሆን፣ በወቅቱ የተሰያዩ ባለሙያዎች፣ ምሁራንና አምባሳደሮች ወዘተ... እንዲፈጠሩ ምክንያት ሆኗል:: ከዚህም ባሻገር አባጎሌ በደርግ ዘመን የሆሳዕና ሆስፒታል ሲሰራ ከሀዲያና ከከምባታ አማኞችና የመንግስት ሰራተኞች እና ከሌሎች አካባቢዎች በወቅቱ 12,000 የአሜሪካን ዶላር በማሰባሰብ ለስራዉ ከፍተኛ አስተዋጽኦ አበርክተዋል:: በጥቅሉ አባጎሌ ከወንጌል ሰባኪነታቸዉ በሻገር በማህበረ-ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች ላይ ባበረከቱት አስተዋጽኦ ምንጊዜም ሲታወሱ ይኖራሉ (ድርሻዬ፡ 2004)::





# ክፍል 5፤በሀዲያ ህዝብ ከልደት እስከ ሞት ያሉ ወጎች

## 5.1. የልደት አከባበር ስርአት

ልጅ መዉለድ በሀዲያ ብሄረሰብ ዘንድ ጋብቻን የበለጠ ትርጉም እንዲኖረው የሚያደርግ ጉዳይ ነው:: በመሆኑም ወላጅ፣ ልጅ ሚስት ሲያገባ የተጋዳኞቹን ልጅ መውሰድ በናፍቆት ይጠባበቃል:: የልጁ ሚስት ነፍሰ ጡር ስትሆን ደግሞ የባሏ ቤተሰብ ፍቅርና እንክብካቤ ጠንካራ ሆኖ ይቀጥለል:: ነፍሰ ጡርዋ የመውለጃዋ ጊዜ ሲቀርብ የተለያዩ ዝግጅቶችን ታደርጋለች:: ከነዚህ ውስጥ ቅቤ፣ ዱቄት እና ከእንሰት ከባ ውስጥ የሚገኝ ጥጥ መሳይ ስስላሳ ክር ማሰናዳት ይጠቀሳል:: ይህም ጥጥ መሳይ ክር በሀዲይሳ *ሀላማ*[74] /ዛንዛ/ ጃንጃ በመባል ይታወቃል:: ባልም በበኩሉ ለአራስ አስፈላጊውን ዝግጅት ያደርጋል:: ሚስት የመውለጃዋ ጊዜ ሲቃረብ በተለይም የመጀመሪያ ልጇን ልትወልድ ስትል አብዛኛውን ጊዜ ወደ ወላጆችዋ ቤት ትወሰዳለች::

ምጥ ሲጀምራት እቤት ውስጥ በምድጃ ዙሪያ እሳት እንዲነድ ይደረግና ቤቱ ይሞቃል:: በእድሜ ገፋ ያሉች የልምድ አዋላጅ ትጠራና በዘር ወይም በጋብቻ የሚዘመዱ ሴቶች ተሰብስበው ከበዋት ማዋለድ ይጀመራል:: በምጡ ሂደት የምታምጠው ሴት ጽንሱን ለመግፋት ከምታሰማው የጣር ድምጽ ጋር ሴቶቹ ድምጻቸውን እኩል በማሰማት ያጅቧታል:: ይህ የሚደረገው የምታምጣውን ሴት ለማበረታታት ሲባል ነው::

[74] *ሀላማ(* hallaamma*)* ሴቶች ፣ ለሚወለዱ ህጻናት እንደማቀፊያ የሚጠቀሙበት ጥጥ መሳይ ነገር ሲሆን ህጻናቱ ሲሸኑ እንደ ንጹህ መጥረጊያ ጨርቅ ይገለገሉበታል:: ሀላማን ሴቶች ከመዉለዳቸዉ በፊት ናትራ እና ናቃ በሚባሉ ቅመማ ቅመሞች አሸተዉ ማስሮ ዉስጥ ያስቀምጣሉ፤ ይህም ህጻናቱን ሲያቅፉ መልካም ጠረን ያላብሳል::

በዚህ ሂደት ወንዶች እቤት ውስጥ እንዲሆኑ አይፈቀድላቸውም። ወንዶቹ እደጅ ቁጭ ብለው ጋያ[75] እያጨሱ ፈጣሪቻቸውን *(ዋዓን)* እየተማጸኑ የልጁን መወለድ ወይም የነፍስ ጡሯን በሰላም መገላገል በጉጉት ይጠባበቃሉ።

የልጅቷ እናትና ሴቶቹ መቀነታቸውን (በህዲይሳ *ሰበታን* /sabbata/) ጠበቅ አድርገው እጆቻቸውን እየታጠቡ ለሰላማዊና ፈጣን መገላገል አምላክን ወይም *የእዶታን*[76] /idoota/መንፈስ ይማጸናሉ። በዚህ ሂደት ህጻን ሲወለድ የህጻኑ መወለድና የተወለደው ህጻን ጾታው እውጭ ለሚጠባበቁ ወንዶች የሚበሰረው በእልልታ ነው። ጾታው የሚነገረው በሴቶቹ በተከታታይ በሚሰማዉ የእልልታ ቁጥር ወይም ድግግሞሽ ነዉ። የእልልታዉ ድግግሞሽ ከአካባቢ አካባቢ ልዩነት ያሳያል። በሶሮ ሀዲያዎች የተወለደው ህጻን ጾታው ወንድ ከሆነ አራት ጊዜ እልል ሲባል፣ ሴት ከሆነች ደግሞ ሶስት ጊዜ እልል ይባላል። በኮንተብ[77] ሀዲያዎች ባህል መሰረት ህጻኑ ወንድ ከሆነ አምስት ጊዜ የእልልታ ድምጽ ሲያሰሙ፣ ሴት ከሆነች ደግሞ ሶስት ጊዜ የእልልታ ድምጽ ያሰማሉ። በሌላ በኩል በባደዋቾ ሀዲያዎች ደግሞ የሚሰማው እልልታ ድምጽ ለወንድ ህጻን ስድስት ጊዜ ሲሆን፣ ለሴት ህጻን አራት ጊዜ ይሆናል። የሁሉንም አካባቢ የሚያመሳስለው፣ የወንድን ጾታ ለመግለጽ የሚሰማው የእልልታ ቁጥር የሴትን ጾታ

[75] ክክርስቲና በተለይም ከፕሮቴስታንት ሃይማኖት መስፋፋት የተነሳ በአሁኑ ጊዜ ጋያ ማጨስ እየቀረ መጥቷል።

[76] *እዶታ* ሴቶችን በተለይ በምጥ ጊዜ ይረዳል ተብሎ የሚታመን መንፈስ ነው።

[77] *ኮንተብ* የሚለዉ ቀደም ሲል በነበረዉ መዋቅር ከሀዲያ ዞን ወረዳዎች አንዱ የነበረ ሲሆን፣ በአሁኑ ወቅት ምሻና ግቤ ወረዳ ተብሎ ተዋቅሯል።





ለመግለጽ ከሚሰማው በድግግሞሽ የሚበልጥ[78] መሆኑ ነው። ሴትዮዋ እንደተገላገለች የእንግዴ ልጅ (በሀዲይሳ *አማ* /Ama/ ወይም *ለሰቅ ሉዋ* /Lasa'qq luwwa/) እስኪመጣ እቤት ሆነው ያጀቧት ሴቶች አምላካቸውን መማጸናቸውን ይቀጥላሉ። ምክንያቱም በባህሉ የእንግዴ ልጅ እስካልመጣ ድረስ የወሊዱ ሂደት ገና እንዳልተጠናቀቀ ይታሰባልና። የእንግዴው ልጅ እንደመጣ በዱቄት ተሸፍኖ በቤቱ አንድ ጥግ ይቀበራል። ባሏ የአማቹ ቤት እንደ ደረሰ የተወለደው ህጻን ጾታ ይነገረውና ሚስቱን ይሰማታል። ከዚያም ለወሊዷ ጊዜ ተብሎ የተዘጋጀውን ኮርማ ወይም በሬ ይታረድና የተለየ መጠጥ ከበሬው ደም፣ ከቅቤና ከትኩስ ወተት ጋር ተቀላቅሎ ለወላጇ ወይም ለትኩስ አራስ ይሰጣታል። ደም ተቀላቅሎ የሚሰጥበት ምክንያት አራሷ በወሊድ ወቅት ያጣችውን ደምና ጉልበት እንዲተካ ታስቦ ነው።

በሰላም የተገላገላችው እመጫት (አራስ) በሶስተኛ ቀኗ የቅርብ ጓደኛ በሆኑ የመንደሯ ሴቶች ወይም አማቷ ዉሃ አሙቀው ያጥቧታል። ይህ ስርአት በባህሉ *ወበጣ*[79] /Wobaxa/ በመባል ይታወቃል። አጠባው እንዳበቃ ከስንዴ ዱቄት የሚዘጋጀውን ቅንጬ መሳይ ምግብ አሰናድተው በቅቤ ሰርተው ይመገባሉ። የምግቡ አይነት በሀዲይሳ *ቀዕል-በሳ* /Qa'll-bassa/ (በአማርኛ የአራስ በሶ) የሚል ስያሜ አለው። ይህንን ምግብ በባህሉ

[78] በሀዲያ ባህል የሴት ልጅ መወለድ ጉልቶ ባያጠላም ወንድ ልጅ ሲወለድ ግን የበለጠ ደስታ በወላጆች ላይ ይንጸባረቃል። ምክንያቱም የዘር ግንድ ቀጣይነት የሚኖረው /የሚረጋገጠዉ/ ወይም ተከታይ ትዉልድ የሚጠራው በወንድ ልጅ ዘር በመሆኑ ነው።

[79] *ወበጣ፣* ወንዝ ዳር አካባቢ የሚያድግ ተክል ሲሆን አራስ ሴቶች ከዉሃ ጋር አፍልተዉ በወበጣ ስነስርአት መፈጸሚያ ቀን የሚታጠቡበት ተክል ነዉ፤ ለአራስ የሚደረግ ስነስርአት ስያሜም የተወሰደዉ ከዚሁ ተክል ስያሜ ነዉ። ይህም ተክል በተፈጥሮዉ የመድሃኒትነት ፋይዳ እንዳለዉ ይታመናል።

ወንዶች እንዲመገቡ አይፈቀድም፣ ምክንያቱም ሴቶች ደካማ እንደሆኑ ስለሚታመንና ያን ምግብ ወንዶች ከተመገቡ እንደ ሴቶች ደካማ ይሆናሉ የሚል አስተሳሰብ በመኖሩ ነው፡፡

ወጣቷ ሴት እናት ከሆነች በሁዋላ የእዶታን ስነስርአት ማክበር ትችላለች፡፡ የእዶታ ስርአት አዘገጃጀት በሚከተለው ቅደም ተከተል ይከናወናል፡፡ ስነስርአቱን አክባሪዋ ሴት መሳተፍ የሚገባቸውን የጐረቤት ሴቶች በሙሉ ትጋብዛቸዋለች፡፡ ሴቶቹ በስነስርአቱ ቀን ሲመጡ ጋባዥዋ አስቀድማ አስፈላጊውን ቁሳቁስና ሌሎች እንደ ቅቤ፣ የተቦካ ገብስ እና የመሳሰሉትን ነገሮች ታሰናዳለች፡፡ ለስነስርአቱ አስፈላጊዎቹ ነገሮች ተዘጋጅተው ለሴቶች ከተሰጣቸው በሁዋላ በበአሉ ዋዜማ በዋናነት ቡሎ /Bullo/ የተበላውን ልዩ ምግብና መጠጥን ቦርዴ (በሀዲይሳ፣ አይዳራ ወይም ሻዕሜታ) ያዘጋጃሉ፡፡ በዋዜማው ሁሉም ተጋባዥ ሴቶች በተገኙበት የወትሮውን ምግብ የሚበላ ሲሆን *ቡሎ* እና ሌሎች መጠጦች በበአሉ ቀን ብቻ የሚጠጣ ይሆናል፡፡ የግብዣው ስርአት እንዳበቃ፣ ሴቶቹ *በሀ* /Baha/ የተሰኘውን ጭፈራ ይጨፍራሉ፡፡ *በሀ* የእዶታ ጭፈራ ሲሆን ሴቶቹ ወደ ላይ ዘለል- ዘለል እያሉ፣ ዳሌያቸውን በሁለት እጃቸው መታ - መታ እያደረጉ፣ *"አሀ - በሀ"... "አሀ - በሀ"* /Aha- baha --- Aha- baha/ በማለት የሚጨፍሩት የጭፈራ አይነት ነው፡፡ በጭፈራው ሂደት የእዶታ ስነስርአት አክባሪ ሴት በተጋባዥ ወዳጆቿ ትታጀባለች፡፡ ጭፈራው እንዳበቃ የተረፈው ምግብ *(ቡሎ)* ለበአሉ ተሳታፊ ሴቶች ተካፍሎ ይሰጣቸዋል፡፡

ከአራስ ዘመዶች ከእህቷ ወይም ከአክስቷ ወይም ልጅቱን ካገባው አማች ወገኖች የሚደረግ ድግስ እና ጥየቃ ሌላው የወሊድ ስርአት ነው፡፡ ይህም *አዲሳ* /Adissa/ ተብሎ





ይጠራል፡፡ ለዚህም ትኩስ ወተት፣ የበግ ሙክት፣ የገብስ ዱቄት፣ ከተልባና ከወተት ተበጥብጦ የሚዘጋጅ መጠጥ (ሻዕሜታ) እና ልዩ ልዩ የምግብ አይነቶች ይዘጋጃሉ፡፡ ከዚያም አራሷን ለመጠየቅ እንደሚመጡ ለቤተሰብ ይነገራል፡፡

ጠያቂዎቹ በእለቱ ወደ ተጠያቂዋ ቤት ሲቃረቡ መቃረባቸውን የሚገልጽ ባህላዊ ዘፈን "አያዶ- መኔዶ -መኔድ አያዶ" /Ayyadoo- manneddoo- Manned ayyaddo/ የሚለዉን በከፍተኛ ድምጽ ይዘፈናል፡፡ እንደደረሱም የባሏ ቤተሰብ ለእንግዶቹ መልካም አቀባበል ካደረገላቸው በሁዋላ፣ ወደ ተዘጋጀላቸው እልፍኝ ይወስዳሉ፡፡ ጥቂት እንዳረፉ ከእንግዶቹ መካከል የተወሰኑት ወደ እመጫቷ ጓዳ ለመግባት ካስፈቀዱ በሁዋላ ወደ ጓዳ ይገባሉ፡፡ በዚያም በእመጫቷ እናት ላይ ቅቤ ይቀባሉ፡፡ ከዚያም በሁዋላ እንግዶቹ ወደ ተዘጋጀላቸው ቦታ በመመለስ ከተቀመጡ በሁዋላ የምግብና የመጠጥ ግብዣ ይደረጋል፡፡ ግብዣው እንዳበቃ፣ በተቀባዩ ቤተሰብ የተዘጋጀው ሙክት ወይም በሬ ቀርቦ ከእንግዶቹ መካከል አንድ ሰው ተወክሎ እንዲባርክ ይደረጋል፡፡ ከከብቱ እርድ በሁዋላ ቁርጥ ስጋና ክትፎ ተዘጋጅቶ የሚበላ ሲሆን የቀረው ተጠብሶና ተቀቅሎ ይቀርብና እንግዶቹ እንደየፍላጐታቸው ይጋበዛሉ፡፡

እንግዶች በዚህ ሁኔታ እየተስተናገዱ አድረው በሁለተኛ ቀን በጧቱ ለመሄድ ፍቃድ ቢጠይቁም ወዲያው አይሸኙም፡፡ እስከ ከሰአት ድረስ ግብዣውና ጨዋታው ይቀጥልና ከሰአት በሁዋላ ይሸኛሉ፡፡ እንግዶቹ እንደተሰናበቱም ጐረቤቶች ከልጅ እስከ አዋቂ የተጋባዥነታቸውን ተራ ይወስዳሉ፡፡ በዚህ ጊዜ ለጐረቤቶች አዲስ ምግብ ማዘጋጀት አይጠበቅም፡፡ እንግዶቹ ይዘውት የመጡትን ምግብ እንዲመገቡ ይደረጋል፡፡ ይህ በእንግዶች የመጣው ልዩ ምግብ *አዲሳ* በመባል ይታወቃል፡፡

የወላጇ የእመጫትነት ጊዜ (በሀዲይሳ *እራነኖ* /Iraannano/) ከሁለት እስከ ሶስት ወራት ይጠናቀቃል፡፡ ወላጅ አባትና እናት አዲስ ለተወለደው ልጃቸው ስም ይሰይሙና እነርሱም በመጀመሪያ ልጃቸው ስም ይጠራሉ[80]፡፡ ይህ አጠራር ወጣት ተጋቢዎቹ ያገኙትን አዲስ የአባትነት ወይም የእናትነት ማእረግ አመልካች ሆኖ ያገለግላል፡፡ እመጫቷ *የእራነኖ* ጊዜ ከማብቃቱ በፊት እመጫት ስለመሆኗ ልዩ ምልክት ሆኖ የሚያገለግል *ቀናፋ*[81] /Qanaafa/ ከሴት ጓደኞችዋ በስጦታ መልክ ይሰጣታል፡፡ ከጸጉሯም *ቀናፋዋ* አይሰይም፡፡ ይህንን ምልክት ያዩ ሴቶች ሁሉ እመጫት መሆኗን ስለሚያውቁ በሄደችበት ሁሉ ቅቤ ይቀቧታል፡፡ *ቀናፋዉ* ጸጉሯ ላይ የሚቆይበት ጊዜ ርዝመት በተወለደዉ ህጻን ጾታ ይሰያያል፡፡ የተወለደው ህፃን ወንድ ከሆነ ለስድስት ወር ሲደረግ፣ ሴት ከሆነች ደግሞ ለአራት ወር ይደረጋል፡፡ ለዚህ ስርአት ማብቂያ *የቀናፋ መፍቻ* ቀን ተዘጋጅቶ ይደገስና የመንደሩ ሴቶች ተሰብስበው ከበሉ በሁዋላ ቅቤ ቀብተዋት ይመርቋታል፡፡ የዚያን ጊዜም የእመጫትነት ጊዜ ማብቂያ ይሆናል፡፡

## 5.2. የሰዉ ስም አወጣጥ እና አጠራር

ስም የተሰያሚውን ባህል፣ ቋንቋ፣ የአኗኗር ሁኔታ፣ አካባቢ፣ ስለሀይወት ያለውን አተያይ፣ እምነቱ'ንና ወጉን የመግለጽ አቅም አለው፡፡ በሀዲያ ልማድ (tradition) ለአንድ አዲስ ለተወለደ ህጻን ወላጆች ለነበሩበት አልያም ላሉበት ሁኔታ ያላቸውን ስሜት የሚገልጹበትን ስያሜ መስጠታቸው የተለመደ ነው፡፡ ለህፃናት ስያሜ የሚሰጠው ህፃኑ ከተረገዘበት

[80] ለተጨማሪ ማብራሪያ በ5.2. ስር የሰዉ ስም አወጣጥና አጠራር በሚል ርእስ የቀረበዉን ሀተታ ይመለከቷል፡፡

[81] *ቀናፋ*፤ ከእንጨት ተስተካክሎ የተሰራ በአራስ አንገት ላይ የሚጠለቅ ነገር ነዉ፡፡ ይሀም አንዲት ሴት አራስ እንደሆነች አመልካች ነዉ፡፡





እስከሚወሰድበት ቀን ድረስ ወላጆች ያለፉበትን የህይወት ጉልህ አጋጣሚዎች መሰረት በማድረግ ነው፡፡ በሀዲያ ባህል፣ የሰው ስም የሚሰየመው አብዛኛውን ጊዜ ህጻኑ ከተወሰደበት ጊዜ አንስቶ እስከ ሁለት ወር ባለ ጊዜ ነው፡፡

በሀዲያ ባህል የሰው ስም ሲሰየም ያለፍች አይሰጥም፡፡ በሌላ በኩል አንድ ሰው ለልጁ ስያሜ ሲሰጥ ከሰያሚው ማንነት ጋር ወይም ካለበት ተጨባጭ ሁኔታ ጋር በማዛመድ ሲሆን ከሉ ማንነት ጋር የማይጣጣም'ን ስም ስሙ ደስ ስላለው ብቻ ቢሰይም እ'ንደነውር ይቆጠራል፡፡ ለምሳሌ፣ አንድ ሰዉ በጦር ሜዳ ውሎ ሳይሳተፍ ጀግንነት አመልካች ስሞች'ን ለልጁ ቢሰይም ተቀባይነት የማይኖረዉና ይልቁንም ሰያሚዉን የሚያስነቅፍ ይሆናል፡፡

በባህሉ ሰዎች ከህጻን እስከ ሽማግሌ የሚጠሩባቸው ጥቅል ሰያሜዎች /የእድሜ ዘመን ስያሜዎች/ አሉዋቸው፡፡ ይህም ቀጥሎ በቀረበዉ ሰንጠረዥ እንደሚከተሰዉ ቀርቧል፡፡

| እድሜ / እመት/ | ጾታ | | የእንግልዝኛ ፍች |
|---|---|---|---|
| | ወንድ/Goona | ሴት/Meento | |
| 0-4 | ጪልቾ Ciilichcho | ጪልቼ Ciilichche | Baby |
| 5-11 | ኦሽቾ Ooshshichcho | ኦሽቼ Ooshshichche | Child |
| 12-17 | ቤቶ Beeto | ለንድቾ Landichcho | Boy/Girl |
| 18-29 | ወራድቾ Woraaddichcho | ባጃሜ Baajaame | Youth |
| 30-59 | ሀርዴኤ Harde'e | ሀርዴኤቴ Harde'ette | Adult |
| >60 | ሎመንቾ Lommancho | ሎመንቼ Lommanche | Elderly |

ከፍ ሲል የቀረበው ሰንጠረዥ፣ ሰዎች በየእድሜ እርከኖቻቸዉ ሲያልፉ የሚኖራቸውን ስያሜ የሚያመለክት ነው። በእነዚህ ደረጃዎች ከልደት እስከ እርጅና የቀረቡ ስያሜዎች የጋራ መጠሪያዎች ናቸዉ። አንድ ህጻን ልጅ ከተወለደበት እስከ አራት አመቱ ጪልቾ (ለወንድ) ጪልቺ (ለሴት) ተብሎ ሲጠራ፣ ከ5-11 አመት ኦሾ (ለወንድ) ኦሼ (ለሴት) ተብሎ ይጠራል። እነዚህ ከእንግሊዝኛ 'baby' እና 'child' ጋር እንደየቅደም ተከተላቸዉ አቻዊ ፍች አላቸው። በሁሉም የእድሜ ክልል ሁለቱም ጾታዎች የየራሳቸው የሆነ አጠራር አላቸው። በሌላ በኩል ሰዎች የወጣትነት እድሜያቸውን ጨርሰው ትዳር ሲመሠርቱ ወንዱ *መንቾ* /Mancho/፣ ሴቷ ደግሞ *ሜንትቼ* /Meentichche/ ተብለው ይጠራሉ። በዚህ አገባብ *መንቾ* ባል የሚል ፍች ሲኖረው *ሜንትቼ* ሚስት የሚል እሳቤን ይሸከማል። ከዚህ አገባብ ውጭ ሲታሰብ ሁለቱ ቃላት የተስፋፋ ፍች አላቸው። *መንቾ* የሚለዉ ሰዉ የሚለዉን እሳቤ ሲገልጽ፣ *መና* /Manna/ የሚለዉ ሰዎች የሚል ፍች አለዉ። በተመሳሳይ ሁኔታ ሜንትቼ የሚለዉ ሴት የሚለዉን ሲገልጽ፣ ሜንቶ /Meento/ የሚለዉ ደግሞ የሜንትቼ የብዙ ቁጥር ቅርጽ ነዉ። ልጆች በወጣትነት የእድሜ ክልል (*ወራድቾ* ወይም *ባዣሜ*) ሲባሉ ርስ በርስ የሚጠራሩበት የጓደኛ ስምም ይሰጣጣሉ። ይህም *ገበጥ-ሱማ* /Gaba'xx summa/[82] ተብሎ ይታወቃል።

ልጆች ያሏቸው በእድሜ ገፋ ያሉ ሰዎች በመጀመሪያ ልጃቸው ይጠራሉ። ለምሳሌ፣ የመጀመሪያ ልጃቸው ስም *ሎጵሶ* /Lophphisso/ ቢሆን፣ አባት በጓደኞቹ ወይም በእኩዮቹ *ሎጵስ አና* /Lophphis anna/ "የሎጵሶ አባት" ተብሎ

[82] ይህንን በሚመለከት የጓደኛ መግባቢያ ስሞች የሚለውን ይመልከቱ።





ይጠራል። እናትም እንዲሁ *ሎጵስ አማ* /Lophphis ama/ *"የሎጵሶ እናት"* ተብላ ትጠራለች። በተመሳሳይ መልኩ የመጀመሪያ ልጅ ሴት ከሆነችም እንዲሁ በሴቷ ይጠራሉ። በዚህ ስርአት ታላላቆችን የሚጠሩት በእድሜ ተመሳሳይ ክልል ውስጥ ያሉት ናቸው እንጂ ወጣቶች የመጀመሪያ ልጅን በማስቀደም አይጠሩም። ወጣቶች የመጀመሪያ ልጅን በማስቀደም የሚጠሩም ከሆነ *አባ* /Abba/ "አባት" የሚል ቃል ስሙ ላይ ቀጥለዉ ይጠራሉ፤ ለምሳሌ፣ እኩዮች *ሎጵስ-አና* /Lophphis anna/ የሚሉትን፣ ታናናሾች *ሎጵስ-አን-አበኣ* /Lophphis anni abba'a/ በማለት ይጠራሉ። በተመሳሳይ እድሜ ክልል ውስጥ ያሉ ወንዶች በተለይም በእድሜ ጠና ያሉት ርስ በርስ ሲጠራሩ በቁልምጫ ስም ሊጠራሩ ይችላሉ።

*ለምሳሌ፣*

| | |
|---|---|
| ሎጵስ አና | "የሎጵሶ አባት" |
| Lophphis anna | (ያለቁልምጫ) |
| አባ ሎባ | "የሎባ አባት" |
| Abbaa loba | (በቁልምጫ) |
| አሻም አና | "የአሻሜ አባት" |
| Aashaam anna | (ያለቁልምጫ) |
| አባ አሾ | "የአሾ አባት" |
| Abba aasho | (በቁልምጫ) |
| ሎምባም አና | "የሎምባሜ አባት" |
| Lombaam anna | (ያለቁልምጫ) |
| አባ ሎምቦ | "የሎምቦ አባት" |
| Abba lombo | (በቁልምጫ) |

እላይ ከቀረቡት መረጃዎች፣ የስም አጠራር በቁልምጫና ያሰቁልምጫ የተሰያየ መሆኑን መረዳት ይቻላል። ለምሳሌ፣ ሎጵስ-አና (የሎጵሶ አባት) የሚለው በቁልምጫ ሲጠራ አባ ሎባ ሆኗል። በዚህም ሁለት መሰረታዊ ለውጦች ተከስተውበታል። የመጀመሪያው አና (አባት) የሚለው አባ በሚል ቅርጽ የተተካ ሲሆን ፣ ሎጵሶ የሚለው በቁልምጫው አጥሮ (ሎባ ሆኖ) ይጠራል። ይህ ስርአት በሌሎችም ምሳሌዎች ተመሳሳይ ሲሆን፣ በቁልምጫው ቅርጽ እናቶች ወይም ሴቶች አይጠሩም፤ በሌላ አነጋገር፣ እናቶች በመጀመሪያ ልጃቸው ስም በቁልምጫ የመጠሪያ ቅርጽ በሀዲይሳ የለም።

በሀዲያ ባህል ሚስት ባሏን የምትጠራበት ቅርጽ አለ። ሚስት ባሏን ስትጠራ በአክብሮት (አንቱ) በማለት የምትጠራ ሲሆን ልጅ ሲወለድ ደግሞ በመጀመሪያ ልጃቸው ትጠራለች። አጠራሩም *[የእገሌ አባት + አንቱታ /አክብሮት/]* ስርአትን የተከተለ ነዉ። ለምሳሌ፣ ሚስት ባሏን ወደእሷ እንዲመጣ ለመጣራት ስትፈልግ፣ የመጀመሪያ ልጃቸው ጡሚሶ / Xummisso/ ቢሆን፣ ጡሚስ-አ'ን ዋሌሄ /Xummis ann waalehe/ "የጡሚሶ አባት ይምጡ" በማለት ትጠራለች። ባል ሚስቱን ሲጠራትም በመጀመሪያ ልጁ የሚጠራት ሲሆን አክብሮት ግን አይጨምርበትም። ለምሳሌ፣ *ጡሚስ አማ ዋሬ* /Xummis ama waare/ (የጡሚሶ እናት ነይ) በማለት ይጠራታል። በሌላ በኩል፣ ባል ሚስቱ በሌለችበት ስለሷ ከቤተሰቡ አባላት መረጃ ለመጠየቅ *እሴ ቤኤኒሄ* /Ise bee'eniihe/ "እሷ የለችም ወይ" ወይም *ንምኔት ቤኤኒሄ'* /Ni minnette bee'eniihe/ "የኛ ቤቷ የለችም ወይ" በማለት ይጠራታል። ሴቷም በተመሳሳይ ሁኔታ በአክብሮት ባል በሌለበት ስለእሱ መረጃ ልትጠይቅ ትችላለች። ለምሳሌ፣ *ን ምእን መንቾ ቤአኬኤንሄ*





/Ni mi'nn manch bee'akkeheniihe/ *የኛ ቤቱ ሰውዬ የሉም* ወይ? በማለት መረጃ ትጠይቃለች። በሌላ በኩል ወላጆች ልጆቻቸዉን ፤ ወንድ ከሆነ *አና* /Anna/ (አባት) ሴት ከሆነች ደግሞ *አማ* /Ama/ ወይም *አምሮ* /Amiro/ (እናት) በማለት ሲጠሩ ሌሎች ጎረቤቶችም የወላጆቻቸዉን አጠራር ተከትለዉ በዚያዉ በቅጽል ስያሜያቸዉ ይጠሩዋቸዋል።

ቀደም ሲል ከቀረበው የስም አጠራር በተጨማሪ የስጋ ዝምድናና የጋብቻ ዝምድና ገላጭ ስሞች በቋንቋ ውስጥ አሉ። ተከታዮቹ ስያሜዎችና አጠራራቸዉ ለዚህ አስረጂዎች ናቸው።

| | |
|---|---|
| አቼ፣ ኣዴ<br>Aachche, Aadde | የእናት መጠሪያ ስም (እማዬ) |
| አባኣ፣ ኣባዮ<br>Abba'a, Abbaayyo | የአባት መጠሪያ ስም (አባዬ) |
| ሎብ ኣያኣ፣ ሎብ ኣዴኤ፣ኢዮ<br>Lob aayya'a, lob aadde'e, Iyyo'o | የሴት አያት መጠሪያ ስም |
| ሎብ አባኣ<br>Lob abba'a | ወንድ አያት መጠሪያ ስም |
| አነባዮ<br>Annabbaayyo | አጐት ወይም የአባት ወንድም መጠሪያ (አጐቴ) |
| ኤሼኤ<br>Eeshe'e | የእናት ወንድም (አጐቴ) |
| አዳዬ<br>Addaayye | አክስት የአባት እህት (አክስቴ) |
| አማዬ<br>Amaayye | አክስት የእናት እህት (አክስቴ) |

| | |
|---|---|
| ኤበር[83] አባዮ /Ebar abbaayyo/ | ታናሽ እህትና ታናሽ ወንድም ታላቅ ወንድማቸዉን የሚጠሩበት፤ ለምሳሌ፣ ጡምኤቦ/Xummeebo/ ታላቅ ወንድም ቢሆን ታናሾቹ "ጤምኤብ አባዮ" /Xummeeb abbaayyo/ ይላሉ። |
| ኤበር አይቼ /Ebar ayichche/ | ታናሽ እህት ወይም ታናሽ ወንድም ታላቅ እህታቸዉን የሚጠሩበት፤ ለምሳሌ፣ ሉምባሜ ታላቅ ብትሆን ታናናሾቿ "ሉምባም አይቼ" ብለው ይጠሯታል። |
| ሄሬቼ /Heereechche/ | አንድ ወንድ የወንድሙን ሚስት የሚጠራበት |
| ሴታ /Seeta/ | አንድ ሴት የወንድሟን ሚስት የምትጠራበት |

[83] *ኤበር፣* የሚለዉ አንትና እንደማለት ሲሆን ታላቅ ወንድም ወይም እህት የሚተካበት የስም ምትክ ሆኖ ሊያገለግል ይችላል፤ ምክንያቱም በሀዲያ ባህል ታናናሾች ታላላቅ ወንድሞቻቸውን ወይም ታላላቅ እህቶቻቸውን በአክብሮት መጥራት እንዳለባቸው ይታመናል። ታናናሽ ታላላቃቸዉን በአክብሮት የሚጠሩበት ደረጃ ከታች ወደ ላይ ከሶስተኛ ታላቅ ጀምሮ ባለዉ ነዉ፤ የእድሜ ተከታይ የሆኑት ከነሱ በእድሜ አንድ ደረጃ የሚቀድማቸዉን በአክብሮት አይጠሩም። በአክብሮት በሚጠሩበት ጊዜ የታላቅ ወንድማቸዉን ወይም እህታቸዉን ስም አስቀድመዉ፣አባዮ/ወንድሜ/ ወይም አይቼ/እህቴ/ የሚለዉን አስከትለዉ ይጠራሉ።

በተጨማሪም አባትን ወይም እናትን አንተ ወይም አንቺ ብሎ መጥራት በባህሉ ተቀባይነት የለውም፤ በመሆኑም ልጆች ወላጆቻቸውን ክኢኔ / Ki'inne/ (እንቱ፣3ኛ መደብ አክብሮት) ብለው የመጥራት ግዴታ አለባቸው። ልጆች፣ ወላጆቻቸውን አንቱ ማለት ሲገባቸው አንተ ወይም አንቺ ብለው ቢጠሯቸው እነሱን እንደማዋረድ ይቆጠርባቸዋል።





| | |
|---|---|
| ለንድ-አሮኦ /Land aro'o/ | ወላጆች ወይም ሌሎች የልጃቸውን ባልየሚጠሩበት (ስሙ ሳልታወቀ ወይም ዉስን ሳልሆነ የሚሰጥ) ሲሆን ሲታወቅ ለንድች አሮኦ /landichch aro'o/ ተብሎ ይጠራል። |
| ቤት-አሬ /Beet are/ | ወላጆች ወይም ሌሎች የልጃቸውን ሚስት የሚጠሩበት (ስሟ ሳልታወቀ ወይም ዉስን ሳልሆነ የሚሰጥ) |

ቀደም ሲል እንደተጠቀመው በሀዲያ ህዝብ ባህል የሰው ስም ያለ አንዳች ምክንያት አይሰየምም። በባህሉ የተለያዩ ሁኔታዎችንና አጋጣሚዎችን መነሻ በማድረግ የሰዉ ስሞች ይሰየማሉ፤ ጉልተው ከሚታዩትም ውስጥ የልደት ስም፣ ከእንስሳትና ከተፈጥሮ የተወሰዱ ስሞች፣ የጓደኛ መግባቢያ ስሞች እና የማእረግ ስሞች የመሳሰሉት ይጠቀሳሉ።

## 5.2.1. የልደት ስም

አንድ ሰዉ እንደሚወለድበት ጊዜ፣ ሁኔታ ወይም አጋጣሚ ስያሜው ከዚያ ሁኔታ ጋር ይያያዛል። ለዚህ ማሳያ እንዲሆን ተከታዮቹ ምሳሌዎች ወይም የአሰያየም ሁኔታዎችና ስሞች ቀርበዋል።

### ሀ. አመሻሽን አመልካች(ገላጭ) ስሞች

አመሻሽ አካባቢ ለሚወለድ ህጻን ከዚያ ጊዜ ጋር ተያይዞ የተወለደበትን ጊዜ ገላጭ ስያሜ ይሰጠዋል። በሀዲያዎች ዘንድ አመሻሽ ለሚለው ቃል "የከብቶች መግቢያ" የሚለዉ ጊዜዉን ገላጭ እሳቤ ሲሆን በሀዲይሳ ለዕል-ኣጋ /La'll aagga/ በመባል ይታወቃል። በዚህ መሰረት፣ ተሰያሚው ወንድ ከሆነ

ለዕላጎ /La'llaaggo/ ተብሎ ሲጠራ፣ ሴት ከሆነች ደግሞ ለዕላጌ /La'llaagge/ ተብላ ትጠራለች።

ለ. ጧትን (ንጋትን) አመልካች ስሞች

ጧት ስሚወስድ ህጻን የሚሰጠው ስያሜ ደግሞ ንጋት በሀዲይሳ ደራ ወይም ሶደና /Dara, Soodanna/ ከሚለው የጊዜ ክፋይ ጋር ተያያዥነት ያለው ነው።

ለምሳሌ፣

| ስም | የአማርኛ ቀጥተኛ ፍቺ |
|---|---|
| ደሪሎ/Dariillo/ | "በጧት ብቅ ያለ" |
| ሶደኖ /Soodanno/ | "ንጋቱ" |
| ሶዲሶ /Soodiso/ | "ያስነጋ" |
| ሶዴ /Soode/ | "ንጋ" |
| በሎሎ/Bololo/ | "አንጸባራቂ/አብሪ" |

ሐ. የጦርነትን ዘመን (ወቅት) አመልካች ስሞች

ጦርነት በነበረበት ዘመን ለተወለደ ልጅ ያንን ክስተት ለማስታወስ ክስተቱን የተወለደው ህጻን ያመጣ ያህል በሚያስመስል መልኩ ይሰየማል።

ለምሳሌ፣

| ስም | የአማርኛ ቀጥተኛ ፍቺ |
|---|---|
| ኦሬቦ/Oreebo/ | "ጦርነት አምጪ" |
| ጋዴቦ/Gaadeebo/ | "ዘመቻ /ጦርነት/ ምጪ" |
| ጋዶሮ/Gaadoro/ | "ጦርነት አምጪ" |
| ሀዎኤቦ/Hawwo'eebo/ | "መከራ አምጪ" |
| ኦራሞ/Oraamo/ | "ጦረኛ" |
| ኦርበጮ/Orbaco/ | "ጠላትን ደምሳሽ" |
| ኦሪቆ/Oriiqo/ | "ጦርነት ሰባሪ፣ ሀያል" |
| ኦረንሶ/Oranso/ | "የጦር አዝማች፣ አዋጊ " |





የሚጠሩ ሲሆን፤ በተጨማሪም ስሞቹ፣ ህጻኑ የነበረበትን የሞት ጫፍ ወይም አፋፍ አስታዋሽ ናቸው።

ሰ. በጥጋብ ዘመን ወይም ሀብት ሲበዛ ለተወለዱ ልጆች የሚከተሉት አይነት ስያሜዎች ይሰጧቸዋል።

ለምሳሌ፣

| ስም | የአማርኛ ቀጥተኛ ፍቺ |
|---|---|
| ጎዴቦ/Goddeebo/ | "ሀብት አምጪ" |
| ለራሞ /Laraamo/ | "ባለ ብዙ ከብት" |
| ለምቦሮ/Laamboro/ | "ከብር አምጪ" |
| ጎዲሶ /Goddiso/ | "አጥጋቢ" |
| አጫሞ/Aacaamo/ | "እርጥብ ነህ /በሀብት/" |
| ሎምቤቦ/Lombeebo/ | "ከብር አምጪ" |
| ኤርማዶ/Ermaaddo/ | "መልካም ማዕድ" |
| ማዴቦ /Maaddeebo/ | "ሁብት አምጪ" |

በሌላ በኩል፣ በኢኮኖሚና በኑሮ ደረጃ ይናቅ የነበረ ሰው ሲያልፍለት የልጁን ስም ገዶሬ /Gadoore/ "ነቀፌታ ወይም ንቀት አስወጋጅ ነህ"፣ ቲርካሶ/Tiirkaaso/ "ልብ የሚያሳርፍ"፣ ቤዮካሶ /Beyyikaaso/ "መሰረት ተካይ" በማለት ይሰይማል።

ሸ. ጦርነትና ሁከት አልፎ ሰላም በሰፈነበት ዘመን ለተወለደ ያንን ዘመን ወይም ሁኔታ ገላጭ ስሞች አዲስ ለተወለደ ህጻን ይሰጠዋል።

ለምሳሌ፣

| ስም | የአማርኛ ቀጥተኛ ፍች |
|---|---|
| ጡሚሶ /Xummiso/ | "ሰላም አስፋኝ" |
| ጡምቲሮ /Xumtiiro/ | "ሰላም ያሰብክ" |
| አኖሮ /Annoro/ | "አባት አ፤°ጪ" |
| ጡምዶዕሎ /Xummdoo'llo/ | "ሰላም ፀዳድ" |
| ጡሞሮ /Xummoro/ | "ሰላም አምጪ" |
| ጡምደዶ /Xumdado/ | "ሰላም ገማጅ" |

ቀ. አንድ ህጻን በሚወለድበት ወይም በምትወለድበት ወቅት በቤተሰብ ዉስጥ በተለይም በባልና ሚስት መካከል የተከሰተ ዉን አንዳች ሁኔታ እንዲገልጽ ተደርጎ ስም ይሰጣል:: ህጻኑ ሲወለድ ባልና ሚስት ቢጣሉ የህጻኑ ስም *ወሼቦ* /Woshsheebo/ «ነገርአምጪ» *ወጭሶ* /Wociso/ «አቃጣሪ» ተብሎ ይሰየማል:: ከዚህ በተቃራኒዉ ተጣልተዉ በነበሩት ባልና ሚስት መካከል እርቀ-ሰላም ቢወርድ በወቅቱ የተወለደዉ ልጅ *ኢተንሶ* /Iittanso/ ፣ *አራሶ* /Araaso/ «አስታራቂ ነህ» ለወንድ ሲባል፤ ለሴት ደግሞ *ሺናቴ* /Shiinaate/ ፣ *አራሴ* /Araase/ «አስታራቂ ነሽ» ተብሎ ይሰየማል::

## 5.2.2. ከእንስሳትና ከተፈጥሮ የተወሰዱ ስሞች

የእንስሳትና የተፈጥሮ ባህርይ ለልጅ አውርሶ ለመግለጽ ሲፈለግ ከዱር አራዊት፣ ከቤት እንስሳት ከተፈጥሮ ክስተቶች ወስዶ ለልጅ ስም መሰየም በሀዲያ ባህል የተለመደ ነው::





ለምሳሌ፣

| ስም | የአማርኛ ቀጥተኛ ፍች |
|---|---|
| ሎብዱኖ/Lobduuno/ | "ትልቁ ተራራ" |
| ዱናሞ /Duunaamo/ | "ተራራማ" |
| ቦላንኮ /Boolaanko/ | "ኮከብ ነህ" |
| ለራሞ /Laraamo/ | "በላብዙ ከብት ነህ" |
| ቢሻሞ /Biishshaamo/ | "ባለዳለቻ በሬ" |
| ከቤሮ /Kabeero/ | "ነብር ነህ" |
| ዳጌሮ /Daageero/ | "ዝንጀሮ ነህ" |
| ደቀዮ /Daqayyo/ | "ሜዳ ነህ" |
| ጎጎ /Googo / | "መንገድ" |
| ደምበሎ/Dambalo/ | "ሀይቅ" |
| ጨፎኦ /Cafo'o / | "ረግረጓ" |
| ድምባቤ /Dimbaabe/ | "ዘምባባ" |

## 5.2.3. የማእረግ ስሞች

በሀዲያ ባህል በተለያዩ መነሻዎች የተለያዩ የማእረግ ስሞች ይሰጣሉ:: በባህሉ የማእረግ ስሞች ከሚያመለክቷቸው መገለጫዎች መካከል፤ የአንድ ግለሰብ የስራ ታታሪነቱን፣ አኗኗሩንና የቤተሰብ አስተዳደሩን፣ የማህበረሰብ አስተዳደር ብቃቱን፣ በጦርነትና በዘመቻ ወቅት የነበረዉን ተሳትፎዉ ፣ የንግግር እና የማሳመን ችሎታዉን፣ የከብቶች ብዛትና ሌሎችንም ሊያመለክት ይችላል:: እላይ በተጠቀሱት በማናቸዉም ምክንያቶች በሀዲያ ባህል ለአንድ ግለሰብ የተሰጠዉ የማእረግ ስም በሌላ በተሻለና ከፍ ባለ ማእረግ እስካልተተካ ድረስ እስከ ግለሰቡ እድሜዉ መጨረሻ ድረስ እየተጠራበት ይኖራል:: በሀዲያ ባህል የሚሰጡት የማእረግ

ስሞች መሰረታዊ ችግር ከወንዶቹ ጋር ተመሳሳይ፣ የተለየ መግለጫ ላላቸዉ ሴቶች ማእረጎቹ የማይሰጡ መሆናቸዉ ነዉ:: ከዚህ የተነሳ የማእረግ ስሞቹ የወንዶች ብቻ ናቸዉ:: ወንዶችም የሀዲያን ባህል የማእረግ ስሞች ለማግኘት ትዳር የመሰረቱና በእድሜና በተግባር የተፈተኑ እንዲሆኑ ይጠበቃል:: ከዚህ በታች በሀዲያ ባህል እጅግ ታዋቂ ከሆኑት የማእረግ ስሞች የተወሰኑት በምሳሌነት ተጠቅሰዋል::

አድላ /Adila/- ለሚመራና ለሚያስተዳድር የሚሰጥ እጅግ ትልቁ ማእረግ

ገራዳ /Garaada/- ለሚያስተዳድርና ሀራጋ /Hiraaga/ ለሚችል የሚሰጥ

አባገዳ /Abaagada/- ለታላቅ የጦር ጀግናና መሪ የሚሰጥ

አበጋዛ /Abagaaza/- ለጎበዝ ጦረኛ የሚሰጥ

አስማቹ /Asmaache'e/- ለመሃራንቾ /Mahaaraancho/ ወይም በሀብት እጅግ ለተከበረ ሰዉ የሚሰጥ

ዳና /Daana/- የተለያዩ የሀዲያ ባህላዊ የአስተዳደር መዋቅሮችን ለሚመሩ ሰዎች የሚሰጥ

ደዳቾ /Daddaachcho/- የንግግርና የማሳመን ችሎታዉን በመጠቀም ችግርን በመፍታት ታዋቂ ለሆነ ሰዉ የሚሰጥ

ላክ አድላ /Laaki Adila/ - የመሃለኖ ማእረግን የመስጠትን ስነስርአቱን ለሚያስፈጽም ሰዉ የሚሰጥ

ኮንቶምቾ /Kontomichcho/- ለጎበዝ ወይም ጠንካራ ግለሰብ የሚሰጥ

አባብያ /Abbaabiyya/- ለጎበዝ ወይም ጠንካራ ግለሰብ የሚሰጥ

እማማ /Imaama/- ለእስልምና ሃይማኖት መሪ የሚሰጥ

አንጃንቾ /Anjaancho/- ለፈንዳነኖ ሃይማኖት መሪና ለሌሎች የሀዲያ ባህል ከፍተኛ ባለስልጣናት አማካሪ ለሆኑት የሚሰጥ





## 5.2.4. ሌሎች ስሞች

### 5.2.4.1. ሃይማኖታዊ ስሞች

በሀዲያ ባህል የፕሮቴስታንት ሃይማኖት በመስፋፋቱ ምክንያት ከክርስቲና እምነት ጋር የተያያዙ የተለያዩ ስያሜዎችን ለልጆች መስጠት የተለመደ እየሆነ መጥቷል:: እነዚህ ስያሜዎች መጽሀፍ ቅዱሳዊ በመሆናቸው ከእስራኤላውያን ባህል የተወሰዱ ናቸው ማለት ይቻላል:: ስሞቹ ወደ ባህሉ ሲገቡ ቅርጻቸውን ከተቀባይ የቋንቋ ስርአት ጋር በመዋሀድ ይነገራሉ:: በዚህም ምክንያት ስሞቹ የራሱ የቋንቋ እስኪ.መስሉ ድረስ ከድምጸ-ልሳናዊ ባህርያት ጋር ተዛምደዋል:: ቀጥለዉ የተዘረዘሩት ስሞች ይህንን ሁኔታ ግልጽ የሚያደርጉ ምሳሌዎች ናቸው::

| የመጽሐፍ ቅዱስ ስሞች | በሀዲይሳ የሚጠሩት ቅርጽ |
|---|---|
| ዳዊት | ዳዊቴ /Daawiite/ |
| ሳሙኤል | ሳሙኤላ/ሳሙኤሌ /Saamu'eela//Saamu'eele/ |
| ዳንኤል | ዳንኤላ/ዳንኤሌ /Daaneela//Daaneele/ |
| ጴጥሮስ | ቤጥሮሴ /Beexiroose/ |
| ዮሀንስ | ዋንሴ /Waanise/ |
| ማቴዎስ | ማቶሴ /Maatose/ |
| ያዕቆብ | ያቆቤ /ያቆባ/ /Yaaqoobe// Yaaqooba/ |
| አብርሃም | አብራሜ /Abraame/ |

### 5.2.4.2.የቅጽል እና የስድብ ስሞች

በሀዲያ ባህል፣ አካባዊ ቅርጽ እና አረማመዳቸው ለማያምር ወይም የማይወደድ ባህርይ ለሚያሳዩ ያንን ግብራቸውን ወይም ባህርያቸውን የሚገልጹ ስያሜዎች ተመርጠው በቅጽል ስምነት ይሰጣቸዋል። ቀጥለዉ በምሳሌነት ከተጠቀሱት ቅጽል ስሞች ዉስጥ አንዳንዱ በቀጥታ ልጆችን ለመጥራት ያገለግላሉ፤ ለምሳሌ፣ አባቶች ልጆቻቸዉን ወይም የልጅ ልጆቻቸዉን *ዳጌሮ* /Daageero/ (ለወንድ) ፣ *ፉርጮ* / Furco'o/ (ለሴት) በማለት መጥራታቸዉ የተለመደ ነዉ።

*ምሳሌ፣*

| *ስም* | ፍችውና ሲገለጽ የታሰበው ነገር |
|---|---|
| ዳጌሮ[84]<br>Daageero | "ዝንጀሮ ነህ"(ለወንድ ልጅ) |
| ፉርጮ<br>Furco'o | "ፉንጋ ነሽ" (ለሴት ልጅ) |
| ባፋ<br>Baafa | "ሽፋፋ" |
| ኡልጉንቾ፣ጉርሳ፣ጉጉማ፣ ቆንጦላ፣ ጌየራ<br>Uulgunchcho, Gursa, Guguma, Qonxolla, Geyyera | "በጣም አጭር፣ ድንክ፣ ጉቶ፣..." |
| ሀቁዳ<br>Haqquuda | "ቀጭንና ኮስማና፣ ቀሽም" |
| ሎጦባ፣ ሁጁባ<br>Loxxobba, Hujuba | "ከመጠን በላይ ረጅም" |
| ንጋራ<br>Niggaara | "ጆማት" (ቀጭንና ጠንካራ ለሆነ ሰው) |

[84] *ዳጌሮ*፣ አንድ አባት ለልጁ ወይም ለልጅ ልጁ እንደቅጽል ስም የሚሰጠዉ መጠሪያ ነዉ፤የዚህ ልጅ መደበኛ ስሙ ሌላ ሊሆን ይችላል።





| *ስም* | ፍችውና ሲገለጽ የታሰበው ነገር |
|---|---|
| ጐተንስቾ<br>Gotansichcho | "ጉጉት" (በየስፋራው የሚያንቀሳፋ) |
| ቀመቾ፣ቄዕሜላ<br>Qamachcho, Qe'mmela | "ጦጣ"(ሳያቋርጥ የሚያወራ፣ ለፍላፊ) |
| ሼርካ፣ ሼታ<br>Sherkka, sheteeta | "አቅመ-ቢስ" |
| ጦዕማ<br>Xo'mma | "ቶሎ የማያድግ ወይም ያልፋፋ (ለልጅ)" |

### 5.2.4.3. የጓደኛ መግባቢያ ስሞች

በተመሳሳይ የእድሜ ክልል ውስጥ ያሉ ወጣቶች እርስ በርሳቸው ስም የሚሰጣጡበት ስርአት በሀዲያ ወጣቶች ዘንድ የተለመደ ነው። የዚህ አይነቱ የስም አሰያየም ወላጆች ለወጣቶች በህጻንነታቸው ወራት ከሰጧቸው ስሞች ወይም ከመደበኛ ስሞች ተጨማሪ ናቸው። ወጣቶች እርስ በርሳቸው የሚጠራሩባቸው ስያሜዎች የጓደኛ ስም (*ደረጵ-ሱማ* /Daraphph summa/) ወይም የገበታ ስም (*ገበጥ-ሱማ* / Gabaxx summa/) የሚባል ሲሆን ይህ የሚፈጸምበት ስርአት ደግሞ ስም መጠራራት (*ሱሜጨንቻ* /Summ weeccancha/) በመባል ይታወቃል።

ወደ *ሱሜጨንቻ* ስርአት ወጣቶች ከመግባታቸው በፊት ወንድ ልጅ *ጌጥ-ቤቶ* /geex-beeto/፣ ሴት ልጅ ደግሞ *ጌጥ-ለንድቾ* /geex- landichcho/ እየተባሉ ይጠራሉ። *በሱማ ዌጨንቻ* ስርአት ሲያልፉ የእድሜ ደረጃ ስማቸው ተቀይሮ ወንዶቹ *ወራድቾ* /Woraadichcho/ (በብዙ ቁጥር፣ *ወራዳ*) ሲባሉ፣ ሴቶች ደግሞ *ባጅና አፎኦ ለንድቾ*

/Baajina afo'oo landichcho/ (የደረሰች ልጅ) ተብለዉ ይጠራሉ።

በዚህ የእድሜ ሽግግር ወቅት በተመሳሳይ የእድሜ ክልል ውስጥ ያሉ ወንዶችም ሆኑ ሴቶች *የሱማ-ዌጪንቻን* በአል ለማክበር በየሰፈራቸው ይፈላሰጋሉ። ከዚያም ለበአሉ ዝግጅት አስተባባሪዎችን ከሁለቱ ጾታዎች በመምረጥ ዝግጅቱ ይጀምራል። በዚህ ሂደት ውስጥ እያንዳንዱ አባል የየድርሻውን እንዲያዋጣ የሚጠበቅበት ሲሆን ወንዶች ገንዘብ እና የተለያዩ ጥራጥሬዎችን ያዋጣሉ። ሴቶቹም በበኩላቸው ቅቤና ቅመማ ቅማም ከእናቶቻቸው በመጠየቅ ያዘጋጃሉ። ሴቶች ሁል ጊዜ በወላጆቻቸው የኢኮኖሚ ጥገኛ ላይሆኑ ይችላሉ። የተለያዩ የእጅ ስራዎችን (ዘንቢል፣ ሴማት፣ እርቦ...) ሰርተው የሸጡት ገንዘብ ካላቸው ለዚህ ዝግጅት ያውላሉ። ቀደም ሲል የተመረጠው ኮሚቴ ስራው ለበአሉ ዝግጅት የሚሆን ቤት /እልፍኝ/ ከማህበረሰቡ በማፈላለግ ማዘጋጀት እና ከየቡድኑ አባላት ገንዘብና አስፈላጊ ነገሮችን መሰብሰብ ነው። የሴቶች አስተባባሪዎችም ድግሱን በተለይ የሚበላን ነገር እንዴት እንደሚያሰናዱ ይመካከራሉ፤ መርሀ-ግብርም ይነድፋሉ።

ይህ ዝግጅት ወይም በአል የሚደረገው ለአንድ ሳምንት ሲሆን ለስነስርአቱ በተመረጠው ቤት ውስጥ ርስ በርስ እየተዝናኑ እና እየጨፈሩ ይቆያሉ። በዚህ ቆይታ ነጻ ሆነው ከመጫወትና ከመዝናናት ያለፈ የግብረ-ስጋ ግንኙት ማድረግ አይፈቀድም። ወጣቶቹ የሚያድሩበት ቤት ወይም እልፍኝ አንድ ቢሆንም የመኝታ ቦታ ሲዘጋጅ ግን ለወንዶቹ ባንድ ወገን ለሴቶቹ በሌላ ወገን በማድረግ ነው። በበኣሉ ቆይታ ውስጥ አንድ ወንድ ከአንድ ሴት ጋር ግብረ ስጋ ግንኙነት





ቢፈጽም ወይም መፈጸሙ ቢሰማ ከማህበረሰቡ ስለሚገለል ወይም ስለሚወገዝ ያንን ድርጊት ለመፈጸም ፍላጐት ቢያድርበት እንኳን ላለመፈጸም ራሱን ያሳምናል። ግንኙነታቸውም የወንድም እና የእህት አይነት ብቻ ሆኖ ይቀጥላል።

*የሱማ-ዌጪንቻ* ስርአት በሚደመደምበት የመጨረሻ ቀን ላይ የስም መጠራራቱ ስርአት ይፋ ይደረጋል። በዚህ ስነስርአት ላይ የሁሉም ወጣቶች ወላጆች እንዲገኙ ጥሪ ይደረግላቸዋል። እያንዳንዱ ወላጅም በዚያ በአል በደስታ ይገኛል። *በሱማ-ዌጪንቻ* ስርአት ለታዳሚዎቹ እንጀራ፣ ወጥና ስጋ የመሳሰሉት የምግብ አይነቶች የሚዘጋጁ ሲሆን ዋናውን የስም አወጣጥ ስነስርአት ለመፈጸም ግን የሚደረገው ከገብስ ዱቄት፣ ከቅቤና ከተለያዩ ቅመማ ቅማም የሚዘጋጅ *ቡሎ* /Bullo/ የተባለ ምግብ በማብሰል ነው። የስም ማውጣቱ ስርአት ከመጀመሩ በፊት የተጋበዙ ወላጆች የተዘጋጀላቸው እንጀራ እና ወጥ ቀርቦላቸው ይመገባሉ። ከዚያ በሁዋላ የወላጆች፣ የወጣት ወንዶች እና የወጣት ሴቶች መቀመጫቸው ለየብቻቸው ሶስት ቦታ ተከፋፍሎ ይደረደርና በዚያ እያንዳንዱ ቡድን በተዘጋጀለት ቦታ ይቀመጣል። ለስም መጠራራቱ ስነስርአት አስቀድሞ የተዘጋጀው ቡሎ ሶስት ቦታ ተከፋፍሎ ገበታ ላይ ከተደረገ በሁዋላ ለሶስቱ ቡድኖች ይሰጣቸዋል። *ቡሎው* ከመበላቱ በፊት ከሁለቱ ጾታዎች የወጣት ተወካዮች ይመረጣሉ። እነዚህ ተመራጮች ለእድሜ እኩዮቻቸው አካላዊ ቅርጻቸውን፣ መልካቸዉንና ባህርያቸውን ገላጭ የሆኑ ስያሜችን እንዲሰጡ ይደረጋል። በዚህ ስነስርአት የወንድ ተወካዮች ለሴቶች ስያሜ ሲስጡ፣ የሴት ተወካዮች ደግሞ ለወንዶች ስያሜ ይስጧቸዋል።

በበአሉ ተሳታፊ ለነበሩት ወጣቶች በሙሉ ስም የማውጣቱ ሂደት እንደተጠናቀቀ ሁሉም በየምድባቸው የተዘጋጀላቸውን *ቡሎ* /Bullo/ ይበላሉ። *ቡሎውን* የመብላቱ ሂደት ሲጀመር በጾታ ተከፋፍሎ የነበረው ቡድን ይፈርስና አንድ ወጣት የእድሜ አቻዉ የምትሆነውን ሴት ጓደኛ መርጦ እያጉረሳት አብሯት ይበላል። ሴቷም ከወንዶቹ ውስጥ ጓደኛዋ ለማድረግ ከመረጠችው ወንድ ጋር አብራ ትመገባለች፤ ለእሱም ታጉርሳለች። ወላጆች ወይም ተጋባዥ ሽማግሌዎች *ቡሎውን* ከተመገቡ በሁዋላ ወጣቶቹን እንደመረቁ የስነስርአቱ ማጠቃለያ ይሆናል።

የስም ማውጣቱ ስነስርአት ከተጠናቀቀበት እለት ጀምሮ ወንዶቹ እና ሴቶቹ ጥንድ ጥንድ በመሆን በተመገቡበት ስርአት መሰፌት አንዳቸው ለሌላቸው ተጠንቃቂና የቅርብ ጓደኛ ሆነዉ ይቀጥላሉ። ሴቷ እንደ ቅርብ ጓደኛ አ፦ርጋ የመረጠችውን ወንድ ከጥቃት ተከላካይ አድርጋ ስ፦ቀጥር ወንዱም ደግሞ እንደ ምቹ ጓደኛው አድርጐ ይቆጥ፦ታል። ወዳጅነቱ በሁለቱ ጓደኛሞች ወይም ወጣቶች መካከል ብቻ ሳይሆን የሚመሰረተው፣ በጓደኛሞቹ ቤተሰቦች መካከልም ተጠናክሮ የሚቀጥል ይሆናል። አንድ ቤተሰብ ሌላውን እንደ ቅርብ ዘመድ ይቆጥራል። ይህን ዝምድናን በተለያዩ ማህበራዊ አጋጣሚዎች ለምሳሌ፣ በሰርግ፣ በግርዛት እና በመሳሰሉት ሁነቶች/events/ በሚደረገው መረዳዳት ወይም ሀላፊነቶችን በመጋራት ይገልጻል። ብዙ ጊዜ ወጣት ወንዶች ለወጣት ሴት ጓደኞቻቸው ቤተሰብ የተለያዩ ስራዎችን በመስራት ለምሳሌ፣ እርሻ በማረስ፣ ቤት በመስራት ወዘተ. ለጓደኞቻቸው ያላቸውን አጋርነትና አለሁ ባይነት ያሳያሉ። ይህንን ሲያደርጉ ተገደው ሳይሆን በፍቅር፣ የራሳቸውን ስራ እንደሚሰሩ ያህል ደስ እያላቸው ነው።





ቀደም ሲል በተገለጸው *ሱማ-ዌጨንቻ* ስርአት ውስጥ የጓደኛ ስም ሲለየም አለያየሙ በአብዛኛው መሰረት የሚያደርጋቸው ጉዳዮች አሉ፤ የተሰያሚው መልክ፣ ጠባይ ወይም ባህርይ፣ ውሎ፣ አካላዊ ገጽታው (ለምሳሌ፤ ቁመት፣ውፍረት፣ እድሜ) የመሳሰሉት ይተኮርባቸዋል። በሌላ አነጋገር፣ ለተሰያሚዎቹ የሚሰጡዋቸው ስያሜዎች ከተፈጥሯዊው ቁሶች ያንዱን ባህርይ፣ መልክ ወይም ቀለም በመውሰድ በተለዋጭ ስያሜ /methaphor/ ለመጥሪያነት የሚያገለግሉ ሊሆኑ ይችላሉ። ቀጥለው የቀረቡ ምሳሌዎች[85] ይህንኑ የሚያሳዩ ናቸው።

*ምሳሌ፣*

| *ጾታ* | | *እንዲገልጽ የሚፈለገው ባህርይ ወይም ስያሜው የተወሰደበት ነገር* |
|---|---|---|
| *ወንድ* | *ሴት* | *የአማርኛ ፍች* |
| ዶዕልቾ<br>Doo'llichcho | ዶዕልቼ<br>Doo'llichche | በጣም ቆንጆ |
| ---------- | ጋልሸዋ<br>Gaalshawwa | ቀጠን ረዘም ያለች |
| ሸዊቾ<br>Shawwichcho | ሸዋ<br>Shawwa | ከወገብ ቀጠን ያለ /ያለች/ |
| ሌግቾ/ሌጋሞ/<br>Leegichcho/Leegaamo/ | ሌጋ<br>Leega | ረጅም ወይም ቀጥ ያለ/ች(ከቀረሮ ዛፍ) |
| አድንቆ<br>Adinqo | አድንቄ<br>Adinqe | ነጭ ጥርስ ያላት |
| አረሶ<br>Araso | አረሴ<br>Arase | ቆንጆ (ከስንዴ መልክ) |
| ---------- | ወዕም<br>Wo' michche | ሞላ ያለ ሰውነት ያላት |

[85] እነዚህ ምሳሌዎች የተገኙት ከአ.ሲዶ (1999፡33)፣ እና የመጽሀፉ ጸሀፊዎች ካነጋገሯቸዉ ቃላዊ መላሾች ነው

| | | |
|---|---|---|
| ---------- | ቦምባ Boomba | ደልደል፣ክብብ ያለ ሰውነት ያላት |
| Laa'wwichcho | Laa'wwichche | |
| ላድቾ Laaddichcho | ላድቼ Laaddichche | ለግላጋ ወጣት |
| ላዊቾ Laa'wwichcho | ላዊቼ/ላዎ/ Laa'wwichche/Laa'wwo/ | ከንጋት ብርሃን የተወሰደ |
| ወሌንዶ Woleendo | --------- | የወንዝ ዳር ቄጠማ |
| ወቻዮ Wochaayyo | ወቻዬ Wochaayye | የጠራች(ከንጹህ የዉሃ መልክ) |
| ------- Atture | አቱሬ | ጥቁር ነሽ (ከአጋም ፍሬ) |
| ቦዬ Booyye | ቦያ Booyya | ከነጭ ነገር |
| ------ | ጉርምሼ Gormishe | ከቀጋ ፍሬ መልክ |
| ----- | ዳንኩሌ Daankuule | ጠይምነትን ገላጭ |
| ለትቾ Latichcho | ለትቼ (ሏታ) Latichche/Lata/ | ለግላጋነት አመልካች |
| ሃብቾ[86] Haabbichcho | ሃብቼ Haabbichche | ጸጉር አሰራር የተወሰደ ሞላ ያለ ጸጉር ያሰው /ያላት/ |
| ሽርዴሞ Shirdeemmo | ------- | ጥቅጥቅ ያለ ቅንድብ ያለዉ |
| ጀጅንቆ Jaanjiiqo | ብትሬ Bitre | ጥርሰ-ፍንጭት |
| ምሽቆ Mishiqo | ----- | ሁልጊዜ ብሩህ ፊት ላለው |
| ወዕምቾ Wo'mmichcho | ወዕምቼ Wo'mmichche | ሞላ ያለ ሰዉነት ያለዉ (ያላት) |

[86] ሀባ/haabba/ ለሹሩባ ያልደረሰ መካከለኛ ጸጉር ወይም አፍሮ የሚባለዉ የጸጉር አሰራር አይነት ነዉ።





እነዚህ ስሞች ተለያሚዎቹ ሳይፈልጉ በግድ የሚቀበሏቸው ሳይሆኑ በእድሜ ዘመናቸው ሁሉ ወደዋቸው የሚጠሩበቸው፣ እንዲያውም የሚኮሩባቸው ተወዳጅ ስሞች ናቸው። የስሞቹ ስነልሳናዊ ገጽታ ሲታይ አብዛኞቹ ስሞች በሁለቱም ጾታዎች የሚነገሩ ሲሆን አንዳንዶቹ (ጥቂቶቹ) በወንድ ወይም በሴት ጾታ የመነገሪያ ቅርጽ የላቸውም። አብዛኞቹ የወንድ (ተባታይ) ጾታ አመልካች የጓደኛ መጠራሪያ ስሞች 'ኦ' በተባለው አናባቢ ሲጨርሱ፣ የሴት (አንስታይ) ጾታ አመልካቹ ደግሞ በ 'ኤ' ይጨርሳሉ።

*ገበጥ-ሱማ* ወይም *ደረጽ-ሱማ*፡ ለሀዲይሳ ቋንቋ የቃላት ፈጠራና መስፋፋት /lexical development/ ከፍተኛ ጥቅም ያለው በመሆኑ፣ ለቋንቋው እድገት በእጅጉ አጋዥ እንደሆነ ይታመናል። ሆኖም ይህ ባህላዊ ቅርጽ እና ስነስርአቱ በአሁኑ ጊዜ በመጥፋት ላይ ያለ በመሆኑ በስፋት ሊሰነድ /to be documented/ የሚገባ ባህላዊ ቅርጽ ነው ማለት ይቻላል።

### 5.2.4.4. የጋብቻ ስሞች

በሀዲያ ባህል፣ ሴቶች ሲያገቡ ወላጆቻቸዉ ባወጡላቸዉ ስሞቻቸዉ አይጠሩም፤ በመሆኑም የባሎቻቸዉ ቤተሰቦች ራሳቸዉ የሚጠሩባቸዉን ሌላ ስያሜ ይሰጧቸዋል። የስሞቹ አሰያየም በአንዳች ፍች የተመሰረተ ሲሆን የመጀመሪያ ልጅ ሲያገባ ብዙ ጊዜ የሚሰጣቸዉ ስያሜዎች አሉ። የመጀመሪያ ልጅን ያገባች ሴት *ሉደጌ* /Ludage/ ('እፍታዉን ጠጪ') ስትባል፣ የተከታዩ ወንድ ሚስት ደግሞ *አዋኔ* /Awwane/ (ተከተይ) ተብላ ትጠራለች። በሰርጉ የተለየ አጋጣሚ ቢከሰት ከዚያ ጋር የተያያዘ ስያሜ ይሰጣታል፤ ለምሳሌ፣ በሰርጉ እለት የተትረፈረፈ ድግስ ቢኖር *ማሶ* /Maasso/ (በረከት) ወይም *ሎንሶ* /Lonso/ (እክባሪ) ተብላ ትጠራለች።

*ለምሳሌ፣*

| *ስም* | *የአማርኛ ቀጥተኛ ፍች* |
|---|---|
| ሉደጌ /Ludage/ | አፍታዉን ጠጪ! |
| ሎንሶ /Lonso'o/ | አክባሪ |
| አዋኔ /Awwane/ | ተከተይ! |
| ሎምቦ /Lombo/ | የተከበርሽ |
| ማሶ /Maasso/ | በረከት ነሽ |

## 5.3. *በሉዊሻ፤ የሀዲያ ሴቶች የቋንቋ አጠቃቀም ገጽታ*

በሀዲያ ባህል ያገባች ሴት የተለየ የቋንቋ አጠቃቀም ስርአት አላት፤ በተለይም ለአማቾችዋ ያላትን አክብሮት የምትገልጽበት የተለየ የስም አጠራር ስርኣት አለ። ይህም በቋንቋዉ *በሉዊሻ* /Balluwwishsha/ የሚል መጠሪያ አለዉ:: *በል* /Ball-/ የሚለዉ ቃል አማች የሚል ፍች ሲኖረዉ፣ *በሉዋ* /Ball-uwwa/ የሚለዉ ደግሞ የአማች የብዙ ቁጥር ወይም አማቾች እንደማለት ነዉ:: በሌላ በኩል፣ *በሉዊሻ* (Balluwwishsha) ባለትዳር ሴት ለአማችዋ የምትሰጠዉን አክብሮት ገላጭ ቃል ነዉ፤ ቀጥታ ፍችዉም «አማች የማድረግ ሂደት» የሚል አንድምታ አለዉ:: /-ishsha/ የሚለዉ ምእላድ አንድ ነገር እንዲሆን ምክንያት የሆነን ነገር አመልካች ነዉ::

በሀዲያ ባህል፣ ባል ያገባች ሴት ባገባችበት ለሞን አማቾችዋን የምትጠራበትን ስርአት ያስተምሯታል:: በባህሉ የባል አባት፣ እናት፣ አጎት፣ አክስትና የባል ጎሳ ስም እንዳለ ወይም ቅርጹን ሳይቀይር አይጠራም፤ በሌላ ቃል ተተክቶ እንጂ:: ከዚህ ስርአት ዉጭ መጥራት ለሴት ልጅ ነዉር ወይም አይነኬ (taboo) ነዉ:: *የበሉዊሻ* አስተማሪ ብዙ ጊዜ የባል እህት





ስትሆን የማስተማሩ ስርአት ሲደረግም *ቡሎ* /Bullo/ የተባለን ባህላዊ ምግብ በእጇ ላይ በማስያዝ ነዉ:: በዚህ ጊዜ በእጇ ላይ *ቡሎ* አስይዘዋት ቡሎዉ ላይ ቅቤ እያፈሰሱላት የማይጠሩ ቃላትን አስተማሪዋ እየጠራች እንዲህ አይባልም፤ እንዲህ ነዉ የሚባለዉ እያለች፣ ቃላቱን እየዘረዘረች፣ አይጠሬ ምቹን ቃላት የሚጠሩበትን ስልት ታስተምራታለች:: ሙሽሪቷ በቀጣይ ህይወትዋም ያንን የተማረችበትን መንገድ ተከትላ አማቾችዋን ብትጠራ፣ አማቾችዋን አክባሪና በጥሩ ሁኔታ ያደገችና ስርአት ያላት እንደሆነች ይነገርላታል::

በአንጻሩ ድንገት ተሳስታ እንኳዋን የአማችዋን ስም ወይም የአማችዋ ስም በሚጠራበት ቃል የመጀመሪያ ፊደል (ፊደላት) ጋር የሚገጥም ሌላ ቃል እንኳዋን ብትጠራ ወዲያዉ ይቅርታ ካልጠየቀች ከቅጣት አታመልጥም:: የምትቀጣበት ምክንያት የባሏን ዘመዶች እንዳዋረደቻቸዉ ስለሚቆጠር ነዉ:: ለቅጣቱ የሚሆን በሬ የሚታረደዉ እንኳዋን፣ ከባሏ በመዉሰድ ሳይሆን ከወላጆችዋ በመዉሰድ ነዉ:: ነገር ግን፣ አስቀድማ ይቅርታ ከጠየቀች ከቅጣቱ እሚታመልጥበት እድል አለ፤የታላቅ ልጅዋን ስም በማንሳት በእገሌ ጠርቻለዉ ካለች ይቅርታ ይደረግላታል:: ለምሳሌ፣ የመጀመሪያ ልጅ ስም ሎምቤቦ ቢሆን በሎምቤቦ ጠርቻለሁ (ሎምቤብኔ ዌሻሞ / Lombeebinne weeshaammo/) ትላለች:: በቀጣዩ ክፍል በሀዲያ ባህል ሴቶች የባሎቻቸዉን አማቾች ወይም ዘመዶች የሚጠሩባቸዉን ስልቶች ይመለከቷል::

*ሀ. የበሉዊሻ ቃላት ፈጠራ*

በዚህ ስልት፣ ሌሎች የቋንቋ ተጠቃሚዎች ወይም ካገቡ ሴቶች ዉጭ ያሉ የባህሉ አባላት ለሚጠቀሙዋቸዉ ቃላት፣ ያገቡ ሴቶች በቀጥታ ስለማይጠሩ በምትኩ ሌላ ቃል ይፈጥራሉ:: በዚህ ስልት የሚፈጠሩት ቃላት ሙሉ በሙሉ